


# የገቢዎች ሚኒስቴር የ5 ዓመት ዝርዝር የልማት ዕቅድ (2013-2017)

ሰኔ 2012 ዓ.ም.

## የክቡር ሚኒስትሩ መልዕክት



የገቢዎች ሚንስቴር ሁለተኛውን ሀገራዊ የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ (2008-2012) መነሻ በማድረግ ሁለተኛውን የገቢው ዘርፍ የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ በማዘጋጀትና በመተግበር የሀገሪቱ ኢኮኖሚ የሚያመነጨውን የታክስ ገቢ በመሰብሰብ የሀገሪቱን የኢኮኖሚና ማህበራዊ ልማት ዕቅዶች በፋይናንስ በመደገፍ የልማቱን ቀጣይነት ለማረጋጋጥ ከፍተኛ ርብርብ ሲያደርግ ቆይቷል፡፡ በተደረገው ከፍተኛ ርብርብ ባለፉት 5 ዓመታት በታክስ አሰባሰብ ረገድ በአማካይ የ13 በመቶ ዕድገት ከመመዝገቡም በላይ የአገልግሎት አሰጣጡን በማሳለጥ የተጋልጋዮችን ዕርካታ ለማረጋጋጥ፣ የታክስና የጉምሩክ ማጭበርበርን በመከላከል የታክስ ፍትሃዊነትን ለማረጋገጥ፣ ለንግድና ኢንቨስትመንት ምቹ ከባቢ ለመፍጠር፣ የማህበረሰቡ ደህንነት ለመጠበቅ፣ ታክስ በፈቃደኝነት የመክፈል ባህልን ለማሳደግ እና የታክስ ህግ ተገዥነትን በማሻሻል ረገድ አበረታች መሻሻሎች እየታዩ መጥተዋል::

ሚኒስቴር መ/ቤታችን በቀጣይም የታክስ አስተዳደር ተግባራትን የበለጠ በማጠናከር መንግስት የነደፈውን የ10 ዓመት የብልጽግና ዕቅድ በፋይናንስ ለመደገፍ የሚያስችል የ10 ዓመት የገቢው ዘርፍ የብልጽግና ዕቅድ በማዘጋጀትና ይህንን ዕቅድ መነሻ በማድረግ የሀገሪቱን የኢኮኖሚ፣ ማህበራዊ እና የፖለቲካ ሁኔታ በመገምገም፣ ያላፉትን 5 ዓመታት የተቋሙን አፈፃፀም በመገምገም፣ አህጉራዊና ዓለም ዓቀፍ ሁኔታዎችን በመዳሰስ፣ የተገልጋዮች፣ የባለድርሻና አጋር አካላት ፍላጎት ትንተና በማካሄድ የገቢውን ዘርፍ የ5 ዓመት የመካከለኛ ዘመን ዕቅድ አዘጋጅቷል፡፡

ይህ የ5 ዓመት ስትራቴጂክ ዕቅድ የተዘጋጀው በዓለም አቀፍ ደረጃም ሆነ በሀገራችን የኮሮና ቫይረስ ወረርሽኝ በኢኮኖሚ፣ በጤናና በማህበራዊ ጉዳዮች ላይ ከፍተኛ ጫና እያሳደረ ባለበት ወቅት በመሆኑ ቫይረሱ የሚያሳድረውን ተፅዕኖ በመቀነስ የታክስ አስተዳደሩን ውጤታማ ማድረግን ታሳቢ ያደረገ ጭምር ነው፡፡ ይህም በተለይ የ5 ዓመቱ ዝርዝር ዕቅድ በመጀመሪያው የዕቅድ ዘመን በአንድ በኩል ቫይረሱ በታክስ አስተዳደሩ የዕለት ከዕለት እንቅስቃሴ ላይ የሚያሳድረውን ተፅዕኖ በመከላከል በሌላ በኩል ደግሞ መንግስት የነደፋቸው የልማት ዕቅዶች በበጀት ዕጥረት ምክንያት እንዳይደናቀፉ ከወትሮው በተለየ ሁኔታ ከሚመለከታቸው የመንግስት አካላት፣ ተገልጋዮች፣ ባለድርሻና አጋር አካላት ጋር ተቀናጅቶ

እና ህብረተሰቡን በማስተባበር የገቢ አሰባሰቡን ለማሻሻል ከፍተኛ ርብርብ ማድረግ ይጠበቅብናል፡፡

ስለሆነም መንግስት የቀረፃቸውን የኢኮኖሚና ማህበራዊ የልማት ዕቅዶች አስተማማኝ በሆነ መልኩ በፋይናንስ ለመደገፍ የተዘጋጀውን የ5 ዓመት የብልፅግና ዕቅድ ለማሳካት በምናደርገው ያልተቆጠበ ጥረት የንግዱ ማህበረሰብ፣ ተገልጋዮች፣ የመንግስት አካላት፣ የሀገር ውስጥና የውጭ አጋር አካላት እንዲሁም አጠቃላይ ህዝቡ የተጠናከረ ድጋፍና ትብብር እንድታደርጉልን ጥሪዬን አቀርባለሁ፡፡

ላቀ አያሌዉ

ሚኒስትር

## ማውጫ

1 መግቢያ ....... 1
2 የተቋሙ የመካከለኛ ዘመን ዕቅድ መነሻ ሁኔታዎች ....... 3
2.1 ሀገራዊ የብልፅግና ርዕይ እንደመነሻ ....... 3
2.2 የማክሮ ኢኮኖሚ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች እንደመነሻ ....... 3
2.3 ዓለም ዓቀፋዊ እና ከባቢያዊ ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች ዳሰሳ እንደመነሻ ....... 4
2.4 ዓለም ዓቀፋዊና አህጉራዊ ስምምነቶች እንደመነሻ ....... 4
2.5 ሀገራዊ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ አፈፃፀም ግምገማ እንደመነሻ ....... 4
2.6 የተቋሙ የአፈፃፀም ግምገማ እንደመነሻ ....... 5
3 የውስጣዊ እና ውጫዊ ሁኔታዎች የዳሰሳ ምልከታዎች ....... 11
3.1 የተቋሙ ዉስጣዊ ጥንካሬዎችና ድክመቶች ....... 11
3.2 ውጫዊ ሁኔታዎች ዳሰሳ ....... 13
3.3 ፈታኝ እና አስቻይ ሁኔታዎች ....... 16
3.4 ዋና ዋና ተግዳሮቶች እና የመፍትሄ ሀሳቦች ....... 17
4 የተቋሙ የአምስት ዓመት ስትራቴጂክ ዕቅድ ....... 21
4.1 የተጠቃለለ ተቋማዊ ርዕይ፣ ተልዕኮ፣ ዕሴቶች፣ የትኩረት መስኮች እና ዓላማዎች ....... 21
4.2 የተቋሙ ስትራቴጂካዊ አቅጣጫዎች ....... 22
4.3 ስትራቴጂያዊ የትኩረት መስኮች እና ዓላማዎች ....... 24
4.4 መለኪያዎች ....... 39
5 ስትራቴጂካዊ የማስፈፀሚያ እርምጃዎች ....... 45
5.1 የትኩረት መስኮች/ ስትራቴጂክ ግቦች /፣ ኢኒሼቲቮች እና ፕሮጀክቶች ....... 45
6 የተጓዳኝ ተቋማት የትስስር ፍላጎት ....... 48
6.1 የተቋማት የትስስር ደረጃ ....... 48
6.2 ትስስር የሚፈለግባቸው ዋና ዋና ጉዳዮች ....... 50
7 ስጋቶች እና የመፍትሄ ሃሳቦች ....... 55
8 የክትትልና ግምገማ ስርዓት ....... 57
8.1 የዕሴት መግለጫዎች ....... 57
9 የሰው ሀብት እና የፋይናንስ ፍላጎት ....... 59
9.1 የሰው ሀብት ፍላጎት ....... 59
9.2 የፋይናንስ ፍላጎት ....... 60
10 ዕዝሎች ....... 61
10.1የአምስት ዓመት የወጪ ፍላጎት (በቢሊዮን ብር) ....... 61
10.2የአምስት ዓመት የሰው ሀብት ፍላጎት ዕቅድ ....... 67
10.3የመለኪያዎች መግለጫ ....... 77

10.4የኢንዴክሶች መግለጫ ........ 83

## ሰንጠረዦች

ሰንጠረዥ 1፦ የተቋሙ ያለፉት ዓመታት የገቢ አፈፃፀም በቢሊዮን ብር ........ 5
ሰንጠረዥ 2፡ የታክስ ገቢ ከአጠቃላይ ሀገራዊ ምርት ያለዉ ጥምርታ ........ 6
ሰንጠረዥ 3፡ የተቋሙ ዉስጣዊ ጥንካሬዎችና ድክመቶች ........ 11
ሰንጠረዥ 4፡ ፈታኝ እና አስቻይ ሁኔታዎች ........ 16
ሰንጠረዥ 5፡ ዋና ዋና ተግዳሮቶች ........ 17
ሰንጠረዥ 6፡ ተግዳሮቶቹን ለመቅረፍ የቀረቡ የመፍትሄ ሀሳቦች ........ 19
ሰንጠረዥ 7፡ የተጠቃለለ ርዕይ፣ ተልዕኮ፣ ዕሴቶች፣ የትኩረት መስኮች እና ዓላማዎች ........ 21
ሰንጠረዥ 8፡ የዘላቂ ገቢ ዕድገት መለኪያዎች ........ 39
ሰንጠረዥ 9፡ የህግ ተገዥነት አመራር ልህቀት መለኪያዎች ........ 40
ሰንጠረዥ 10፡ የአሠራር ልህቀት መለኪያዎች ........ 42
ሰንጠረዥ 11፡ የስትራቴጂክ አጋርነት ልህቀት መለኪያዎች ........ 43
ሰንጠረዥ 12፡ ኢኒሼቲቮች እና ፕሮጀክቶች ........ 45
ሰንጠረዥ 13፡ የተቋማት የትስስር ደረጃ ........ 48
ሰንጠረዥ 14፡ ስጋቶች እና የመፍትሄ ሀሳቦች ........ 55
ሰንጠረዥ 15፡ የተጠቃለለ የሰው ሀብት ፍላጎት ........ 59
ሰንጠረዥ 16፡ የ5 ዓመት የፋይናንስ ፍላጎት በቢሊዮን ብር ........ 60
ሰንጠረዥ 17፡ የስትራቴጂክ ዕርምጃዎች ማስፈፀሚያ በጀት ........ 61
ሰንጠረዥ 18፡ የአገር ዉስጥ ታክስ የካፒታል በጀት እቅድ ........ 62
ሰንጠረዥ 19፡ የጉምሩክ ኮሚሽን የካፒታል በጀት እቅድ ........ 65
ሰንጠረዥ 20፡ ዝርዝር የሰው ሀብት ፍላጎት ........ 67

## ሥዕሎች

ምስል 1: የታክስ ሀገራዊ ምርት ጥምርታ ከሰሀራ በታች ባሉ ሀገራት ........ 7

# 1 መግቢያ

መንግስት ኢትዮጵያን የአፍሪካ የብልፅግና ተምሳሌት የማድረግ ርዕይ ለማሳካት የተረጋጋ የማክሮ ኢኮኖሚ ሁኔታን በመፍጠር ኢኮኖሚዉን በአማካይ በ10.2 በመቶ ለማሳደግ፣ የአምራች ዘርፎችን በመደገፍና ተወዳዳሪነትን በማጎልበት የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለዉጥ ለማረጋገጥ፣ የኢኮኖሚ እና ማህበራዊ መሰረተ ልማት ተደራሽነትን በማረጋገጥ ዜጎች የልማቱ ባለቤትና ተጠቃሚ ኢንዲሆኑ ለማድረግ እና የግሉን ዘርፍ ተሳትፎ ለማሳደግ የሚያስችሉ ዓላማዎችን ታሳቢ ያደረገ የአስር ዓመት የብልፅግና መሪ ዕቅድ መንደፉ ይታወቃል፡፡ በዚሁ መሰረት የገቢዎች ሚኒስቴር የሀገሪቱን የአስር ዓመት የብልፅግና መሪ ዕቅድ መነሻ በማድረግ መንግስት የነደፋቸዉን የኢኮኖሚና ማህበራዊ ልማት ዕቅዶች በፋይናንስ መደገፍ የሚያስችል የአሰር ዓመት የብልፅግና መሪ ዕቅድ አዘጋጅቷል፡፡

ሀገራችን ፈጣንና ፍትሃዊ የኢኮኖሚ ዕድገት በማስቀጠል የልማት ግቦቿን ለማሳካት በአስር ዓመት የብልጽግና መሪ ዕቅድ ዘመን ዉስጥ በመጀመሪያዎቹ አምስት ዓመታት የሚሰሩ ስራዎችን እና የሚጠበቁ ዉጤቶችን የያዘ የአምስት ዓመታት (2013-2017) የገቢዉ ዘርፍ ስትራቴጂክ ዕቅድ ተዘጋጅቷል፡፡ ይህም ዕቅድ የሚኒስቴር መ/ቤቱን ማህበረሰብ፣ ተገልጋዮችን፣ ባለድርሻ አካላትን እና የልማት ኃይሎችን በማስተባበር ፈጣን ሀገራዊ ዕድገትን ለማምጣትና በሂደቱም የዜጎችን እኩል ተሳታፊነትንና ፍትሃዊ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ያስችላል ማለት ነዉ፡፡

የሚኒስቴር መ/ቤቱ የአስር ዓመት የብልጽግና እቅድ የትኩረት መስኮች ቀጣይነት ያለው ተቋማዊ አቅም መገንባት፣ የአሰራር ልህቀትን ማረጋገጥ፣ ስትራቴጂያዊ አጋርነት ልህቀት ማምጣት፣ የህግ ተገዥነት አመራር ልህቀትን ማረጋገጥ እና ዘላቂ የገቢ ዕድገት ማምጣት ሲሆኑ እነኝህም በስራቸዉ አስራ አምስት ስትራቴጂክ ግቦችን ይዘዋል፡፡ የትኩረት መስኮቹንና የግቦቹን ዉጤታማነት ለማረጋገጥ ተቋሙ ታክስ በፈቃደኝነት የመክፈል ባህል ማሳደግ፣ ዲጂታል የገቢ አስተዳደር ስርዓትን መገንባት፣ ፍትሀዊነትን ለማረጋገጥ ኮንትሮባንድ፣ ታክስ ማጭበርበር እና ህቡዕ ኢኮኖሚን ወደ ታክስ ስርዓት ማምጣት፣ የዳበረ የስራ ባህል መገንባት እና ስትራቴጂክ አጋርነትን ማጠናከር የሚሉ አቅጣጫዎችን አስቀምጧል፡፡

የገቢዉ ዘርፍ ዕቅድ ተፈፃሚ ሲደረግ ሀገራዊ ገቢ የማመንጨት አቅምን በላቀ ደረጃ በማሳደግ እና የመንግስትን የወጪ ፍላጎት በመሸፈን የዜጎችን የኢኮኖሚና ማህበራዊ ተጠቃሚነት

በማረጋገጥ ሀገራችን ዝቅተኛ መካከለኛ ገቢ ካላቸዉ ሀገራት ተርታ ለማሰለፍ ቁልፍ ድርሻ የሚኖረዉ ሲሆን ዕቅዱ በቀጣይ ወደ ዓመታዊ ዕቅድ እየተመነዘረ በስራ ላይ የሚዉል ይሆናል፡፡

ሰነዱ መግቢያውን ጨምሮ ዘጠኝ ክፍሎች ያሉት ሲሆን የሁለተኛው ክፍል የተቋሙ የመካከለኛ ዘመን ዕቅድ መነሻ ሁኔታዎችን ይዟል፡፡ በክፍል ሶስት የዉስጣዊና እና ዉጪያዊ ሁኔታዎች የዳሰሳ ምልከታዎች የተካሄዱበት ሲሆን ክፍል አራት የተቋሙ የአምስት ዓመት ስትራቴጂክ ዕቅድን ይዟል፡፡ በክፍል አምስት ስትራቴጂካዊ የማስፈፀሚያ እርምጃዎች የተዳሰሱበት ሲሆን በሌላ በኩል በክፍል ስድስት የተጓዳኝ ተቋማት የትስስር ደረጃ እንዲካተት ተደርጓል፡፡ በክፍል ሰባት ስጋቶችና የመፍትሄ ሃሳቦች እንዲመላከቱ ተደርጓል፡፡ በመጨረሻዎቹ ሁለት ክፍሎች የክትትልና ግምገማ ስርዓት እና የተቋሙ የሰዉ ሃብት እና የፋይናንስ ፍላጎት እንዲቀመጥ በማድረግ የአምስት ዓመቱ ዝርዝር ዕቅድ እንዲዘጋጅ ተደርጓል፡፡

# 2 የተቋሙ የመካከለኛ ዘመን ዕቅድ መነሻ ሁኔታዎች

የዘርፉ የመካከለኛ ዘመን ስትራቴጂክ እቅድ ዝግጅት መነሻዎች የሀገራችን የረዥም ጊዜ ራዕይ፣ የማክሮ ኢኮኖሚ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች፣ ህጎችና የአሰራር ስርዓቶች፣ ዓለም አቀፋዊ እና ከባቢያዊ ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች ዳሰሳ፣ ዓለም አቀፋዊና አህጉራዊ ስምምነቶች፣ ሀገራዊ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን አቅድ አፈጻጸም ግምገማ እና የተቋሙ ያለፉት ዓመታት አፈፃፀም ግምገማ ለዘርፉ የመካከለኛ ዘመን ስትራቴጂክ ዕቅዱ ዝግጅት እንደመነሻነት ተወስደዋል።

## 2.1 ሀገራዊ የብልፅግና ርዕይ እንደመነሻ

በሀገር ደረጃ የተነደፈው የብልፅግና ዕቅድ እንደመነሻ ይዞ የተነሳው ርዕይ "ኢትዮጵያ፤ የአፍሪካ የብልፅግና ተምሳሌት" (African Beacon of Prosperity) ማድረግ የሚለዉን ነው። ብልፅግና ሲባል በጥቅል የዜጎችን ነፃነት በሂደት እየጨመረ የሚሄድ ማህበረሰብ መገንባት በሚለው አግባብ የተሰላ ሆኖ ዝርዝርና ተጨባጭ መገለጫዎች እንዳሉት ይታወቃል። ስለሆነም በቀጣዩ የመካከለኛ ዘመን ዕቅድ ውስጥ የሚከናወኑ የልማት ተግባራት በሙሉ ወደዚህ ርዕይ በሂደት በአስተማማኝ ሁኔታ የሚያደርሱ መሆናቸዉን እያረጋገጡ መሄድን ይጠይቃል። ስለሆነም የገቢዉ ዘርፍ ወደ ሀገራዊ ርዕይ የሚያደርሱ ርዕይ፣ ተልዕኮ፣ የትኩረት አቅጣጫዎች፣ የትኩረት መስኮች፣ ዓላማዎች እና ግቦችን ከአስር ዓመት ዕቅዱ ወስዷል። ስለሆነም የአምስት ዓመቱ ዕቅድ ከአስር ዓመቱ ዕቅድ ጋር የተሳሰረ በመሆኑ እና የመጀመሪያዉ ምዕራፍ ዕቅድ መሳካት ለሁለተኛዉ ምዕራፍ ዕቅድ አፈፃፀም ወሳኝ ሚና የሚኖረዉ መሆኑን ተገንዝቦ መስራትና መረባረብ የሚጠይቅ በመሆኑ ሀገራዊ ርዕይ ለመካከለኛዉ ዘመን ዕቅድ ዝግጅት በመነሻነት ተወስዷል።

## 2.2 የማክሮ ኢኮኖሚ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች እንደመነሻ

ሀገራችን ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት በማስመዝገብ መዋቅራዊ ለውጥ ለማምጣትና በየደረጃው የህዝቡን ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የሚያስችሉ የማክሮ ኢኮኖሚ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች፣ ህጎችና አሰራሮች እንዲሁም የሀገር በቀል የኢኮኖሚ ሪፎርም ያስቀመጣቸው ቁልፍ የትኩረት አቅጣጫዎች ማለትም የማክሮ ኢኮኖሚ፣ የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለዉጦችና እና የኢኮኖሚ ዘርፎች ማሻሻያዎች ለተቋሙ የመካከለኛ ዘመን ስትራቴጂክ እቅድ ዝግጅት እንደመነሻ ተወስደዋል።

ከዚህ ጋር ተያይዞ አሁን በሀገሪቱ ያለዉ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ በተሻለ ሁኔታ ዕድገት እንደሚያሳይ፣ የንግድ ስርዓቱ የተረጋጋ ሆኖ እንደሚቀጥል፣ የሚታየዉ የዉጪ ምንዛሬ ዕጥረት በቀጣይ ዓመታት የሚቀረፍ መሆኑን እና በገቢያ ላይ የሚታየዉ የዋጋ ግሽበት አሁን ካለበት ያነሰ እንደሚሆን ታሳቢ ተደርጓል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ህገወጥ የንግድ እንቅስቃሴና የህቡዕ ኢኮኖሚ ስራዎች ወደ ህጋዊ የታክስ ስርዓት እንዲመጡ ለማደረግ ከአጋር አካላት ጋር በጋራ እንደሚሰራ ታሳቢ ተደርጓል፡፡

## 2.3 ዓለም ዓቀፋዊ እና ከባቢያዊ ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች ዳሰሳ እንደመነሻ

የዓለም ኢኮኖሚ ሁኔታ ፈጣን ተለዋዋጭነት የሚታይበት በመሆኑ ለውጡ በሀገራችን ኢኮኖሚ እና በገቢዉ ዘርፍ ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድር መሆኑ እና በዚሁ መሰረት በታክስ አስተዳደሩ ላይ ተፅዕኖ ከሚያሳድሩት ዋና ዋና ጉዳዮች መካከል የንግድ፣ የኢንቨስትመንት እና የቴክኖሎጂ ዕድገትና ለዉጦች ለእቅድ ዝግጅቱ እንደመነሻ ተወስዷል፡፡

## 2.4 ዓለም ዓቀፋዊና አህጉራዊ ስምምነቶች እንደመነሻ

ዓለም ዓቀፍና ከባቢያዊ ሁኔታዎችን በተመለከተ አሁን ባለንበት ዘመንና በቀጣዮቹ ዓመታትም የዓለም ኢኮኖሚ ሁኔታ ፈጣን ተለዋዋጭነት የሚታይበት በመሆኑ እነዚህ ለውጦች በሀገራችን ኢኮኖሚ እና በገቢዉ ዘርፍ ላይ አዎንታዊና አሉታዊ ተፅዕኖ ማሳረፋቸው የማይቀር ነው፡፡ ምንም እንኳን አሁን ላይ ሆኖ በቀጣይ ዓመታት የሚሆነውን የዓለምን ኢኮኖሚ ሁኔታ በትክክል መተንተን እና መተንበይ አስቸጋሪ ቢሆንም በዋናነት ግን መሰረታዊ የሆኑ እና በገቢዉ ዘርፍ ላይ ቀጥተኛ የሆነ ተፅዕኖ ሊያሳድሩ የሚችሉት የንግድ፣ የኢንቨስትመንት፣ የቴክኖሎጂ እና የማህበራዊ ጉዳይ አዝማሚያዎችን ከግምት ውስጥ ማስገባት በጣም አስፈላጊ በመሆኑ ለተቋሙ የመከከለኛ ዘመን የአምስት ዓመት ስትራቴጂክ ዕቅዱ ዝግጅት እንደ መነሻ ተወስደዋል፡፡

## 2.5 ሀገራዊ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን አቅድ አፈፃፀም ግምገማ እንደመነሻ

ባለፉት ሁለት የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ትግበራ ዓመታት (2003-2012) ተከታታይነት ያለው የሁለት አሃዝ የኢኮኖሚ ዕድገት ተመዝግቧል፡፡ በሌላ በኩል በዕቅድ

ዘመኑ የታክስ ገቢ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ያለው ድርሻ በ2003 በጀት ዓመት ከነበረበት የ11.4 በመቶ በ2012 በጀት ዓመት ወደ 9.2 በመቶ ዝቅ ብሏል:: ይህም በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን በ2012 በጀት ዓመት ይደረስበታል ተብሎ ከተገመተዉ የ17.2 በመቶ ግብ አንፃር ሲታይ ዝቅተኛ መሆኑን ያሳያል:: ይህ አፈፃፀም ከሰሃራ በታች የሚገኙ የአፍሪካ ሀገሮች ካስመዘገቡት አንፃር ሲታይም በጣም አነስተኛ መሆኑን ከግንዛቤ በማስገባት ለእቅድ ዝግጅቱ በመነሻነት ተወስዷል::

## 2.6 የተቋሙ የአፈፃፀም ግምገማ እንደመነሻ

የዘርፉ የገቢ አፈፃፀም፣ የገቢ ፊሲካል ስራዎች እና ሌሎች አንኳር ተግባራት አፈፃፀም ግምገማ ለእቅድ ዝግጅቱ በመነሻነት ተወስዷል:: በዚህም መሰረት የተቋሙ የባለፉት ዓመታት የገቢ አፈፃፀም ግምገማ በሚከተለዉ ሰንጠረዥ 1 መሰረት ቀርቧል::

### 2.6.1 የገቢ አፈፃፀም ግምገማ

ሰንጠረዥ 1፦ የተቋሙ ያለፉት ዓመታት የገቢ አፈፃፀም በቢሊዮን ብር

| መግለጫ | የዕድገት እና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ (ዕትዕ) | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ዕትዕ 1 | | | | | ዕትዕ 2 | | | | | የዕትዕ አማካይ |
| | 2003 | 2004 | 2005 | 2006 | 2007 | 2008 | 2009 | 2010 | 2011 | 2012 | |
| ዕቅድ (በቢሊዮን ብር) | 54.18 | 76.37 | 101.66 | 116.80 | 134.20 | 146.26 | 186.14 | 230.14 | 241.69 | 270.21 | 155.77 |
| ዓመታዊ ገቢ (በቢሊዮን ብር) | 50.82 | 70.75 | 84.41 | 106.80 | 128.32 | 144.35 | 160.18 | 176.10 | 198.23 | 233.73 | 135.37 |
| አፈፃፀም በመቶኛ | 94.8 | 92.6 | 83.0 | 91.4 | 95.6 | 98.7 | 86.1 | 76.5 | 82.0 | 86.50 | 88.72 |
| የገቢ ዕድገት (በቢሊዮን ብር) | 15.12 | 19.93 | 13.67 | 22.38 | 21.52 | 16.03 | 15.83 | 15.92 | 22.13 | 35.50 | 19.80 |
| የገቢ ዕድገት (በመቶኛ) | 42.31 | 39.22 | 19.32 | 26.52 | 20.15 | 12.49 | 10.97 | 9.94 | 12.57 | 17.91 | 21.14 |

*ምንጭ: - የተቋሙ ያለፉት ዓመታት የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርቶች*

ከላይ በቀረበዉ ሠንጠረዥ እንደተመለከተዉ በባለፉት አስር የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ትግበራ ዓመታት (2003-2012) የገቢ አፈፃፀሙ በአማካይ በየዓመቱ በ21.1 በመቶ ዕድገት አሳይቷል:: የገቢ አሰባሰቡ በየዓመቱ ዕድገት እያሳየ የመጣ ቢሆንም አፈፃፀሙ ከአማካይ ዕቅዱ አንፃር ሲታይ በ11.3 በመቶ ጉድለት ታይቶበታል:: ለገቢ አሰባሰቡ ጉድለት ተጠቃሽ ከሆኑ

ምክንያቶች መካከል የተቋሙ የማስፈፀም አቅም ውሱንነት፣ የታክስ አስተዳደሩ በመረጃ ቴክኖሎጂ በሚገባ አለመደገፉ፣ የአገልግሎት አሰጣጥ አርኪ አለመሆን፣ የታክስ ስወራ እና ማጭበርበር መስፋፋት፣ የህገወጥ ንግድ እና ኮንትሮባንድ መንሰራፋት፣ የቀረጥ እና ታክስ እፎይታ መብቶች በከፍተኛ ሁኔታ መጨመር፣ ከባለድርሻ አካላት ጋር ያለው ቅንጅት ጠንካራ አለመሆን፣ የህቡዕ ኢኮኖሚ መስፋፋት እና የታክስ መሰረቱ አለመስፋት ዋና ዋናዎቹ ናቸዉ::

በሌላ በኩል ከታች በቀረበዉ ሰንጠረዥ እንደተመለከተዉ ባለፉት የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ትግበራ ዓመታት የታክስ ከአጠቃላይ ሀገራዊ ምርት ጥምርታ ያለዉን ድርሻ በአማካይ 14.27 በመቶ ለማድረስ ታቅዶ አፈፃፀሙ በአማካይ 11.46 በመቶ ሊሆን ችሏል:: ይህ አፈፃፀም ከዕቅዱ ጋር ሲነፃፀር በ19.67 በመቶ ዝቅ ያለ ነዉ::

ሰንጠረዥ 2፡ የታክስ ገቢ ከአጠቃላይ ሀገራዊ ምርት ያለዉ ጥምርታ

| መግለጫ | ዕትዕ 1 | | | | | ዕትዕ 2 | | | | | የዕትዕ አማካይ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 2003 | 2004 | 2005 | 2006 | 2007 | 2008 | 2009 | 2010 | 2011 | 2012 | |
| ዕቅድ (ቢሊዮን ብር) | 56.17 | 87.13 | 110 | 133.12 | 158.24 | 195.04 | 226.89 | 266.61 | 289.52 | 331.04 | 185.38 |
| ዓመታዊ ገቢ (ቢሊዮን ብር) | 58.98 | 85.74 | 107.01 | 133.12 | 165.28 | 190.52 | 210.17 | 235.23 | 268.46 | 311.48 | 176.60 |
| አፈፃፀም በመቶኛ | 105.00 | 98.40 | 97.28 | 100.00 | 104.45 | 97.68 | 92.63 | 88.23 | 92.72 | 94.09 | 97.05 |
| የገቢ ዕድገት (ቢሊዮን ብር) | 15.66 | 26.76 | 21.27 | 26.11 | 32.16 | 25.24 | 19.65 | 25.06 | 33.23 | 43.02 | 26.82 |
| የገቢ ዕድገት (በመቶኛ) | 36.16 | 45.37 | 24.81 | 24.40 | 24.16 | 15.27 | 10.32 | 11.92 | 14.13 | 16.02 | 22.26 |
| አጠቃላይ ሀገራዊ ምርት (በቢሊዮን ብር) | 515.08 | 747.33 | 866.92 | 1,060.83 | 1,297.96 | 1,568,1 | 1,832.55 | 2,202.373 | 2,696.22 | 3,374.35 | 1,621.51 |
| የታክስ አጣቃላይ ሀገራዊ ምርት ጥምርታ ዕቅድ (GDP) | 11.70 | 12.10 | 13.20 | 14.70 | 15.00 | 13.70 | 14.00 | 15.20 | 15.90 | 17.20 | 14.27 |

| መግለጫ | ዕቅድ 1 | | | | | ዕቅድ 2 | | | | | የዕቅድ አማካይ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 2003 | 2004 | 2005 | 2006 | 2007 | 2008 | 2009 | 2010 | 2011 | 2012 | |
| የታክስ አጣቃላይ ሀገራዊ ምርት ጥምርታ አፈጻጸም (Tax/GDP) | 11.40 | 11.50 | 12.40 | 12.70 | 12.70 | 12.10 | 11.50 | 10.70 | 10.40 | 9.23 | 11.46 |

ምንጭ: - የገንዘብ ሚኒስቴር ዓመታዊ ሪፖርት

የኢኮኖሚ ትብብርና ልማት ድርጅት (OECD) 2017 መረጃ መሠረት የ26 የአፍሪካ ሀገራት አማካኝ የታክስ ሀገራዊ ምርት ጥምርታ 17.2% ነው። የኢትዮጵያ 10.7% ሲሆን ይህም ከ26 የአፍሪካ ሀገራት

ምስል 1፡ የታክስ ሀገራዊ ምርት ጥምርታ ከሰሀራ በታች ባሉ ሀገራት




አማካይ በ61% ያነሰ ነው።

## 2.6.2 የአሠራር ስርዓት አፈፃፀም ግምገማ እንደ መነሻ

ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ከሚመለከታቸዉ አካላት ጋር በመቀናጀት ለንግድና ኢንቨስትመንት ምቹ ከባቢ ለመፍጠር እና ታክሱን ለማስተዳደር የሚያስችሉ አዋጆች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎች እና የአሰራር ስርዓቶች ተቀርፀዉ በስራ ላይ እንዲዉሉ በማድረጉ በአገልግሎት አሰጣጥ፣ የታክስ ህጎችን በማስከበርና የገቢ አሰባሰቡን በማሻሻል ረገድ የበኩላቸዉን አስተዋጽዎ

አበርክተዋል። ይሁን እንጂ የተዘጋጁት የህግ ማዕቀፎች እና የአሰራር ስርዓቶች ከወቅታዊ የሀገሪቱ የኢኮኖሚ ዕድገትና የንግድ እንቅስቃሴ አንፃር በየጊዜዉ እየተቃኙ እንዲሻሻሉ አለመደረጋቸዉ እና ዝርዝር የአፈፃፀም መመሪያ ያልተዘጋጀላቸዉም በመኖራቸዉ በአገልግሎት አሰጣጥ፣ በንግድ ስራ አመቺነት፣ በህግ ማስከበር እና በገቢ አሰባሰብ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ አሳድረዋል።

### 2.6.3 የህግ ተገዥነት አፈፃፀም ግምገማ እንደ መነሻ

የህግ ተገዥነትን ለማሳደግ የተጠናከረ የግንዛቤ ማስጨበጫ ከማካሄድ ጀምሮ ኮንትሮባንድንና ህገወጥ ንግድን፣ ንግድ ማጭበርበርን እና ታክስ ስወራን ለመከላከል የሚያስችሉ ስራዎች ተከናዉነዋል። ከነዚህም መካከል የስጋት ስራ አመራር ስርዓትን በመተግበር፣ የኢንተለጀንስ እና የድንገተኛ ፍተሻ አሰራርን በማሻሻል፣ የኦዲት ዉጤታማነትን በማረጋገጥ፣ ሀገራዊ የፀረ ኮንትሮባንድ ንቅናቄ በመፍጠር፣ የታክስና የጉምሩክ ጉዳዮችን በፍርድ ቤት የመርታት አቅምን በማሳደግ እና የህቡዕ ኢኮኖሚ መከላከያ ስትራቴጂ በመቅረፅና በመተግበር ህገወጥነትን ለመከላከል የተከናወኑ ዋና ዋና ስራዎች ናቸዉ።

ከላይ እንደተገለፀዉ የታክስና ጉምሩክ ህግ ተገዥነትን ለማሳደግ በርካታ ስራዎች ቢከናወኑም ህገወጦች በየጊዜዉ የሚጠቀሙባቸዉ ዘዴዎች እየረቀቁና እየተወሳሰቡ በመሄዳቸዉ፣ የተቋሙ የመፈፀም አቅም ዉስንነት፣ እና ከሌሎች አጋር አካላት ጋር በሚገባ ተቀናጅቶ ህግን ማስከበር ባለመቻሉ ኢኮኖሚዉ የሚያመነጨዉን የታክስ ገቢ በብቃት መሰብሰብ እና የታክስ ፍትሃዊነት ማረጋገጥ አልተቻለም።

### 2.6.4 የአገልግሎት አሰጣጥ አፈፃፀም ግምገማ እንደ መነሻ

ተቋሙ የተገልጋዮችን ዕርካታ በማረጋገጥ የታክስ ገቢን በብቃት ለመሰብሰብ የሚያስችሉ በርካታ የአገልግሎት አሰጣጥ የሪፎርም ስራዎችን አከናዉኗል። ከነዚህም መካከል የመፈፀም አቅምን ለማሳደግና የአገልጋይነት አመለካከትን ለማስረፅ የተከናወኑ ሰፋፊ የአቅም ግንባታ ስራዎች፣ በስታንዳርድ መሰረት አገልግሎት ለመስጠት የተገልጋዮች ቻርተር ተቀርጾ መተግበሩ፣ የአገልግሎት አሰጣጡን በቴክኖሎጂ ለማስደገፍ በበይነ መረብ ታክስን ማሳወቅና መክፈል፣ የአንድ መስኮት የምዝገባ አገልግሎት፣ የጉምሩክ ትራንዚት፣ የዕቃ አወጣጥ፣ የመጋዘን እና የስጋት ስራ አመራር ተጠቃሾች ናቸዉ።

ይሁንና የአገልግሎት አሰጣጡን ዘመናዊ፣ ተደራሽና በስታንዳርድ የተለካ ለማድረግ እና የተገልጋዮችን ዕርካታ ለማሳደግ ያልተቆጠበ ጥረት ቢደረግም የአገልግሎት የሪፎርም ስራዎቹ የተገልጋዩን የህግ ተገዥነት ወጪ በመቀነስ፣ የአገልጋይነት አመለካከት በሚፈለገዉ ደረጃ በማዳበር እና ተነሳሽነት በመፍጠር፣ የገቢና ወጪ ንግድ ስራዎችን በማሳለጥ፣ የአቤቱታ አፈታት ስርዓቱን በማቀላጠፍ፣ በአጠቃላይ ዓለም ዓቀፍ ደረጃዉን የጠበቀ ግልፅ፣ ቀልጣፋ፣ ተገማችና ተደራሽ አገልግሎት በመስጠት የተገልጋዮችን ዕርካታ ማረጋገጥና በፈቃደኝነት የሚከፈለዉን የታክስ ገቢ በሚፈለገዉ ደረጃ ማሳደግ አልተቻለም፡፡

### 2.6.5 የአጋር አካላት ቅንጅታዊ አሰራር አፈፃፀም ግምገማ እንደ መነሻ

ተቋሙ የተሰጠውን ተልዕኮ ለማሳካት በሀገር ውስጥ እና በውጪ ካሉ አጋር አካላት ጋር በመቀናጀት እየሰራ ይገኛል፡፡ ይህ ቅንጅት ተቋሙ ተልዕኮዉን በአግባቡ ለመወጣት እንዲያስችለዉ የቴክኒክ ድጋፍ፣ የዕዉቀት ሽግግር፣ የመረጃ ልዉዉጥ፣ የታክስ ስርዓትን ለማጣጣም፣ የህብረተሰቡን ደህንነት ለመጠበቅ፣ቅንጅታዊ አሰራርን ለማስፈን እና የህግ ተገዥነትን ለማረጋገጥ ዓላማ ያደረገ ነዉ፡፡ ከዚህ አኳያ የተቋሙን ተልዕኮ ለማሳካት ከባለድርሻ አካላት፣ ከንግዱ ማህበረሰብ፣ ከሞያ እና ሲቪክ ማህበራት፣ ከድንበር አስተዳደር አካላት ጋር ተቀናጅቶ በመስራት ለገቢዉ አሰባሰብና የህግ ተገዥነት ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ጥረቶች ተደርገዋል፡፡

ይሁን እንጂ የህግ ተገዥነትን በማረጋገጥ የታክስ ገቢን ከማሳደግ አኳያ ከዉስጥና ከዉጪ አጋር አካላት ጋር የተፈጠረዉ ቅንጅታዊ አሰራር በስትራቴጂ ተደግፎ ቀጣይነት ባለዉ አግባብ መመራት ባለመቻሉ ምክንያት ቅንጅታዊ አሰራሩ በሚጠበቀዉ ልክ ዉጤታማ መሆን አልቻለም፡፡

### 2.6.6 የታክስ መረጃ እና የቴክኖሎጂ አፈፃፀም ግምገማ እንደ መነሻ

የታክስ መረጃ እና ቴክኖሎጂ ለታክስ አስተዳደሩ ዉጤታማነት ወሳኝ ድርሻ አላቸዉ፡፡ በመሆኑም የመረጃ ምንጮችን ለይቶ የመሰብሰብ፣ የማደራጀት፣ የማጠናቀር፣ የመተንተን፣ የማሰራጨት እና ጥቅም ላይ የማዋል ስራዎችን በማከናወን የታክስ አሰባሰቡና እና የጉምሩክ ስነ-ስርዓት አፈፃፀሙ በተጨባጭ መረጃ ላይ እንዲመሰረት ጥረት ተደርጓል፡፡

የታክስ አስተዳደር ስርዓቱ በቴክኖሎጂ እንዲደገፍ በማድረግ የታክስ አስተዳደሩ ዘመናዊ፣ ለአገልግሎት አሰጣጡ ቀልጣፋ፣ ፈጣን፣ ተደራሽ፣ ወጪ ቆጣቢ፣ አስተማማኝ እና ደህንነቱ የተጠበቀ የመረጃ ክምችት እንዲኖር ለማድረግ ተሞክሯል፡፡

ነገር ግን የታክስ መረጃ አስተዳደር ስርዓቱ ሁሉንም የመረጃ ምንጮች ባማከለ መልኩ በጥራት የማይሰበሰብ፣ የማይደራጅ፣ የማይተነተን፣ የማይሰራጭ እና ጥቅም ላይ የማይዉል ሲሆን የታክስ ስርዓቱን በዘመናዊ ቴክኖሎጂ ከማስደገፍ አኳያ ሲታይ ከወቅታዊ ተለዋዋጭ የቴክኖሎጂ ዕድገት፣ በየጊዜዉ እያደገ ከመጣዉ የአገልግሎት ፍላጎት፣ ከአጠቃቀም አኳያ ዉስንነት በመኖሩ የተቋሙ የመረጃ ቅብብሎሽ፣ የአገልግሎት አሰጣጥ እና የገቢ አሰባሰብ በሚፈለገዉ መጠን ሊደግፍና ሊያዘምን አልቻለም፡፡

## 2.6.7 የሰብዓዊ እና ቁሳዊ ሀብቶች አፈፃፀም ግምገማ እንደ መነሻ

ሰብዓዊና ቁሳዊ ሀብቶች የተቋሙን ተልዕኮ ለማሳካት የማየተካ ሚና አላቸዉ፡፡ ከዚህ አኳያ ተቋሙ አደረጃጀት በመቅረፅ፣ የሰዉ ሀብት ምልመላና ሙሌት በመተግበር፣ የማትጊያና የማቆያ ስርዓቶችን በመዘርጋት፣ የሰራተኛ አስተዳደርና የስነ-ምግባር ደንብ በስራ ላይ በማዋል፣ የአቅም ግንባታ ስልጠናዎችን በማካሄድ፣ የሰራተኛዉን ተነሳሽነትና ምርታማነት በማሳደግ የተቋሙን አፈፃፀም በማሻሻል ረገድ የበኩሉን አስተዋፅዎ አበርክቷል፡፡ በሌላ በኩል ለታክስ አስተዳደር አስፈላጊ የሆኑ የመደበኛና የካፒታል የበጀት ፍላጎት በማቅረብ፣ በማስፈቀድ፣ ለዋና ዋና የተቋሙ ተግባራት ትኩረት በመስጠት መደልደል፣ በቁጠባ በመጠቀም፣ አጠቃቀሙን በመከታተልና በመገምገም የተመደበዉን ዉስን ሀብት በአግባቡ በስራ ላይ ለማዋል ጥረት ተደርጓል፡፡

ይሁን እንጂ ከተቋሙ የስራ ስፋት፣ ዉስብስብነትና ልዩ ባህሪን የሚመጥን አቅሙ የተገነባ እና ተነሳሽነት ያለዉ የሰዉ ኃይል በሚፈለገዉ ደረጃ ማፍራትና ማቆየት ባለመቻሉ በተቃሙ አፈፃፀም ላይ ተፅዕኖ እያሳደረ ይገኛል፡፡ በሌላ በኩል ተቋሙ ለሰራተኛና ለተገልጋዩ ምቹ የሆነ የስራ ቦታ ለማመቻቸት፣ኮንትሮባንድ እና ህገወጥ ንግድን ለመከላከል የሚያስችል ግብዓት ለማሟላት፣ ተቋሙን በቴክኖሎጂዎች ለማዘመን የሚያስችል የበጀት ድጋፍ አለመኖሩና የተመደበዉም አነስተኛ በጀትም ቢሆን በአግባቡ በጥቅም ላይ ማዋል አለመቻል በስራዉ ላይ ተፅዕኖ እያሳደረ ይገኛል፡፡

# 3 የውስጣዊ እና ውጫዊ ሁኔታዎች የዳሰሳ ምልከታዎች

## 3.1 የተቋሙ ዉስጣዊ ጥንካሬዎችና ድክመቶች

ሰንጠረዥ 3፡ የተቋሙ ዉስጣዊ ጥንካሬዎችና ድክመቶች

| ስትራቴጂክ ጉዳዮች | ጥንካሬ (Strength) | ድክመት (Weakness) |
|---|---|---|
| የማስፈፀም አቅም | • ለሠራተኞች ተከታታይ ሙያዊ ስልጠና በመስጠት የሰራተኛ ምርታማነት ዕያደገ መምጣቱ፣<br>• የተለያዩ ሙያና ዕውቀት ያላቸውን የከፍተኛ ትምህርት ምሩቃንን መልምሎና አሰልጥኖ ወደ ተቋሙ በመቀላቀል ያለዉን የሰለጠነ የሰዉ ኃይል ዕጥረት ለመቅረፍ መቻሉ፣<br>• ተቋሙ የተሰጠዉን ተግባርና ኃላፊነት በዉጤታማነት ለመወጣት በየጊዜዉ ከነባራዊ ሁኔታ ጋር የተጣጣመ የአደረጃጀት ማስተካከያ ማድረጉ፣<br>• የታክስና ጉምሩክ አስተዳደር ስራዎችን በመረጃ ቴክኖሎጂ ለማስደገፍ ጥረት መደረጉ፣ | • የሰው ሀብት ስራ አመራር ስትራቴጂ ተቀርጾ አለመተግበሩ፣<br>• የሰራተኛ የመፈፀምና አመራሩ የማስፈፀም ዉስንነት የሚታይበት መሆኑ፣<br>• የአገልጋይነት አመለካከት በሚፈለገው ደረጃ አለመዳበሩ፣<br>• በየዕርከኑ ያለው አመራር ከማቀድ፣ ወደ ፈፃሚ ከማዉረድ፣ ተቀናጅቶ ከመስራት፣ ክትትል እና ድጋፍ ከማድረግ አንፃር ክፍተት መኖሩ፣<br>• የስራ አፈፃፀም ምዘና ሥርዓት ቢቀረጽም በተሟላ ሁኔታ መተግበር አለመቻሉ፣<br>• ተቋም ዓቀፍ ስጋት ስራ አመራር ስርዓት በሚፈለገዉ ደረጃ ተግባራዊ አለመደረጉ፣<br>• ምቹ የስራ አካባቢ በተሟላ መልኩ አለመፈጠሩ፣<br>• የመረጃ ቴክኖሎጂ አስተዳደር ፖሊሲ እና ስትራቴጂ ተቀርጾ አለመተግበሩ፣<br>• ከወሳኝ ባለድርሻ አካላት ጋር በመረጃ ቴክኖሎጂ ትስስር አለመፈጠሩ፣<br>• የታክስ አስተዳደሩ አሰራሮችን በተሟላ መንገድ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ አለመደገፉና ያሉትንም ቢሆን በአግባቡ መጠቀም የሚያስችል አቅም አለመፈጠሩ፣<br>• በሀብት አስተዳደር ረገድ የአጠቃቀም ክፍተቶች መኖራቸዉ፣<br>• የፕሮጀክት ስራ አመራር ክፍተት ያለበት መሆኑ፣ |
| አገልግሎት አሰጣጥ | • የተገልጋዮች ቻርተር ተዘጋጅቶ መተግበሩ፣<br>• አገልግሎት ተደራሽ ለማድረግ የታክስ ማዕከሎችንና የጉምሩክ መቅረጫ ጣቢያዎችንና | • አሠራሮች ለተገልጋዮች ግልፅ፣ ቀላል፣ ተገማችና ተደራሽ አለመሆን፣<br>• አገልግሎቱን ለማሳለጥ የሚያስችል የኢ-ታክስ ሥርዓት በተሟላ መንገድ ተዘርግቶ አለመተግበሩ፣ |

| ስትራቴጂክ ጉዳዮች | ጥንካሬ (Strength) | ድክመት (Weakness) |
|---|---|---|
| | መስኮቶችን በመክፈት ወደ ሥራ እንዲገቡ መደረጉ፤<br>• የንግድ ስርዓቱን ለማሳለጥ እና ለግብር ከፋዩ ወጪና ጊዜ ቆጣቢ አገልግሎት ለመስጠት ይቻል ዘንድ በየጊዜው አዳዲስ የህግና የአሠራር ስርዓቶች መቀረፃቸዉና መሻሻላቸዉ፣<br>• ተገልጋዮች የሚያቀርቧቸውን የታክስና የጉምሩክ ዉሳኔ ቅሬታዎች ለመፍታት የሚያስችል አደረጃጀትና አሰራር ከዋናው መ/ቤት እስከ ቅ/ጽ/ቤት ድረስ ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉ፣<br>• በየዓመቱ የተገልጋዮች የዕርካታ ዳሰሳ ጥናት በማድረግ ለአገልግሎት ማሻሻያ በግብዓትነት መወሰዱ፣ | • ከአጋር ድርጅቶች ጋር ያለዉ ቅንጅታዊ አሰራር ደካማ መሆኑ በአገልግሎት አሰጣጡ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ማሳደሩ፣<br>• የተገልጋዮችን ዕርካታ በሚፈለገዉ ደረጃ ማረጋገጥ አለመቻል፣ |
| ህግ ማስከበር | • የታክስና ጉምሩክ ወንጀሎችን ለመከላከል የሚያስችል የህግ ማዕቀፍ ተቀርፆ የታክስ ህጎችን ለማስከበር እንቅስቃሴ መጀመሩና ውጤትም እየተመዘገበ መሆኑ.፣<br>• የስጋት ስራ አመራር ስትራቴጂ ተቀርፆ በስራ ላይ መዋሉ፣<br>• የታክስ ጉዳይ ሀገራዊ አጀንዳ እንዲሆን ጥረት እየተደረገ መሆኑ፣<br>• ታክስ በትምህርት ስርዓት ዉስጥ እንዲካተት ጥረት መጀመሩ፣ | • የህግ ተገዥነትን ለማሳደግ የሚያስችል የታክስ ከፋዮች ትምህርት ስትራቴጂ ተቀርፆ ተግባራዊ አለመደረጉ፣<br>• በፈቃደኝነት ታክስ አስታውቆ የመክፈል ባህል ዝቅተኛ መሆኑ፣<br>• የታክስ ስወራ እና ማጭበርበር በመንሰራፋቱ በየዓመቱ ህገወጥ ኪሳራ፣ ባዶ እና ተመላሽ የሚያሳውቁ ግብር ከፋዮች ቁጥር እየጨመረ መምጣቱ፣<br>• ከባለድርሻ አካላት ጋር ያለው ቅንጅታዊ አሠራር ጠንካራ እና አስገዳጅ አለመሆኑ፣<br>• የኮንትሮባንድ መስፋፋት እና የመከላከል አቅም ደካማ መሆኑ፣<br>• የሚሰሩ የህግ ማስከበር ስራዎች ስጋት በመፍጠር የታክስና የጉምሩክ ማጭበርበርን መቀነስ አለመቻላቸዉ፣<br>• በህቡዕ ኢኮኖሚ የሚንቀሳቀሰዉ ሀብት |

| ስትራቴጂክ ጉዳዮች | ጥንካሬ (Strength) | ድክመት (Weakness) |
|---|---|---|
| | | ወደ ታክስ መረቡ ማስገባት አለመቻል፣ |
| ገቢ አሰባሰብ | • የገቢ አሰባሰቡን ማሻሻል የሚያስችሉ የህግ ማዕቀፎችና አሠራሮች ተዘጋጅተው መተግበራቸዉ ለገቢ አሰባሰቡ አስተዋፅዎ እያበረከቱ መምጣታቸዉ፣<br>• በየዓመቱ የሚሰበሰበው ገቢ በአንፃራዊነት እያደገ መምጣቱ፣<br>• የገቢ ፊዚካል ስራዎች አፈፃፀም መሻሻል እያሳያ መምጣቱ፣ | • ከኢኮኖሚ ዕድገቱ አኳያ ወደ ታክስ ስርዓቱ የሚገቡ አዳዲስ የታክስ ከፋዮች ቁጥር አነስተኛ መሆኑ፣<br>• ኢኮኖሚው ከሚያመነጨው እምቅ አቅም (Potential) አንፃር ሲታይ የሚሰበሰበዉ ገቢ ዝቅተኛ መሆኑ፣<br>• የቀረጥ ነፃ እና የታክስ ዕፎይታ መብት አጠቃቀም ላይ የሚደረገዉ ክትትል ደካማ መሆን፣<br>• ለበርካታ ዓመታት የጉምሩክ ቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ ማሻሻያ አለመደረጉ፣<br>• የታክስ ዕዳ ክምችትን በሚፈለገዉ ደረጃ ወደ ገቢ መቀየር አለመቻል፣ |

## 3.2 ውጫዊ ሁኔታዎች ዳሰሳ

| የመመዘኛ መስፈርት | መልካም አጋጣሚ (Opportunity) | ስጋት (Threat) |
|---|---|---|
| ፖለቲካዊ | • የፖለቲካ አመራሩ የታክስ እና የጉምሩክ አስተዳደሩን ለመደገፍ ቁርጠኛ መሆኑ፣<br>• የመንግስትና የግሉ ዘርፍ ተቀራርበው መስራት መጀመራቸው፣<br>• በዘላቂ ልማት ግቦች ታክስ ዓለም ዓቀፍ አጀንዳ መሆኑ፣<br>• የታክስ እና ጉምሩክ አስተዳደሩን ለማሻሻል የውጭ የቴክኒክ ትብብርና ድጋፍ እየጨመረ መምጣቱ፣<br>• ከጎረቤት ሀገራት ጋር የድንበር ላይ የንግድ እንቅስቃሴ በህጋዊ አግባብ ለመምራት ስምምነት | • በየደረጃዉ ያለዉ የፖለቲካ አመራር በሚፈለገዉ ደረጃ ኮንትሮባንድን እና ህገ-ወጥ ንግድን በቅንጅት መከላከል አለመቻል፣<br>• ሙስና በተቋሙና በሀገር ደረጃ በበቂ ሁኔታ መከላከል አለመቻሉ፣<br>• በተወሰኑ የጎረቤት ሀገሮች የፖለቲካ አለመረጋጋት መኖር፣<br>• ሀገሪቱ የምትፈራረማቸዉ አህጉራዊና እና ዓለም ዓቀፋዊ የንግድ ስምምነቶች ከአጭር ጊዜ አንፃር ተፅዕኖ የሚያሳድሩ መሆኑ፣ |

| የመመዘኛ መስፈርት | መልካም አጋጣሚ (Opportunity) | ስጋት (Threat) |
|---|---|---|
| | መፈረሙ፣<br>• ሀገራችን ከጎረቤት ሀገራት ጋር ያላት ግንኙነት እየተሻሻለ መምጣቱ፣<br>• መንግስት የዴሞክራሲ ምህዳር ለማስፋት አበረታች ጅምሮች መኖራቸዉ፣<br>• መንግስት ትላልቅ የልማት ድርጅቶችን ወደ ግል በማዞር ላይ መሆኑ፣ | |
| ኢኮኖሚዊ | • ቀጣይነት ያለው የኢኮኖሚ ዕድገት እየተመዘገበ መሆኑ፣<br>• ሀገራዊ የቁጠባ ባህላችን እያደገ መምጣቱ፣<br>• የግሉ ዘርፍ በሀገሪቱ ኢኮኖሚ ላይ ያለዉ ተሳትፎ እያደገ መምጣቱ፣<br>• የዉጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት እያደገ መምጣቱ፣<br>• የኢንዱስትሪ ፓርኮች፣ የደረቅ ወደቦች፣ የባቡር መሰረተ ልማት፣ የአየር ማረፊያዎች እና የሎጂስቲክስ አቅም እያደገ መምጣቱ፣<br>• በሀገር ደረጃ የአስር ዓመት መሪ የብልፅግና ፍኖተ ካርታ መዘጋጀቱ፣<br>• ኢንቨስትመንትን የሚያበረታቱ ፖሊሲዎች መኖራቸው፣<br>• የመሠረተ ልማት አውታሮች እየተስፋፉ መምጣታቸው፣ | • የንግድ ማጭበርበር እና ኮንትሮባንድ እየጨመረ መምጣት፣<br>• የዜጎች የነፍስ ወከፍ ገቢ ዝቅተኛ መሆን፣<br>• የዜጎች ምርታማነትና ሥራ የመፍጠር አቅም ዝቅተኛ መሆን፣<br>• የቀረጥ ነፃ እና የታክስ ዕፎይታ መብቶች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመሩ መምጣታቸዉ፣<br>• የግብይት ስርዓቱ ጥሬ ገንዘብ ላይ መሠረት ያደረገ መሆኑ፣<br>• የውጭ ምንዛሬ ማሸሽ እና የዋጋ ሽግግር /Transfer Pricing/ መኖር፣<br>• የህቡዕ ኢክኖሚ እየተስፋፉ መሄድ፣<br>• ያልተረጋጋ የዋጋ ንረት መኖር፣<br>• የውጭ ምንዛሬ እጥረት ያልተፈታ መሆኑ፣<br>• የሎጂስቲክስ ወጪ እየጨመረ መምጣቱ፣ |
| ማህበራዊ | • የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መስፋፋት፣<br>• የታክስ ወንጀሎች እና | • በፈቃደኝነት ቀረጥና ታክስ አሳውቆ የመክፈል ባህል ያልዳበረ መሆኑ፣<br>• ደረሰኝ የመስጠትና የመቀበል ባህል |

| የመመዘኛ መስፈርት | መልካም አጋጣሚ (Opportunity) | ስጋት (Threat) |
|---|---|---|
| | ኮንትሮባንድ ላይ ከህብረተሰቡ የሚሰጥ ጥቆማ እና ተባባሪነት እያደገ መምጣቱ፣<br>• የብዙሀን መገናኛ እየተስፋፉ መምጣታቸው እና በጋራ ለመስራት ያለው ዝግጁነት እየተሻሻለ መምጣት፣<br>• ከከተሞች መስፋፋት ጋር ተያይዞ የአገልግሎት ዘርፉ እያደገ መምጣቱ፣ | አለመጎልበት፣<br>• በህብረተሰቡ ዉስጥ የሙስና አመለካከትና ተግባር በሚፈለገው ደረጃ አለመቀረፉ፣<br>• የኮረና ቫይረስ ወረርሽን በኢኮኖሚዉ እና በታክስ ገቢዉ ላይ አሉታዊ ጫና ማሳደሩ፣ |
| ቴክኖሎጂያዊ | • የመረጃ ቴክኖሎጂ ደህንነት ለመጠበቅ የሚያስችል ተቋም መቋቋሙና ድጋፍ ማድረግ መቻሉ፣<br>• በሀገር ዓቀፍ ደረጃ የመረጃ ቴክኖሎጂ መሰረተ ልማት እና ዓይነት መስፋፋቱ፣<br>• ሀገር ዓቀፍ የዲጂታል ትራንስፎርሜሽን ስራ መጀመሩ፣<br>• የታክስ እና ጉምሩክ አስተዳደርን ለማዘመን ከመንግስት በኩል ድጋፍ መኖሩ፣<br>• የቴሌኮም ሴክተሩን ተወዳዳሪነት ለማሳደግ ለግል ባለሀብቱ ክፍት መደረጉ፣<br>• የኢ-ኮሜርስ ህግ በስራ ላይ መዋሉ፣ | • የቴሌኮም ኔትዎርክና የኤሌክትሪክ ተደራሽ አለመሆን እና አገልግሎት መቆራረጥ፣<br>• የሳይበር ጥቃት ስጋት መኖር፣<br>• የቴክኖሎጂዎች እርስ በእርስ መናበብ አለመቻል፣<br>• የቴክኖሎጂ ፕሮጀክቶችን የማስተዳደር አቅም አለመጎልበት፣ |
| ከባቢያዊ | • የአየር ንብረት ለውጥ የሚያስከትለውን ተፅዕኖ ለመከላከል ሀገራዊ የአረንጓዴ ልማት ስትራቴጂ ተቀርጾ ተግባራዊ መደረጉ፣ | • የአየር ንብረት ለውጥ በኢኮኖሚው ላይ ተፅዕኖ የሚፈጥር መሆኑ፣<br>• በጠረፋማ አካባቢዎች የበረሀማነት መስፋፋት በኮንትሮባንድ መከላከሉ ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድር መሆኑ፣ |

| የመመዘኛ መስፈርት | መልካም አጋጣሚ (Opportunity) | ስጋት (Threat) |
|---|---|---|
| ህጋዊ ማዕቀፍ | • ህግን ለማስከበር፣ ኢንቨስትመንትን ለማሳለጥ እና ገቢ አሰባሰቡን ለማሻሻል የሚያስችሉ ቀጣይነት ያላቸው የህግ ማሻሻያዎች እየተደረጉ መሆኑ፣<br>• በሀገሪቱ ግልፅና ወጥ የሆነ የሂሳብ መዝገብ አያያዝ ስርዓት መዘርጋቱ፣ | • የተለያዩ የህግ ማዕቀፎች አለመናበብ እና ተቋማትን በቅንጅት የሚያሰራ የህግ ማዕቀፍ አለመኖር፣<br>• በፍ/ቤቶች የታክስ ጉዳዮችን የማየት ሂደት ፈጣን ያለመሆን፣ |

## 3.3 ፈታኝ እና አስቻይ ሁኔታዎች

ሰንጠረዥ 4፡ ፈታኝ እና አስቻይ ሁኔታዎች

| ፈታኝ ሁኔታዎች | አስቻይ ሁኔታዎች |
|---|---|
| • በየርከኑ ያለው አመራር ከማቀድ፣ ወደ ፈፃሚ ከማዉረድ፣ ተቀናጅቶ ከመስራት፣ ክትትል እና ድጋፍ ከማድረግ አንፃር ክፍተት መኖሩ፣<br>• ብቃት ያለው የሰው ኃይል ለመሳብ እና ለማቆየት የሚያስችል ስትራቴጂ ቀርፆ መተግበር አለመቻል፣<br>• የመረጃ ምንጭ የመለየት፣ የመሰብሰብ፣ የማደራጀት፣ የመተንተን፣ የማጠናቀር፣ የማሰራጨት እና የመጠቀም ክፍተት መኖር፣<br>• የአሰራር ስርዓቶች በተሟላ ሁኔታ በመረጃ ቴክኖሎጂ አለመደገፍ እና ደህንነታቸዉ በአስተማማኝ ሁኔታ ያልተጠበቀ መሆን፣<br>• የተዘረጉ የአሰራር ስርዓቶች በየጊዜው ውጤታማነታቸው እየተፈተሸ ማሻሻያ የማይደረግላቸዉ መሆኑ፣<br>• የተገልጋዩ የህግ ተገዥነት ደረጃ ዝቅተኛ መሆን፣<br>• ተገልጋዮችን በሚፈለገዉ ደረጃ ማርካት አለመቻል፣ | • በየጊዜዉ በሚሰጡ ስልጠናዎች የመፈፀም አቅም እያደገ መምጣቱ፣<br>• የተደራጀ መሠረተ ሰፊ የትራንስፎርሜሽን ፕሮግራም እየተተገበረ መሆኑ<br>• የታክስ ጉዳይ ሀገራዊ አጀንዳ እንዲሆን ማድረግ መቻሉ፣<br>• የሀገር ውስጥ ታክስ እና የጉምሩክ አዋጆች፣ ደንቦች ፣ መመሪያዎችና አሰራሮች ተቀርፀዉ መተግበራቸዉ፣<br>• ተቋማዊ የአደረጃጀት ለውጥ መደረግ መቻሉ፣<br>• የላቀ አፈፃፀም ላስመዘገቡ ሰራተኞችና ታክስ ከፋዮች ዕውቅና መሰጠቱ፣<br>• የታክስ ስርዓቱን ዉጤታማ ለማድረግ የመንግስት ልዩ ድጋፍ መኖሩ፣<br>• ከጎረቤት ሀገራት እና ዓለም ዓቀፍ ተቋማት ጋር ተባብሮ ለመስራት የሚያስችሉ የጋራ ሥምምነቶች መፈጠራቸዉ፣<br>• የታክስ ስርዓቱን ለማዘመን የልማት አጋሮች |

| | |
|---|---|
| • የታክስ ስወራን፣ የቀረጥና ታክስ ማጭበርበርን እና ኮንትሮባንድን መቆጣጠር አለመቻል፣<br>• የኮንትሮባንድ መከላከል ስራ የህይወት መስዋትነትን ጭምር እየጠየቀ መምጣቱ፣<br>• ከባለድርሻ እና አጋር አካላት ጋር ያለዉ ቅንጅታዊ አሰራር ዉጤታማ አለመሆን፣<br>• የተቋሙ የገቢ አሰባሰብ አፈፃፀም ዝቅተኛ መሆኑ፣<br>• የግብር ከፋዩን እና አስከፋዩን የስነ-ምግባር ጉድለቶች በወሳኝ መልኩ መቅረፍ አለመቻሉ፣<br>• የውጭ ምንዛሬ እጥረት አለመቀረፉ፣<br>• የህቡዕ ኢኮኖሚው እየተስፋፋ መሄድ፣<br>• የኔትወርክ መቆራረጥ እና የኤሌክትሪክ አቅርቦት አስተማማኝ አለመሆን፣<br>• መሰረተ ልማት በጠረፍ አካባቢ የተሟላ አለመሆኑ፣<br>• የኮረና ቫይረስ ወረርሽኝ በኢኮኖሚ ፣ በንግድ ስርአቱ እና በታክስ አስተዳደሩ የስራ እንቅስቃሴ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ማሳደሩ፣ | ድጋፍ እየተጠናከረ መምጣቱ፣<br>• የደረቅ ወደቦች መስፋፋት እና የሎጂስቲክ አቅም እያደገ መምጣቱ<br>• በሀገሪቱ ዓለም ዓቀፍ የሂሳብ መዝገብ አያያዝ ሥርዓት (IFRS) መተግበር መጀመሩ፣<br>• ቀጣይነት ያለው የኢኮኖሚ ዕድገት እየተመዘገበ መሆኑ፣<br>• የስጋት ስራ አመራር ስርዓት መተግበር መጀመሩ፣<br>• የንግድ ስራ አመቺነትን ለማስፈን የሚያስችሉ ስራዎች በሀገር አቀፍ ደረጃ መተግበራቸዉ፣<br>• የመንግስት ተቆጣጣሪ አካላት የቅርብ ክትትልና ድጋፍ መኖሩ፣ |

## 3.4 ዋና ዋና ተግዳሮቶች እና የመፍትሄ ሀሳቦች

### 3.4.1 ዋና ዋና ተግዳሮቶች

ከላይ ለማቅረብ እንደተሞከረዉ ባለፉት ዓመታት በተቋሙ የአፈፃፀም ግምገማ የታዩ ጥንካሬዎች፣ ድክመቶች፣ ስጋቶች እና መልካም አጋጣሚዎች በዝርዝር ተገምግመዉ የተለዩ ቁልፍ ችግሮች እና አስቻይ ሁኔታዎች ተመልክተዋል:: ከዚህ በመነሳት ባለፉት የስትራቴጂክ የእቅድ አመታት ተቋሙ ተልዕኮዉን በተሟላ መልኩ እንዳያሳካ ማነቆ የነበሩና በቀጣይ ስትራቴጂክ ዘመናት በወሳኝ መልኩ ማነቆዎቹን ለመፍታት ትኩረት ሰጥቶ የሚሰራባቸዉ ዋና ዋና ተግዳሮቶችና መገለጫዎቻቸዉ ከዚህ እንደሚከተለዉ ቀርበዋል::

ሰንጠረዥ 5፡ ዋና ዋና ተግዳሮቶች

| ተግዳሮቶች | መገለጫዎች |
|---|---|
| ዝቅተኛ የገቢ አፈፃፀም | • በ2012 የታክስ-ሀገራዊ ምርት ጥምርታ ከባለፉት ዓመታት እየቀነሰ መጥቶ በ2012 9.2% መድረሱ እና ከሰሀራ በታች ካሉ የአፍሪካ ሀገራትም አንፃር |

| ተግዳሮቶች | መገለጫዎች |
|---|---|
| | ዝቅተኛ መሆኑ፣<br>• በመንግስት የሚሰጡ ማበረታቻዎች እና የታክስ ዕፎይታ በከፍተኛ ሁኔታ ማደጋቸው (6% የሚሆነው ከዓመታዊ የሀገሪቱ ምርት በቀረጥ ነፃ፣ ታክስ ዕፎይታ እና ታክስ ስወራ የሚታጣ መሆኑ[1]) |
| ዝቅተኛ የታክስ ህግ ተገዢነት | • የታክስ ስወራ እና ማጭበርበር ማደጉ፣<br>• በየዓመቱ ኪሳራ፣ ባዶ እና ተመሳሽ የሚያሳውቁ ግብር ከፋዮች ቁጥር መጨመሩ፣<br>• ህቡዕ ኢኮኖሚው ከሀገሪቷ ምርት ወደ 40% ያህሉን የሚሸፍን መሆኑ[2]፣<br>• ከባለድርሻ አካላት ጋር ቅንጅታዊ አሠራሩ ጠንካራ እና አስገዳጅ አለመሆኑ፣<br>• የታክስ ህግ የማስከበር አቅም ውስንነት ያለበት መሆኑ፣<br>• የታክስ ትምህርት የህግ ተገዢነት ባህሪን ማረጋገጥ አለመቻሉ፣<br>• ደረሰኝ የመስጠት እና የመጠየቅ ባህል አለመዳበሩ፣<br>• የኢንተለጀንስ ስራዎች በሚፈለገዉ ደረጃ ዉጤታማ አለመሆኑ፣<br>• የኮንትሮባንድ መስፋፋትን የመከላከል አቅም በሚፈለገዉ ደረጃ አለመገንባቱ፣ |
| የታክስ መሠረቱ አለመስፋት | • አዳዲስ የታክስ ዓይነቶች ወደ ታክስ ስርዓቱ አለመግባታቸው፣<br>• ከኢኮኖሚ ዕድገቱ አኳያ ወደ ታክስ ስርዓቱ የሚገቡ አዳዲስ የታክስ ከፋዮች ቁጥር አነስተኛ መሆን፣<br>• የንግድ ትርፋማነት ምጣኔ ማስተካከያ ወቅታዊ አለመደረጉ፣ |
| የመረጃ ቴክኖሎጂ ውስንነት | • የሀገር ውስጥ ታክስ መረጃ ቴክኖሎጂ ስርዓት ወቅታዊ አለመሆኑ፣<br>• የመረጃ ቴክኖሎጂ ስርዓቶቻችን የተቀናጁ እና የተናበቡ አለመሆን፣<br>• የመረጃ ቴክኖሎጂ መሠረተ ልማት አስተማማኝ አለመሆን፣<br>• የመረጃ ቴክኖሎጂ አጠቃቀም ዝቅተኛ መሆን፣<br>• የጉምሩክ መረጃ ቴክኖሎጂዎች በአግባቡ ጥቅም ላይ አለመዋላቸው፣ |
| የመፈፀም ብቃት ማነስ እና አርኪ አገልግሎት አለመስጠት | • የሰዉ ሀብት ብቃት ማነስ፣<br>• የውሳኔ ሰጪነት አቅም እጥረት ያለበት መሆኑ፣<br>• የስነ-ምግባር መጓደል፣<br>• ፈጣን እና ቀልጣፋ አገልግሎት መስጠት አለመቻል፣<br>• የተገልጋይ ዕርካታ አለመረጋገጥ፣ |

[1] Illicit Financial Flows Report of the High-Level Panel on Illicity Financial Flows from Africa, ECA

[2] Shadow Economies Around the World: What Did We Learn Over the Last 20 Years? IMF Working Paper 18/17

| ተግዳሮቶች | መገለጫዎች |
|---|---|
| | • የስራ እና የአገልጋይነት ባህል አለመዳበር፣<br>• ከተቆጣጣሪ እና አጋር አካላት ጋር ያለው ቅንጅታዊ አሰራር ዝቅተኛ መሆን፣ |

### 3.4.2 የመፍትሄ ሀሳቦች

ሰንጠረዥ 6፡ ተግዳሮቶቹን ለመቅረፍ የቀረቡ የመፍትሄ ሀሳቦች

| የመፍትሄ አመላካቾች | የመፍትሄ ሀሳቦች |
|---|---|
| ሰው ሀብት | • የሰው ሀብት ስራ አመራር ስትራቴጂ መቅረፅና መተግበር፣<br>• የመፈፀምና የማስፈፀም አቅም መገንባት፣<br>• የስነ-ምግባር ስትራቴጂን መተግበር፣ |
| አሠራር ስርዓት | • አሠራሮችን ግልፅ፣ ቀላል ፣ተገማች እና ተደራሽ ማድረግ፣<br>• የህግ ማዕቀፎችን ቀጣይነት ባላዉ መልኩ ማሻሻያ ማድረግ፣<br>• የክትትል፣ ድጋፍና ሱፐርቪዥን ስርዓት መዘርጋት እና መተግበር፣<br>• የገቢ ሪፎርም ስራዎችን መቅረፅና መተግበር፣ |
| መረጃ እና ቴክኖሎጂ | • የመረጃ ቴክኖሎጂ ስትራቴጂ መቅረፅና መተግበር፣<br>• አሰራሮችን በዘመናዊ የመረጃ ቴክኖሎጂ ማስደገፍ፣<br>• ከባለድርሻ አካላት ጋር የመረጃ ቴክኖሎጂ ትስስር መፍጠር፣<br>• የመረጃ ቴክኖሎጂ ደህንነትን ማረጋገጥ፣<br>• የመረጃ ቴክኖሎጂ አጠቃቀምን ማሳደግ፣ |
| የባለድርሻ አካላት ትብብር | • የአጋር አካላት የቅንጅት ስትራቴጂ ቀርፆ መተግበር፣<br>• በገቢ ዘርፍ የክልልና የከተማ አስተዳደሮች የድጋፍ ስትራቴጂ በመቅረፅ መተግበር፣ |
| ህግ ተገዢነት | • የታክስ ጉዳይ ሀገራዊ አጀንዳ እንዲሆን ማድረግ፣<br>• የህግ ተገዥነትን በማስተማር ማሳደግ፣<br>• በአጥፊዎች ላይ አስተማሪ የሆነ የህግ ዕርምጃ መውሰድ፣<br>• ታክስ በትምህርት ስርዓት ዉስጥ እንዲካተት ማድረግ፣<br>• የኮንትሮባንድ እና ህገ-ወጥ ንግድ መከላከልን በቴክኖሎጂ መደገፍ፣ |
| ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች | • የታክስ መሠረቱን ለማስፋት የፖሊሲ ማሻሻያ ምክረ-ሀሳብ ማመንጨት፣<br>• ኢኮኖሚው የሚያመነጨውን ገቢ በብቃት መሰብሰብ፣<br>• ግብይት በባንክ ስርዓት እንዲመራ ማድረግ፣<br>• ንግድና ኢንቨስትመንት እንዲሳለጥ መደገፍ፣<br>• የኮሮና ቫይረስ ወረርሽኝ ቀጣይነት የሚኖረው ከሆነ የስራ ቦታዎችን ምቹ በማድረግ ፣ የቴክኖሎጂ ሁኔታዎችን በማሻሻል እና ከነባራዊ ሁኔታ ጋር |

| የመፍትሄ አመላካቾች | የመፍትሄ ሀሳቦች |
|---|---|
| | የተጣጣመ አመራር በመስጠት እና እንዳስፈላጊነቱ የፖሊሲ እርምጃዎች እንዲወሰድ በማድረግ መከላከል ይጠበቃል |

# 4 የተቋሙ የአምስት ዓመት ስትራቴጂክ ዕቅድ

ከሀገራዊ ስትራቴጂክ ዕቅድ ማዕቀፍ እና ራዕይ በመዉሰድ ተቋሙ የሚመራበት የአስር ዓመት ተሻጋሪ እቅድ የተዘጋጀ ሲሆን ይህን የረዥም ጊዜ እቅድ መሰረት በማድረግ የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የአምስት ዓመት ወይም የመካከለኛ ጊዜ እቅድ ተዘጋጅቷል፡፡ ይህ የአምስት ዓመት እቅድ በረዥም ጊዜ መሪ እቅድ ዉስጥ የተያዙትን ስትራቴጂካዊ ጉዳዮች ለማሳካት በሚያስችል መልኩ በመካከለኛ የጊዜ ማዕቀፍ ዉስጥ መተግበር የሚገባቸዉንና ለረዥም ጊዜ እቅድ ፈር ቀዳጅ በመሆን የሚያገለግል ይሆናል፡፡ በመሆኑም በዚህ ክፍል ተቋማዊ ርዕይ፣ ተልዕኮ፣ ዕሴቶች፣ የትኩረት መስኮች፣ የትኩረት መስኮቹን ለማሳካት የሚያስችሉ ዓላማዎች፣ መለኪያዎች እና የማስፈፀሚያ ስትራቴጂክ እርምጃዎች ተቀርፀዋል፡፡

## 4.1 የተጠቃለለ ተቋማዊ ርዕይ፣ ተልዕኮ፣ ዕሴቶች፣ የትኩረት መስኮች እና ዓላማዎች

ሰንጠረዥ 7፡ የተጠቃለለ ርዕይ፣ ተልዕኮ፣ ዕሴቶች፣ የትኩረት መስኮች እና ዓላማዎች

| ርዕይ | በ2022 ዘመናዊ የታክስ አስተዳደር ተገንብቶ ሀገራዊ ወጪ በታክስ ገቢ ተሸፍኖ ማየት | |
|---|---|---|
| **ስትራቴጂያዊ የትኩረት መስኮች** | **ተልዕኮ** | **ዕሴቶች** |
| 1 ቀጣይነት ያለው ተቋማዊ አቅም ልማት<br>2 የአሠራር ልህቀት<br>3 ስትራቴጂያዊ አጋርነት ልህቀት<br>4 የህግ ተገዢነት አመራር ልህቀት<br>5 ዘላቂ የገቢ ዕድገት | ብቃት ያለው የሰው ኃይል በማፍራት ፣ ዘመናዊ ቴክኖሎጂ በመጠቀም ፣ ፍትሀዊ የታክስ ስርዓት በመገንባት ፣ ታክስን በፍቃደኝነት የመክፈል ባህልን በማዳበር ኢኮኖሚው የሚያመነጨውን ገቢ መሰብሰብ | 1 አገልጋይነት<br>2 መሰጠት<br>3 ሙያዊ ብቃት<br>4 ታማኝነት<br>5 በቡድን መስራት |
| ትኩረት መስክ 1፡ **ቀጣይነት ያለው ተቋማዊ አቅም ልማት** | | |
| • የሰዉ ኃይል መሳብ፣ ማቆየትና የመፈፀም ብቃትን ማሳደግ<br>• የመረጃ ቴክኖሎጂ ሀብት | • የሀብት አጠቃቀም ውጤታማነትን ማሳደግ<br>• የባለብዙ ዘርፍ አካታችነትና ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ | • ተቋማዊ የስጋት ስራ አመራርን ማጠናከር |

| | | |
|---|---|---|
| እና አጠቃቀምን ማዘመን | | |
| ትኩረት መስክ 2: **የአሠራር ልህቀት** | | ረት መስክ 3: **ስትራቴጂያዊ አጋርነት ልህቀት** |
| • የአገልግሎት አሰጣጥ አፈፃፀምን ማሻሻል<br>• የመረጃ አስተዳደር አፈፃፀምን ማሻሻል | • የአሰራር ስርዓት አፈፃፀምን ማሻሻል<br>• የተጣጣመ ሀገራዊ የታክስ አስተዳደርን ማስፈን | • የሀገር ውስጥ አጋር አካላት አጋርነትና ትብብር ማሻሻል<br>• የውጭ ሀገራትና ድርጅቶች አጋርነትና ትብብርን ማሻሻል |
| ትኩረት መስክ 4: **የህግ ተገዢነት አመራር ልህቀት** | | ትኩረት መስክ 5: **ዘላቂ የገቢ ዕድገት** |
| • የስጋት ስራ አመራር አፈፃፀምን ማሻሻል<br>• የታክስ ማጭበርበር እና ኮንትሮባንድ መከላከል አፈፃፀምን ማሻሻል | • የታክስ ህግ ተገዥነት አፈፃፀምን ማሻሻል | • የገቢ አሰባሰብ ውጤታማነትን ማሻሻል |

## 4.2 የተቋሙ ስትራቴጂካዊ አቅጣጫዎች

የሚኒስቴር መ/ቤቱ በመካከለኛ የዕቅድ ዘመን ቀደም ሲል በአስር ዓመት የስትራቴጂክ ዕቅድ ዘመን የቀረፀውን ርዕይ ለማሳካት የሚያስችሉ አምስት ዋና ዋና ስትራቴጂክ አቅጣጫዎች የተለዩ ሲሆን እነኝህን ስትራቴጂክ አቅጣጫዎች በመካከለኛ የስትራቴጂክ ዕቅድ ዘመን በመጠቀም እና መሰረት በማድረግ በአስር ዓመት ለመድረስ የተቀመጠዉን የተቋሙን ርዕይ ለማሳካት በነዚህ ጉዳዮች ላይ ትኩረት በመስጠት የሚሰራ ይሆናል፡፡ የተለዩትም ስትራቴጂክ አቅጣጫዎች እንደሚከተለዉ ቀርበዋል፦

### 4.2.1 ታክስ በፈቃደኝነት የመክፈል ባህል የማሳደግ አቅጣጫ

የዚህ ስትራቴጂያዊ የትኩረት አቅጣጫ ግብ ታክስ በፈቃደኝነት የመክፈል ባህልን ማዳበር ሲሆን ይህንንም ለማሳካት የታክስ ስርዓቱን ለግብር ከፋዩ ግልጽ የማድረግ ሥራን፣ የግብር ክፍያ ስርዓትን በማዘመን ቀላልና ጊዜ ቆጣቢ አገልግሎት መሥጠት፣ የግብር ከፋዩን ታክስና ቀረጥ ላይ ያለዉን ግንዛቤ የመጨመር ስራ መስራት እና የህግ ተገዥነት ስትራቴጂ በመቅረጽ መተግበርን የሚያጠቃልል ነዉ፡፡ ስትራቴጂዉ ታሳቢ ያደረገዉ ታክስ ከፋዩን በልዩ ልዩ የግንኙነት አግባቦች በማስተማር፣ በመደገፍ እና እዉቅና በመስጠት አብዛኛዉ ግብር ከፋይ በፈቃደኝነት የታክስ ግዴታውን እንዲወጣ ማስቻል ሲሆን የታክስ ህግ ተገዥነት ባህሪ ለዉጥ

ማምጣት ባልቻሉ አካላት ላይ ተመጣጣኝ የህግ ማስከበር ተግባር ተፈፃሚ የሚደረግበት ነዉ፡፡ ስለሆነም በቀጣይ አምስት ዓመታት ታክስ በፈቃደኝነት የመክፈል ባህል እንዲጨምር ከላይ በተጠቀሱት ጉዳዮች ላይ ትኩረት ተደርጎ የሚሰራ ይሆናል ፡፡

### 4.2.2 ዲጂታል የገቢ አስተዳደር ስርዓትን የመገንባት አቅጣጫ

የዲጂታል የገቢ አስተዳደር ስርዓት የመገንባት አቅጣጫ ታሳቢ የሚያደርገዉ አጠቃላይ የታክስ እና የጉምሩክ አስተዳደር ስርዓቱን ዓለም በደረሰበት የመረጃ ቴክኖሎጂ ስርዓት እንዲደገፍ ማድረግን ሲሆን ይህ የዲጂታል የገቢ አስተዳደር ስርዓት ለአገልግሎት ተቀባዩ ግልጽ፣ ቀላል እና ተደራሽ አገልግሎት በመስጠት፣ የህግ ተገዥነትና አስተዳደራዊ ወጪ በመቀነስ እና የተገልጋዩን ዕርካታ በላቀ ደረጃ በማረጋገጥ የተቋሙን ተልዕኮ ማሳካት ነዉ፡፡ በመሆኑም በቀጣይ አምስት የመካከለኛ እቅድ ዘመን የገቢ አሰባሰቡን ሂደት ዲጅታል በማድረግ ግብር ከፋዩ ባለበት ቦታ ሆኖ የታክስ እና የቀረጥ ግዴታዉን በኤሌክትሮኒክ መንገድ አሳዉቆ እንዲከፍል የማድረግ ስራ በመስራት የግብር ስርዓቱን የማዘመን ስራ የሚሰራ ይሆናል፡፡

### 4.2.3 የታክስና የጉምሩክ አስተዳደር ፍትሃዊነትን የማረጋገጥ አቅጣጫ

የሀገራችን የታክስ አስተዳደር ስርዓት በኢመደበኛ ኢኮኖሚ፣ በህገ ወጥ ንግድ፣ በታክስ ማጭበርበር እና በኮንትሮባንድ ምክንያት ከሀገሪቱ ኢኮኖሚ መሰብሰብ ያለበትን የታክስና ቀረጥ ገቢ ለመሰብሰብ ካለማስቻሉም ባሻገር የንግዱ ማህበረሰብ በእኩልነት ተወዳዳሪ እንዲሆን ያላስቻለ ሲሆን ይህም በሀገሪቱ ያለዉን የሀብት ክፍፍል ኢ-ፍትሀዊ አድርጎታል፡፡ ስለሆነም በሀገሪቱ የሚታየዉን ያልተማከለ የንግድ ስርዓት ከባለድርሻ አካላት ጋር በጋራ በመስራት ወደ ትክክለኛ የንግድና ታክስ ስርዓት እንዲመጡ ማድረግ፣ የታክስ ህጎችን በሁሉም ታክስ ከፋዮች በእኩል ደረጃ ተፈፃሚ በማድረግ የታክስ ፍትሃዊነትንና የእኩል የሃብት ተጠቃሚነትን የማረጋገጥ ስርዓትን ታሳቢ ያደረገ አቅጣጫ ነዉ፡፡

### 4.2.4 የውስጥ እና የውጭ ስትራቴጂክ አጋርነትን የማጠናከር አቅጣጫ

የታክስና የጉምሩክ አስተዳደር ዉጤታማነትን ለማረጋገጥ ከአጋር እና ባለድርሻ አካላት ጋር ተቀናጅቶ ለአንድ ዓላማ በጋራ መንቀሳቀስን ይጠይቃል፡፡ በመሆኑም ይህ አቅጣጫ የቴክኒክ፣

የእዉቀት ሽግግር፣ የመረጃ ልዉዉጥ፣ ህገ ወጥነትን የመከላከል አሰራር መዘርጋትን ታሳቢ ያደረገ ነዉ። በዚህ መሰረት አጋር አካላትን መለየት፣ ግንኙነት እና ስምምነት መፍጠር እና በስምምነቱ መሰረት ለመፈፀም ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮችንና ማነቆዎችን በጋራ ለይቶ በመፍታት ተጠቃሚነትን ማረጋገጥን ታሳቢ ያደረገ ነዉ።

### 4.2.5 የዳበረ የስራ ባህል የማምጣት አቅጣጫ

የታክስ ስርዓቱን ዉጤታማ ለማድረግ የተቋሙን ርዕይ፣ ተልዕኮ እና ዕሴቶችን የተላበሰ እና ሁለንተናዊ አቅሙን በመገንባት የዳበረ የስራ ባህል ያለዉ የሰዉ ኃይል ማፍራትን ታሳቢ ያደረገ ነዉ። ይህ አቅጣጫ የሰው ኃይል ስራ አመራር ልማት ስትራቴጂ ከመቅረፅ ጀምሮ፣ ብቃት ያለዉ የሰዉ ኃይል መሳብና ማቆየት፣ የምዘና፣ የማትጊያ እና የተጠያቂነት ስርዓት መዘርጋትና መተግበር፣ ምቹ የስራ ከባቢ መፍጠር፣ ታማኝና ለስራ ተነሳሽ የሆነ አመራር እና ፈፃሚ ማፍራትን የሚያጠቃልል ነዉ።

## 4.3 ስትራቴጂያዊ የትኩረት መስኮች እና ዓላማዎች

ተቋሙ የሚመራባቸዉ የትኩረት መስኮቹን ለመለየት የመንግስት የትኩረት አቅጣጫ፣ ያለፉትን ሁለት የስትራቴጂክ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዶች አፈፃፀም ግምገማ እና የውስጣዊና ውጫዊ ሁኔታዎች ዳሰሳ እንደመነሻ ተወስደዋል። ከዚህ አኳያ የሚከተሉት አምስት የትኩረት መስኮች ተለይተዋል።

- ቀጣይነት ያለው ተቋማዊ አቅም ልማት
- የአሠራር ልህቀት
- ስትራቴጂያዊ አጋርነት ልህቀት
- የህግ ተገዢነት አመራር ልህቀት
- ዘላቂ የገቢ ዕድገት

### 4.3.1 ቀጣይነት ያለው ተቋማዊ አቅም ልማት

ይህ የትኩረት መስክ ቀጣይነት ያለዉ ተቋማዊ አቅም ለመገንባት የሚያስችሉ ግቦችን ያካተተ ሲሆን በስሩ የሰዉ ሀብት መሳብ፣ ማቆየት እና ብቃት ማሳደግን፣ የመረጃ ቴክኖሎጂ አቅርቦት እና አጠቃቀም ማዘመንን፣ የሀብት አጠቃቀም እና ውጤታማነት ማረጋገጥን፣ ተቋማዊ ስጋት

ስራ አመራር ማጠናከርን እና የባለብዙ ዘርፍ አካታችነትና ተጠቃሚነት ማረጋገጥን የሚያጠቃልል ነው።

## ዓላማ 1. የሰዉ ኃይል መሳብ፣ ማቆየትና የመፈፀም ብቃትን ማሳደግ

### መግለጫ

የሰዉ ኃይል መሳብ፣ ማቆየትና የመፈፀም ብቃትን ማሳደግ ማለት ተቋሙ ሁለንተናዊ አቅሙ የተገነባ አመራርና ፈፃሚ በመፍጠር የተቋሙን ምርታማነት ማሻሻል ነዉ።

### ዓላማውን ለማስፈፀም የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት

የሰዉ ኃይል ልማት ስትራቴጂ መቅረፅ፣ የተቋሙን ርዕይና ተልዕኮ የተረዳ እና ዕሴት የተላበሰ አመራርና ፈፃሚ ማፍራት፣ የአመራር እና የፈፃሚውን ክህሎት ማሳደግን፣ የሰራተኛ ደህንነትና ጤንነት ማረጋገጥ ፣ ዉጤታማ የምዘና ስርዓት መተግበር ፣ የጠራ የሰራተኛ መረጃ ስርዓት ማደራጀትንና በቴክኖሎጂ ማስደገፍን፣ ምቹ የስራ ከባቢ መፍጠርን፣ የማትጊያ ስርዓት ተግባራዊ ማድረግ፣ የሰው ኃይል መሳብና ማቆየትን እንዲሁም የስራ ተነሳሽነት በማሳደግ እና ዕርካታዉን በማረጋገጥ ምርታማነቱን ማሳደግን ያጠቃልላል።

### ውጤት፡- የረካ ሰራተኛ፤ ምርታማነቱ ያደገ ሰራተኛ

## ዓላማ 2. የመረጃ ቴክኖሎጂ ሀብት እና አጠቃቀምን ማዘመን

### መግለጫ

የመረጃ ቴክኖሎጂ ሀብት እና አጠቃቀምን ማዘመን ማለት ለአገልግሎት አሰጣጥ፣ ለህግ ማስከበር ስራዎች፣ ለገቢ አሰባሰቡ ዉጤታማነት እና ሌሎች የተቋሙን የአሠራር ስርዓቶች የሚደግፉ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን የመግዛት፣ የማልማት፣ የማስተዳደር፣ የመጠቀም እና የማሻሻል ስራዎችን የሚያካትት ነዉ።

### ዓላማውን ለማስፈፀም የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት

የዳታ ማዕከል (Data Center) መገንባት፣ የመጠባበቂያ ዳታ ማዕከል (Disaster Recovery Data Center) መገንባት፣ የመረጃ ደህንነትን (IT Security) ማረጋገጥ፣ የመረጃ መሰብሰቢያና ማደራጃ ሶፍትዌሮችን ማልማት፣ የመረጃ ቋት (Data Base) ማበልፀግ እና ማሰራጨትን፣ በስራ ላይ ያለዉ የሲግታስ (SIGTAS) ስርዓት በአዲስ የዲጂታል (Digital System ) ስርዓት

መተካት፣ የኦንላይን አገልግሎት (Online service ) ማቅረብ፣ የተከፋፈሉ ስርዓቶችን (Sub Systems) በኢንተርፌስ እንዲቀናጁ ማድረግ፣ ግብር ከፋዩ በቀጥታ የሚያቀርባቸውን የአገልግሎት ጥያቄዎች ለመመለስ የሚያስችሉ የመተግበሪያ ሶፍትዌሮች ማልማትንና መጠቀም፣ በስራ ቦታ እንደ ሲሲቲቪ ካሜራና ሌሎች የቴክኖሎጂ የመቆጣጠሪያ መንገዶችን ተግባራዊ ማድረግ፣ ተገልጋዩ ጉዳዩ የደረሰበትን ደረጃ እንዲያውቅ የአገልግሎት ደረጃ ማሳወቂያ (Service Level Tracking) ሶፍትዌርን ማልማት፣ በቴክኖሎጂ የተደገፉ የመረጃ መለዋወጫ ኪዮስኮች (Customer Interaction Kiosks) ማደራጀት፣ የመረጃ አቅርቦት ማዕከላትን (Contact Center) ማደራጀት፣ አጠቃላይ ቅሬታ፣ የታክስና የጉምሩክ አቤቱታ ጥያቄዎችን ምላሽ አሰጣጥ በቴክኖሎጂ ማስደገፍ፣ ያሉትን የጉምሩክና የታክስ ስርዓቶች ማስተሳሰር (Interface)፣ የካርጎ ስካኒንግ፣ የካርጎ ትራኪንግ፣ የጉምሩክ ስራ አመራር ስርዓት(ECMS)፣ የአንድ መስኮት አገልግሎት(ESW)፣ የጉምሩክ ዋጋ ዳታቤዝ ሲስተምን ማሻሻል፣ የትልልቅ መረጃዎችን ትንተና(Big Data Analysis) ስርዓት መዘርጋት፣ ከአጋር አካላት ጋር የሚኖረዉን ግንኙነት ማስተሳሰርና የተቋሙን የመረጃ ቴክኖሎጂ አጋር አካላት ከሚጠቀሙበት ቴክኖሎጂ ጋር ማናበብን እና የተቋሙን አሰራሮች ወደ ዲጂታል የቴክኖሎጂ ስርዓት መቀየርን የሚያካትት ነው።

**ውጤት፡ በቴክኖሎጂ የተደገፉ ውጤታማ አሠራሮች**

## ዓላማ 3. የሀብት አጠቃቀም ውጤታማነትን ማሳደግ

**መግለጫ**

የሀብት አጠቃቀም ውጤታማነትን ማሳደግ ማለት ተቋሙ የተሰጠዉን ተልዕኮ ለማሳካት አስፈላጊ ቁሳዊ ሀብት እንዲመደብ የማድረግ፣ ሃብት የማመንጨት እና የተመደበዉን ሀብት በዉጤታማነት ማስተዳደር ነዉ።

**ዓላማውን ለማስፈፀም የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

የሀብት ፍላጎት እቅድ ማዘጋጀት እና ተደራድሮ ማስፈቀድ፣ ፍትሀዊ የበጀት ድልድል ማካሄድ፣ የበጀት አጠቃቀም ውጤታማነት ማረጋገጥ፣ የግዥ ፍላጎትን መለየት፣ በወቅቱ ጥራቱን የጠበቀ ግዥ መፈፀም፣ ማስራጨትና አጠቃቀሙን በመከታተል ውጤታማነቱን ማረጋገጥ፣ የቁሳዊ ሀብቶችንና የግብዓቶች አቅርቦት አፈፃፀምን ማሻሻል፣ ዉጤታማ የሆነ የፕሮጀክት አስተዳደር፣ ዉጤታማ የንብረት አያያዝ እና አወጋገድ፣ በበጀት አጠቃቀም ዙሪያ ተጠያቂነትን ማረጋገጥ እና የኦዲት ግኝቶች ላይ ወቅታዊ የእርምት እርምጃ መዉሰድን ይጨምራል።

**ውጤት፦ ዉጤታማ የሀብት አጠቃቀም**

## ዓላማ 4. የባለብዙ ዘርፍ አካታችነትና ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ

**መግለጫ**

የባለብዙ ዘርፍ አካታችነትና ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ ማለት በዓለም ዓቀፍ ህጎች እና መንግስት በሴቶችና በወጣቶች፣ በህፃናት፣ በአካል ጉዳተኞች፣ በኤች.አይ. ቪ. ኤድስ፣ የጤና እና አካባቢ ጥበቃ ስራዎች፣ በስርዓተ ፆታ ዙሪያ ያወጣቸውን የተለያዩ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችንና መመሪያዎችን በሚኒስቴር መ/ቤቱ በተሟላ ሁኔታ እንዲተገበሩ ማድረግ ነዉ::

**ዓላማውን ለማስፈፀም የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

የሴቶች አመራር ሰጪነት እና ተጠቃሚነትን ማረጋገጥን፣ በኤች.አይ.ቪ ቫይረስ በደማቸው ላለ እና በቫይረሱ ምክንያት ወላጅ እና አሳዳጊያቸውን ላጡ ድጋፍ ማድረግ፣ ለሴት ነጋዴዎች በታክስ አስተዳደር ዙሪያ ድጋፍ መስጠትን፣ የውስጥ ማህበራዊ ኃላፊነቶች ማለትም የህፃናት ማቆያ ማዘጋጀት ፣ ለአካል ጉዳተኛ ሰራተኞች እና ተገልጋዮች የተመቻቸ ሁኔታ መፍጠር፣ አነስተኛ ገቢ ያላቸውን ሰራተኞች ተጨማሪ የገቢ ምንጭ የሚያገኙበት ሁኔታ ማመቻቸት፣ አነስተኛ መደብ ላይ ያሉ ሰራተኞችን የትምህርት ደረጃቸውን እንዲያሻሽሉ ድጋፍ ማድረግ፣ ሰራተኛው አካላዊ ብቃቱ እና ጤንነቱ የተጠበቀ እንዲሆን የሚያስችሉ የስፖርታዊ እንቅስቃሴ የሚደረጉበትን ሁኔታ ማመቻቸት ፣ የወጣቶችን ተሳትፎ በልዩ ልዩ መንገዶች ማረጋገጥ፣ ለሰራተኞች የስነ ልቦና የምክር አገልግሎት የሚያገኙበት ሁኔታ ማመቻቸት፣ የሰራተኞች መረዳጃ ማህበር ማቋቋም ፣እንዲሁም የውጪ ማህበራዊ ሀላፊነቶች ማለትም የተቋሙ አመራር እና ሰራተኞችን በማስተባበር የአረንጓዴ ልማት እና የአካባቢ ጥበቃ ስራዎች ማከናወንን፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግር ያጋጠማቸውን የህብረተሰብ ክፍሎችን መርዳት የሚያካትት ነው።

**ውጤት፦ ያደገ የባለብዙ ዘርፍ ስራዎች ውጤታማነት**

## ዓላማ 5. ተቋማዊ የስጋት ስራ አመራርን ማጠናከር

**መግለጫ**

ተቋማዊ የስጋት ስራ አመራርን ማጠናከር ማለት በተቋም ደረጃ በተለያዩ የስራ ክፍሎች ሊያጋጥሙ የሚችሉ ስጋቶችን አስቀድሞ በመለየት የስጋት መጠኑን በመቀነስ ተቋማዊ ጤንነትን ማረጋገጥ ነው፡፡

**ዓላማውን ለማስፈፀም የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

ይህን ዓላማ ለማሳካት የሚከናወኑ ስራዎች የስጋት መከላከያ ስትራቴጂ መቅረፅ፣ ተቋማዊ ስጋቶችን መለየት እና ወቅታዊ ማድረግ፣ መተንተን፣ የስጋት ደረጃ ማውጣት፣ የስጋት ባለቤቶችን መለየት፣ የማስተካከያ እርምጃዎችን መውሰድ እና ውጤታማነትን ማረጋገጥን ያጠቃልላል፡፡

**ውጤት፡- ያደገ ተቋማዊ ጤንነት**

### 4.3.2 የአሠራር ልህቀት

የአገልግሎት አሰጣጡን ግልፅ፣ ቀላል፣ ቀልጣፋ፣ ተገማች እና ወጪ ቆጣቢ ለማድረግ፣ የህግ ማስከበርን ለማረጋገጥ እና ኢኮኖሚው የሚያመነጨውን የታክስ ገቢ በብቃት ለመሰብሰብ ዓለም ዓቀፍ ደረጃቸዉን የጠበቁ የአሠራር ተሞክሮዎችን በማምጣት የአሰራር ልህቀት ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ የአሰራር ልህቀትን ለማምጣት የህግ ማዕቀፎችን እና አሰራሮችን የማሻሻል፣ አዳዲስ የህግ ማዕቀፎችን እና አሠራሮችን የመቅረፅ፣ የታክስ መረጃ አስተዳደር ስርዓትን መዘርጋት እና ውጤታማነቱን ማረጋገጥን እንዲሁም በሀገር አቀፍ ደረጃ የተጣጣመ የታክስ አስተዳደር ስርዓት መዘርጋትን ያጠቃልላል፡፡

## ዓላማ 1. የአገልግሎት አሰጣጥ አፈፃፀምን ማሻሻል

**መግለጫ**

የአገልግሎት አሰጣጥ አፈፃፀምን ማሻሻል ማለት ተቋሙ በህግ የተሰጠዉን ስልጣንና ኃላፊነት ለማስፈፀም ቀጣይነት ባለዉ መልኩ የሚያከናዉናቸዉ ተግባራት ሲሆኑ እነዚህንም ተግባራት ለተገልጋዩ በጊዜ፣ በጥራት፣ ወጪ ቆጣቢ በሆነ መንገድ መፈፀምና ዕርካታዉን ማረጋገጥ የሚያጠቃልል ነዉ፡፡

**ዓላማውን ለማስፈፀም የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

ለተገልጋዩ በቀጥታ/Online/ አገልግሎት የሚያገኝበት ስርዓት መዘርጋት፣ የአንድ መስኮት አገልግሎት መዘርጋት፣ የአገልግሎት ተደራሽነትን ማስፋት፣ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ

አገልግሎት መስጠት፣ ዘመናዊ የቅሬታና አቤቱታ አፈታት ስርዓት መዘርጋት እና መተግበር፣ የአገልግሎት አሰጣጡ በተገልጋይ አገልግሎት መስጫ የስምምነት ሰነድ(የተገልጋዮች ቻርተር) መሰረት መሰጠቱን ማረጋገጥ፣ የአገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርድ ስምምነት ሰነድ በየጊዜዉ ወቅታዊ ማድረግ፣ የመረጃ አቅርቦት ማዕከሎችን (Contact Center) አፈፃፀም ማሻሻል፣ የደንበኞች አቀባበልና አገልግሎት አሰጣጥ ስርዓት መዘርጋት እና ተግባራዊ ማድረግ፣ ለተገልጋዮች ምቹ የሆነ የስራ ከባቢ መፍጠር፣ የ24/7 የጉምሩክ አገልግሎት መስጠት፣ ለተገልጋዩ እንደየ ባህሪዉ እና ደረጃዉ ልዩ አገልግሎት ማግኘት የሚችልበት የአገልግሎት ስርዓት መዘርጋት እና መተግበር፣ ዓለም ዓቀፍ የአገልግሎት አሰጣጥ ልህቀት /ISO Certificate/ ዕዉቅና ማግኘት እና በመጨረሻም ተገልጋዩ መርካቱን ማረጋገጥ የሚያጠቃልል ነዉ::

**ውጤት፡- ያደገ የተገልጋይ ዕርካታ**

## ዓላማ 2. የመረጃ አስተዳደር አፈፃፀምን ማሻሻል

**መግለጫ**

የመረጃ አስተዳደር አፈፃፀም ማሻሻል ማለት ለታክስና ጉምሩክ አስተዳደሩ አስፈላጊ የሆኑ የመረጃ ምንጮችን መለየት፣ መረጃ መሰብሰብ፣ ማጥራትና ማደራጀት፣ መረጃ መተንተን፣ መረጃ ማሰራጨትና ጥቅም ላይ ማዋልን ያካትታል:: በተጨማሪም የመረጃ አስተዳደር ፖሊሲ እና አጠቃቀም ስርዓት በመዘርጋት የመረጃ ደህንነትን ማረጋገጥን የሚያጠቃልል ነዉ::

**ዓላማውን ለማስፈፀም የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

የመረጃ አስተዳደር ፖሊሲ እና ስትራቴጂ ቀርፆ ስራ ላይ ማዋልን፣ የመረጃ ልዉዉጡን በቴክኖሎጂ ማስደገፍን፣ አህገራዊ፣ ቀጠናዊ፣ አህጉራዊና ዓለም ዓቀፋዊ የመረጃ ትስስር የሚፈጠርበት አሰራር መቅረፅ እና መተግበር፣ ከሀገራት ጋር የኢንተለጀንስ መረጃዎችን ልውውጥ አፈጻጸምን ማሻሻል፣ የመረጃ ደህንነትና ጥራት ማስጠበቅ፣ ትልልቅ መረጃዎችን ለመተንተን /Big Data Analysis/ የሚያስችል ስርዓት መዘርጋት እና ጥቅም ላይ እንዲውል ማድረግ፣ የመረጃ አሰጣጥ ስርዓት መዘርጋት እና መተግበረ፣ የዳታ ፎረንሲክ ላብራቶሪ መገንባትን፣ ዓለም አቀፍ የጉምሩኮች ድርጅት የዳታ ሞዴልና ፎርማት የተከተለ የንግድ መረጃ ልውውጥ ስርዓት መዘርጋት፣ ከሌሎች ሀገራት የጉምሩክ ተቋማት በሚደረግ የሁለትዮሽ የትብብር ስምምነትና ከአለም አቀፍ የዋጋ መረጃ አቅራቢ ደርጅቶች የጉምሩክ መረጃ መሰብሰብ፣ መተንተን እና መጠቀም ማስቻል፣ ተቋሙ የሚያመነጨውን እና የሚሰበስበውን

መረጃ በአግባቡ የማስተዳደር እና የመጠቀም አፈጻጸምን የማሻሻል፣ የየመረጃ ማከማቻ ማዕከል መገንባት፣ ዕዳና የዋስትና ሂሳቦች መረጃ አያያዝና አስተዳደር ማሻሻል እና የገቢ እና ወጪ ንግድ መረጃን ማደራጀት እና ማሰራጨትን ያጠቃልላል።

**ውጤት፡- የላቀ የመረጃ አያያዝ ስርዓት እና አጠቃቀም**

## ዓላማ 3. የአሠራር ስርዓት አፈፃፀምን ማሻሻል

**መግለጫ**

የአሰራር ስርዓት አፈፃፀምን ማሻሻል ማለት የታክስ፣ የጉምሩክና የሎተሪ የህግ ማዕቀፎች፣ የአሠራር ስርዓቶችን ማሻሻልን፣ አዳዲስ መቅረፅን እና በዘመናዊ ቴክኖሎጂ በማስደገፍ የላቀ አገልግሎት መስጠትን፣ ህግን ማስከበር እና የገቢ አሰባሰቡን ዉጤታማ ማድረግን የሚያካትት ነው።

**ዓላማውን ለማስፈፀም የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

የሀገር ውስጥ ታክስ አስተዳደር በተመለከተ የታክስ ህጎችን፣ የአሰራር ስርዓቶችን፣ የስራ ሂደቶችን በአዲስ መልክ የመቅረፅ፣ የማሻሻልና በቴክኖሎጂ የመደገፍ፣ ዓለም ዓቀፍ ደረጃቸውን የጠበቁ የአሰራር ስርዓቶችን በመዘርጋት የንግድ ስራን በማቅለል እና አመቺነቱን በማረጋገጥ /Ease of Doing Business/ የአሠራር ስርዓት ልህቀትን ማምጣት ነዉ። ከእነዚህም ውስጥ ዋና ዋናዎቹ የታክስ ከፋዮች ምዝገባ ስርዓትን በመዘርጋት እና በማዘመን ወደ ታክስ መረቡ ያልገቡትን ወደ ታክስ መረቡ ማስገባት፣ የተቀናጀ አንድ መስኮት አገልግሎትን ማስፋት፣ ወቅታዊ የንግድ ስራ ሀብቶች ዋጋ ማደራጃ ስርዓት መዘርጋት፣ የታክስ ከፋዮች ክትትል ስትራቴጂ ቀርፆ መተግበር፣ የታክስ ዉሳኔ ቅሬታ አሠራር ስርዓትን ማዘመን፣ የታክስ ዕዳ አስተዳደር ስርዓት መዘርጋት እና ማዘመንን፣ ውጤታማ የታክስ ተመላሽ አስተዳደር ስርዓትን መዘርጋት እና መተግበር፣ የገቢ አቅም ጥናት በማካሄድ የታክስ እምቅ አቅምን መለየት፣ የገቢ ሂሳቦች መረጃ አያያዝና ትልልፍ ስርዓትን ማዘመንን የሚያጠቃልል ነው። በተጨማሪም የታክስ መርሆዎችን፣ የታክስ ፖሊሲ አቅጣጫዎችን፣ የታክስ አስተዳደር ህግጋትን በሁሉም የፌደራልና የክልል/ከተማ አስተዳደርር አካላት እኩል ተፈፃሚ የሚሆኑበትን የአሰራር ስርዓት መዘርጋት፣ የታክስ ህጎች ማናበብ፣ የአቅም ግንባታ ድጋፍ ማድረግ፣ የክትትልና ድጋፍ ስርዓት መቅረፅ፣ ወጥ የሆነ የቴክኖሎጂ ዝርጋታና

አጠቃቀም ማሳደግ፣ የጋራ ገቢ እና ትልልፉን ማሳለጥ እና በመጨረሻም በሀገር ደረጃ የተጣጣመ ጠንካራ የታክስ አስተዳደር ስርዓት መገንባትን ያጠቃልላል፡፡

የጉምሩክ ህጎችን፣ የአሰራር ስርዓቶችን፣ የስራ ሂደቶችን በአዲስ መልክ የመቅረፅ፣ የማሻሻልና ዓለም ዓቀፍ ደረጃቸውን የጠበቁ የአሰራር ስርዓቶችን በመዘርጋት የንግድ ስራን በማቅለል እና አመቺነቱን በማረጋገጥ /Ease of Doing Business/ የአሠራር ስርአት ልህቀትን ማምጣት ነው፡፡

**የጉምሩክ ትራንዚትን** በተመለከተ ከጎረቤት አገራት ጋር አንድ ወጥ የጋራ የትራንዚት ሰነድ (SAD) እና የድንበር አንድ ማዕከል አገልግሎት (One Stop Border Post) መጀመር፣ ቀጠናዊ የጉምሩክ ትራንዚት ዋስትና ስርአት (Regional Customs Transit Guarantee - RCTG) መዘርጋት፣ ቀጠናዊ የጭነት መቆጣጠሪያ መሳሪያ (Regional Cargo Tracking) ስራ ላይ እንዲዉል ማድረግ፣ Cargo Scanning በመጠቀም የፍተሻ እና ቁጥጥር ስርዓቱን ውጤታማ ማድረግ እና ከአጓጓዥ ድርጅቶች ጋር የጭነት መግለጫ (cargo manifest) መረጃ ልዉዉጥ ሥርአት መዘርጋትን ያካትታል፡፡

**የመጋዘን አስተዳደር** ጋር በተያያዘ የጉምሩክ የመጋዘን አስተዳደር ስርአትን ማሻሻል ፣ የጭነት ማቀናጀት እና ማከፋፈል (cargo consolidation and deconsolidation) አሠራር ስርአት መዘርጋት ፣ ነፃ የንግድ ቀጠና /Free Zone/ አሰራር ስርዓት መዘርጋት፣ የተተዉና የተወረሱ እቃዎች አስተዳደር ስርአትን ማሻሻል እና በደህንነት ካሜራ የተደገፈ የአየር እና የደረቅ ወደብ የቁጥጥር ስርዓት መዘርጋት ያጠቃልላል፡፡

**የዕቃ አወጣጥ ጉምሩክ ሥነ ሥርአትን** በተመለከተ ቀላል የጉምሩክ ስነ ስርዓት (Simplified Customs Procedures) አፈፃፀምን ማሻሻል፣ የቅድመ እቃ አወጣጥ (Pre-arrival Clerance) አገልግሎት ማስፋት፣ የኢኮኖሚ አንቀሳቃሾች ስርአትን ማሻሻል፣ የቅድመ መረጃ አሰጣጥ (advance ruling) ስርአት ማሻሻል፣ የወጪ ንግድ ማበረታቻ ስርዓት ማሻሻል፣ የዋጋ ትመና አሰራርን ማሻሻል፣ የጉምሩክ ላብራቶሪ ማቋቋም፣ ከሀገራት ጋር ለተገቡት ስምምነቶች የአሠራር ስርአት መቅረፅ፣ የኤሌክትሮኒክስ ንግድ (e-commerce) ጋር የተጣጣመ የጉምሩክ አሠራር ሥርዓት መዘርጋት፣ የሸቀጦች አመዳደብ እና የታሪፍ ማሻሻያዎችን ወቅታዊ ማድረግ፣ የተሻሻለውን የኪዮቶ ስምምነት ስታንዳርድ (RKC) በሙሉ መተግበርና ዕውቅናን ማግኘት፣ የISO certificate ማግኘት የሚያስችል አሠራር መዘርጋት፣ የዕቃ ፍተሻ አሰራርን በዘመናዊ መሳሪያ እና በሰለጠኑ ውሾች ማስደገፍ ይጨምራል፡፡

የህግ ተገዢነትን ከማረጋገጥ አኳያ የኮንትሮባንድ እና ንግድ ማጭበርበር መከላከል አሰራር መቅረፅ ፣ የሥጋት ሥራ አመራር ስርአትን ማሻሻል ፣ የድህረ እቃ አወጣጥ ኦዲት አሰራርን ማሻሻል ፣ የኢንተለጀንስ እና ድንገተኛ ፍተሻ አሰራር ስርአት መዘርጋት ፣ በመንግስት የተሰጡ የቀረጥና ታክስ ማበረታቻዎች ክትትል እና ቁጥጥር ስርአት መዘርጋት ፣ የህግ ረቂቅ ፣ ምክር እና አስተያየት አሰጣጥ ስርአት መዘርጋት ፣ የፍትሀ ብሔር ጉዳዮች አሰራር ማሻሻል የሚያካትት ነው፡፡

የመፈፀም እና ማስፈፀም አቅም አሰራርን በተመለከተ አደረጃጀትን በየጊዜው እየፈተሹ ማስተካከያ ማድረግ ፣ የሰው ሀይል ምልመላ ፣ ቅጥር ፣ ስልጠና ፣ ማትጊያ አሠራር ስርአት ማሻሻል ፣የተተኪ አመራር የማፍሪያ ስርአት መዘርጋት፣ የሰራተኛ ደህንነት እና የጉዳት ካሳ አከፋፈል የአሰራር ስርዓት መዘርጋትን፣ ዉጤታማ የሰራተኛ ምዘና ስርዓት መዘርጋት ፣ የጥናትና ምርምር ስርአትን ማጠናከር ፣ የንብረት አስተዳደር እና አጠቃቀም ስርአትን ማሻሻል እና የክትትል ፣ ድጋፍ እና ግብረ መልስ ስርአት መዘርጋት ያካትታል፡፡

የሎተሪ አሠራር ስርዓትን በተመለከተ አዳዲስና አጓጊ የሎተሪ ጨዋታዎችን ማስተዋወቅ፣ የሎተሪ ሽያጭና የዕጣ አወጣጥ ስርዓት በመረጃ ቴክኖሎጂ ማስደገፍ፣ የዕድል ጨዋታ ተደራሽነትን ማሳደግ፣የዕድል ሽልማት መጠን ማሳደግ፣ አገልግሎት ሰጪውን ከተቆጣጣሪነት የሚለይ ህግ ማውጣትን ያጠቃልላል፡፡

**ውጤት፦ የላቀ የአሰራር ስርዓት**

## ዓላማ 4. የተጣጣመ ሀገራዊ የታክስ አስተዳደርን ማስፈን

**መግለጫ**

የተጣጣመ ሀገራዊ የታክስ አስተዳደርን ማስፈን ማለት ሚኒስቴሩ በአዋጅ የተሰጠውን ተልዕኮ መነሻ በማድረግ ኢኮኖሚው የሚያመነጨውን ገቢ በብቃት ለመሰብሰብ፣ ኢንቨስትመንትን ለመደገፍና ለማበረታታት፣ ፍትሃዊ የንግድ ውድድርን ለማጐልበት፣ በፌደራልና በክልሎች/ከተማ መስተዳድሮች፣ በክልሎች እና ከተማ መስተዳድሮች መካከል፣ ጠንካራ ኢኮኖሚያዊ ትስስር ለመፍጠር፣ በሀገር ደረጃ የተጣጣመ የታክስ አስተዳደር ለመገንባት የሀገር ውስጥ ታክስ አስተዳደር ስርዓቱን ማጣጣም የሚያካትት ነው፡፡

**ዓላማውን ለማስፈፀም የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- የታክስ አስተዳደር ተግባራትን በፌደራል እና በክልሎች/ከተማ መስተዳደሮች በሁሉም ዕኩል ተፈፃሚ እንዲሆኑ የሚያስችል የቴክኒክ ድጋፍ መስጠት፣
- የክልሎችን ተጨባጭ ሁኔታ መሰረት ያደረገ የክትትልና ድጋፍ ስርዓት ቀርፆ መተግበር። በዚህም ክልሎች ተመሳሳይ የታክስ አስተዳደር አፈፃፀም እንዲኖራቸው ማስቻል፣
- በሀገር ደረጃ የታክስ አስተዳደሩ በመረጃ ቴክኖሎጂ በማስደገፍ ጠንካራ የመረጃ ቅብብሎሽና አጠቃቀም ስርዓት መዘርጋት፣
- በክልል በሚገኙ የፌደራል ገቢ ሰብሳቢ ቅ/ጽ/ቤቶችና በክልል የገቢ ባለስልጣናት መካከል በህግ ማስከበር፣ በግብር ከፋዮች ትምህርትና ድጋፍ፣ በአቅም ግንባታና በሌሎች የታክስ ጉዳዩች የጋራ ስምሪት ማድረግና የገቢ አሰባሰቡን ማሻሻል፣
- ከክልል የገቢ ሰብሳቢና የፋይናንስ ዘርፍ ተቋማት ጋር ቋሚ የግንኙነት ስርዓት (ማለትም የምክክር መድረኮችን) በመዘርጋት የታክስ ፖሊሲና አስተዳደር አፈፃፀሞችን በጋራ መገምገም፣ መፍትሄ ማስቀመጥና አፈፃፀማቸውን መከታተል፣
- የጋራ ገቢዎች እና በዊዝሆልዲንግ ስርዓት የሚሰበሰቡ ግብርና ታክሶች በወቅቱ ወደ ገቢው ባለቤቶች መተላለፋቸውን ማረጋገጥ፣

**ውጤት፦ የተጣጣመ ሀገራዊ የታክስ አስተዳደር**

### 4.3.3 ስትራቴጂያዊ አጋርነት ልህቀት

ተቋሙ የተሰጠዉን ተልዕኮ ለማሳካት ከሀገር ዉስጥና ከዉጪ አጋር እና ባለድርሻ አካላት ጋር ተቀናጅቶ መስራት አስፈላጊ ነዉ። በዚህ የትኩረት መስክ የቅንጅት ስትራቴጂ መቅረፅ፣ አጋር አካላትን መለየት እና ተግባራዊ ማድረግን የሚያካትት ነዉ። በዚህ መሰረት ከሀገር ዉስጥ አጋር አካላት ጋር በህግ ማስከበር፣ በድንበር አስተዳደር፣ በታክስ ማጣጣም፣ በህጎች ዝግጅት፣ በሰዉ ኃይል አቅም ግንባታና ቅንጅት፣ በመረጃ ልዉዉጥ እና በቴክኖሎጂ ትስስር ላይ የሚያተኩር ሲሆን በተመሳሳይ ከዉጪ አጋር አካላት ጋር በቴክኒክ ድጋፍ፣ በዕዉቀት ሽግግር፣ በልምድ ልዉዉጥ ላይ በማተኮር በጋራ ተቀናጅቶ በመስራት ዉጤታማነትን ማረጋገጥ ታሳቢ ያደረገ የትኩረት መስክ ነዉ።

## ዓላማ 1. የሀገር ውስጥ አጋር አካላት አጋርነትና ትብብር ማሻሻል

**መግለጫ**

የሀገር ውስጥ አጋር አካላት ትብብር ማሻሻል ማለት ተቋሙ በህግ የተሰጠውን ስልጣንና ኃላፊነት ለመወጣት ቁልፍ ሚና ካላቸዉ የባለድርሻ አካላት ማለትም ከተቆጣጣሪ አካላት፣ ከክልልና ከከተማ አስተዳደር፣ ከፌዴራል ተቋማት፣ ከንግድና ሙያ ማህበራት ጋር ቅንጅት

በመፍጠር አገልግሎቱን በማሳለጥ፣ ንግድና ኢንቨስትመንትን በማበረታታት፣ የታክስና የንግድ ማጭበርበር እንዲሁም ኮንትሮባንድ መከላከልን ያጠቃልላል፡፡

### ዓላማውን ለማስፈፀም የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት

በዚህ ዓላማ የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት የቅንጅት ስትራቴጂ መቅረፅ፣ አጋር አካላትን መለየት ፣ ግኑኝነት መፍጠር እና አብሮ ለመስራት የሚያስችል የስምምነት ሰነድ (Service Level Agremeent) መፈራረም እና ቅንጅታዊ አሰራር በመዘርጋት በህግ ማስከበር፣ በአገልግሎት አሰጣጥ ፣ በድንበር አስተዳደር፣ በህጎች ዝግጅት፣ በሰዉ ኃይል አቅም ግንባታ፣ በመረጃ ልዉዉጥ እና በቴክኖሎጂ ትስስር ላይ በጋራ መስራትን የሚያካትት ነው፡፡

በዚሁ መሰረት ቅንጅት የሚፈጠርባቸዉ ዋና ዋና ባለድርሻ አካላት የገንዘብ ሚ/ር፣ የንግድ እና ኢንዱስትሪ ሚ/ር፣ የትራንስፖርት ሚ/ር፣ የትምህርት ሚ/ር፣ የሰላም ሚ/ር፣ የግብርና ሚ/ር፣ የኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ሚ/ር፣ የውጭ ጉዳይ ሚ/ር፣ የማዕድንና ነዳጅ ሚ/ር፣ የጤና ሚ/ር፣ የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚ/ር፣ የፌዴራል ዓቃቤ ህግ፣ የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ፣ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን፣የፕላንና ልማት ኮሚሽን፣ የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን፣ የክልል እና ከተማ አስተዳደሮች  የኢ.ባ.ት.ሎ.አ.ድ፣ የኢትዮ-ቴሌኮም፣ የኢትዮጵያ አየር መንገድ፣ ባንኮች፣ የንግድ ዘርፍ ማህበራት፣ የታክስ እና ኦዲት ባለሙያዎች፣ የአካዉንታንቶች እና ሂሳብ አዋቂዎች ማህበር እና የጉምሩክ አስተላላፊዎች የሙያ ማህበር ናቸዉ፡፡

### ውጤት፦ የተፈጠረ ዉጤታማ ቅንጅት ፤ የተፈቱ ችግሮች

## ዓላማ 2. የውጭ ሀገራትና ድርጅቶች አጋርነትና ትብብር ማሻሻል

### መግለጫ

የውጭ ሀገራትና ድርጅቶች አጋርነት ማጠናከር ማለት ተቋሙ ተልኮዉን ለማሳካት እንዲያስችለዉ ከዉጭ ሀገራት፣ ዓለም ዓቀፍና አህጉራዊ ድርጅቶች ጋር የቴክኒክ ድጋፍ እና ተሞክሮ ማግኘት የሚያስችል ትብብር መፍጠርን የሚያካትት ነዉ፡፡

### ዓላማውን ለማስፈፀም የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት

ተቋሙ ተልኮዉን ለማሳካት እንዲያስችለዉ ትብብር መፍጠር አስፈላጊ የሆነባቸዉን የውጭ አገራት፣ ዓለም አቀፋዊና አህጉራዊ ድርጅቶችን ፣ የቴክኒክ ድጋፍ ዓይነቶችን የመለየት፣ ትብብር በመፍጠር የጉምሩክ የሁለትዮሽ (Bilateral agreements) እና የቡዝዮሽ (Multi-

lateral agreement) ስምምነት የመፈራረም፣ በአህጉራዊ እና በዓለም አቀፍ መድረኮች ላይ በመሳተፍ ለተቋሙ ጥቅም በሚያስገኙ ጉዳዮች ላይ መደራደር፣ መረጃ ልውውጥ፣ በጋራ ድንበር አስተዳደር፣ ኮንትሮባንድ መከላከል እና ቁጥጥር፣ በቴክኒክ ድጋፍ፣ በእዉቀት ሽግግር እና በልምድ ልዉዉጥ ላይ በማተኮር በቅንጅት እና በትብብር በመስራት አገልግሎት አሰጣጥን ማሳለጥ እና ህግ ተገዢነት ማረጋገጥን ያካተተ ነው፡፡

በዚሁ መሰረት አጋርነት የሚፈጠርባቸዉ አገራት፣ አህጉራዊና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች መካከል የጎረቤት አገራት፣ ከኢትዮጵያ ጋር ከፍተኛ የሆነ የንግድ ትስስር ያላቸዉ አገራት፣ ለወጪ ዕቃዎች የቀረጥ ነጻ ዕድል የሰጡ ሀገራት፣ የምስራቅና የደቡባዊ አፍሪካ አገራት የጋራ ገቢያ (COMESA)፣ የአፍሪካ ህብረት (AU)፣ የዓለም ንግድ ድርጅት (WTO)፣ የዓለም ጉምሩኮች ድርጅት (WCO)፣ የዓለም ባንክ (WB)፣የአፍሪካ ልማት ባንክ (AfDB)፣ የዓለም ገንዘብ ድርጅት (IMF)፣ የአወሮፓ ህብረት (EU)፣ የአሜሪካ የልማት ተራድኦ ድርጅት (USAID)፣ የእንግሊዝ ዓለም አቀፍ የልማት ድርጅት (DFID)፣ የጃፓን ዓለም አቀፍ ትብብር ኤጀንሲ (JICA)፣ የኮሪያ ዓለም አቀፍ ትብብር ኤጀንሲ (KOICA) እና ሌሎች የውጭ አጋር አካላትን የሚያጠቃልል ነዉ፡፡

**ውጤት፡- የተፈጠረ ዉጤታማ ግንኙነት፣ የተገኘ የቴክኒክ ድጋፍ**

### 4.3.4 የህግ ተገዢነት አመራር ልህቀት

ሀገራዊ የታክስና ጉምሩክ ገቢ በላቀ ሁኔታ ለማሳደግ የህግ ተገዢነትን ማሳደግ ወሳኝ ነው፡፡ የህግ ተገዢነት ስራዎች ሲባል በዋናነት የስጋት ስራ አመራር ስራዎችን ማጠናከር፣ የታክስ ከፋዮች ትምህርት፣ ታክስ እና ቀረጥ በፈቃደኝነት የመክፈል ባህልን ማሳደግ፣ የታክስ ማጭበርበርና እና ኮንትሮባንድን መከላከል የሚያስችል ስርዓት በመዘርጋት የታክስና ጉምሩክ ህግ ተገዢነትን በላቀ ደረጃ ማሳደግን ታሳቢ ያደረገ ነዉ፡፡

## ዓላማ 1. የስጋት ስራ አመራር አፈፃፀምን ማሻሻል

**መግለጫ**

የስጋት ስራ አመራር አፈፃፀምን ማሻሻል ማለት ተቋሙ የአገልግሎት አሰጣጡን ለማላቅ፣ የህግ ተገዢነትን ለማሳደግ እና የገቢ አሰባሰቡን ለማሻሻል የስጋት ስራ አመራር ስርዓት በመዘርጋት ዉጤታማነትን ማረጋገጥ ነዉ፡፡

### ዓላማውን ለማስፈፀም የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት

የስጋት ስራ አመራር ስትራቴጂ ማሻሻል፣ ስጋቶችን መለየትና መተንተን፣ የስጋት ፕሮፋይል ማደራጀትን፣ የስጋት ደረጃ ማዉጣት እና ማስተናገድ፣ የስጋት ደረጃ መለያ አሰራርና መስፈርት መቅረፅን፣ ታክስ ከፋዮችን በስጋት ደረጃ መለየትን፣ ስጋት መጣልን፣ የስጋት ስራ አመራር ስራዓቱ ዉጤታማ መሆኑን መገምገምና የማስተካከያ እርምጃ በመዉሰድ የአገልግሎት አሰጣጥና የቁጥጥር ስርዓቱ ዉጤታማ በሆነ የስጋት ስራ አመራር ስርዓት መመራቱን ማረጋገጥን ያካትታል፡፡

### ውጤት፦ ያደገ የስጋት ስራ አመራር ዉጤታማነት

## ዓላማ 2. የታክስ ማጭበርበር እና ኮንትሮባንድ መከላከል አፈፃፀምን ማሻሻል

### መግለጫ

የታክስ ማጭበርበር እና ኮንትሮባንድ መከላከል አፈፃፀምን ማሻሻል ማለት በታክስ ማጭበርበር፣ በገቢና ወጪ ዕቃዎች ላይ የሚፈፀምን የንግድ ማጭበርበር እንዲሁም ኮንትሮባንድን በመከላከል እና በመቆጣጠር የንግድ ስርዓቱን ፍትሀዊነት እና የህብረተሰቡን ደህንነት ማረጋገጥ፣ በህገ-ወጥ ተግባራት ላይ የተሰማሩ ወደ ህጋዊ መስመር እንዲገቡ በማስተማር ግንዛቤያቸዉን ማሳደግ እና ከጥፋታቸዉ መታረም ያልቻሉትን ደግሞ ከአጋር አካላት ጋር በመቀናጀት አስተዳደራዊና ህጋዊ ዕርምጃ በመዉሰድ ሌሎችም እንዲማሩበት ማድረግን የሚጨምር ነዉ፡፡

### ዓላማውን ለማስፈፀም የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት

ዓላማዉን ለማሳካት በታክስ ማጭበርበር፣ በተለያዩ ህገወጥ ተግበራት ላይ የተሰማሩትን በስጋት ደረጃቸዉ በመለየት ማስተማር፡፡ ለህግ ተገዥ ያልሆኑትን በኢንተለጀንስ ክትትል፣ በኢንቨስትጌሽን ኦዲት እና በወንጀል ምርመራ ተገቢዉን ማጣራት በማድረግ በታክስ ስወራና ማጭበርበር ላይ የተሰማሩትን እንዲሁም ለጥፋቱ ተባባሪ አካላትን በመለየት እንደየጥፋት ደረጃቸዉ አስተማሪ እና ስጋት የሚፈጥር ህጋዊ እርምጃ መዉሰድ ይጠበቃል፡፡

የንግድ ማጭበርበር መከላከል እና መቆጣጠር ስራዎች ውጤታማነት ማረጋገጥ፣ የዕቃ እና ሰነድ ምርመራ፣ የድህረ እቃ አወጣጥ ኦዲት፣ የፍትህብሔር ጉዳዮች ክትትል እና አስተዳደራዊ ቅጣቶችን መተግበርን ያካትታል፡፡ ኮንትሮባንድን በመከላከል እና በመቆጣጠር ረገድ የኢንተለጀንስ

ክትትል፣ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘ የቅኝት ስራ መስራት፣ ከህግ አስከባሪ አካላት ጋር በቅንጅት መስራት፣ በመግቢያ በሮች እና በትራንዚት መስመሮች ላይ ያለውን የቁጥጥር ስርአት ማጠናከር እና በኮንትሮባንድ ተዋናዮች ላይ ተመጣጣኝ ህጋዊ እርምጃ ማስወሰድን ያካትታል፡፡

**ዉጤት፡- የቀነሰ ንግድ ማጭበርበር እና ኮንትሮባንድ**

## ዓላማ 3. የታክስ ህግ ተገዢነት አፈፃፀምን ማሻሻል

**መግለጫ**

የታክስ ህግ ተገዢነት አፈፃፀም ማሻሻል ማለት ዋና ዋና የታክስና የጉምሩክ የህግ ተገዢነት ስራዎች በስጋት ስራ አመራር መርህ መሰረት እየተመሩ ውጤታማነታቸውን ማረጋገጥን የሚያካትት ነዉ፡፡

**ዓላማውን ለማስፈፀም የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

የትምህርት ስትራቴጂ መቅረፅ እና መተግበርን፣ ትምህርቱ ያመጣውን ፋይዳ በመገምገም ቀጣይነት ያለው ማሻሻያ ማድረግን፣ ተገልጋዮች ታክስ እና ቀረጥ በወቅቱ እና በትክክል አሳውቀው መክፈላቸውን ማረጋገጥን፣ የታክስ እና ጉምሩክ የኦዲት ስትራቴጂ ቀርፆ በመተግበር የኦዲት ውጤታማነት ማረጋገጥን የሚያካትት ሲሆን በተጨማሪም ለታክስ ህጉ ተገዥ የሆኑትን በመለየት ዕውቅናና ሽልማት መስጠትን ይጨምራል፡፡

**ውጤት፡ ያደገ የህግ ተገዥነት**

### 4.3.5 ዘላቂ የገቢ ዕድገት

መንግስት የቀረፀው የብልፅግና እቅድ ሊሳካ የሚችለዉ ኢኮኖሚዉ የሚያመነጨዉ የታክስ ገቢ በብቃት መሰብሰብ ሲቻል ነዉ፡፡ በመሆኑም የትኩረት መስኩ ዋነኛ ግብ ከላይ ከተመለከቱት የትኩረት መስኮች ተፈፃሚነት ጋር ቁልፍ ትስስር ያለዉ ነዉ፡፡ ስለሆነም ዘላቂ ገቢን ለማረጋገጥ ቀጣይነት ያለዉ ተቋማዊ አቅም መገንባት፣ የአሰራር ስርዓት መዘርጋት፣ የህግ ተገዥነትን ማረጋገጥ እንዲሁም ስትራቴጂክ አጋርነትን ማጠናከር ወሳኝነት አላቸው፡፡ በዚሁ መሰረት ቀጣይነት ባለዉ መልኩ የገቢ ዕድገትን ለማረጋገጥ የታክስ ድርሻን ከአጠቃላይ ሀገራዊ ምርት አንፃር በማሳደግ ሀገራዊ ወጪን በታክስ ገቢ መሸፈንን ታሳቢ ያደረገ የትኩረት መስክ ነዉ፡፡

## ዓላማ 1. የገቢ አሰባሰብ ውጤታማነትን ማሻሻል

**መግለጫ**

የገቢ አሰባሰብ ውጤታማነትን ማሻሻል ማለት በተገነባ ተቋማዊ አቅም፣ በላቀ የታክስ እና ጉምሩክ አስተዳደር ስርዓት፣ በተሳለጠ የአገልግሎት አሰጣጥ፣ ባደገ ጠንካራ የሀገር ዉስጥና የዉጪ ሀገር ትብብርና አጋርነት እና በላቀ የህግ ተገዢነት የሚመጣ የተቋሙ ቁልፍና የመጨረሻ ውጤት ነው፡፡ ይህ ዓላማ በእነዚህ ማሻሻያዎች መነሻነት ከሀገር ውስጥ እና ከውጭ ንግድ የሚሰበሰበዉን ገቢ በውጤታማነት መሰብሰቡን የምናረጋግጥበት እና በአፈፃፀም ሂደት የሚያጋጥሙ ችግሮችን በመለየት ቀጣይነት ላለዉ የማሻሻያ ስራ በግብዓትነት መጠቀምን የሚያካትት ነው፡፡

**ውጤት፡- ያደገ ገቢ**

## 4.4 መለኪያዎች

### 4.4.1 የዘላቂ ገቢ ዕድገት መለኪያዎች

ሰንጠረዥ 8፡ የዘላቂ ገቢ ዕድገት መለኪያዎች

| የስትራቴጂክ ግብ | መለኪያ | መነሻ /2012/ | ዒላማ /2017/ | ዓመታዊ ዒላማ | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | 2013 | 2014 | 2015 | 2016 | 2017 |
| የገቢ አሰባሰብ ውጤታማነትን ማሻሻል | አጠቃላይ የታክስ ገቢ ዕቅድ በቢሊዮን ብር | 311.5 | 947.9 | 379.0 | 500.7 | 610.7 | 747.6 | 947.9 |
| | የታክስ ገቢ ለሀገራዊ ምርት ያለው ጥምርታ በመቶኛ | 9.2 | 12.7 | 10.2 | 11.4 | 11.7 | 12.0 | 12.7 |
| | የታክስ ገቢ ከሀገራዊ ወጪ ያለው ድርሻ በመቶኛ | 63.8 | 70.7 | 63.9 | 68.4 | 68.5 | 69.1 | 70.7 |
| | የፌደራል ገቢ ዕቅድ በቢሊዮን ብር | 209.3 | 640.0 | 271.8 | 336.5 | 421.5 | 515.5 | 640.0 |
| | የፌደራል ታክስ ገቢ ለሀገራዊ ምርት ያለው ጥምርታ በመቶኛ | 6.2 | 8.6 | 7.5 | 7.7 | 8.1 | 8.3 | 8.6 |
| | የፌደራል ታክስ ገቢ ከሀገራዊ ወጪ ያለው ድርሻ በመቶኛ | 42.9 | 47.7 | 47.0 | 47.2 | 47.3 | 47.6 | 47.7 |
| | የሀገር ውስጥ ገቢ ከአጠቃላይ ገቢ ያለው ድርሻ በመቶኛ | 55.0 | 59.0 | 55.0 | 56.0 | 57.0 | 58.0 | 59.0 |

| የስትራቴጂክ ግብ | መለኪያ | መነሻ /2012/ | ዒላማ /2017/ | ዓመታዊ ዒላማ | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | 2013 | 2014 | 2015 | 2016 | 2017 |
| | የጉምሩክ ገቢ ከአጠቃላይ ገቢ ያለው ድርሻ በመቶኛ | 45.0 | 41.0 | 45.0 | 44.0 | 43.0 | 42.0 | 41.0 |
| | የታክስ አስተዳደር ወጪ (100 ብር ለመሰብሰብ) | 1.7 | 2.2 | 5.3 | 3.5 | 2.0 | 2.6 | 2.2 |

## 4.4.2 የህግ ተገዥነት አመራር ልህቀት መለኪያዎች

ሰንጠረዥ 9፡ የህግ ተገዥነት አመራር ልህቀት መለኪያዎች

| ስትራቴጂክ ግብ | መለኪያ | መነሻ /2012/ | ዒላማ /2017/ | ዓመታዊ ዒላማ | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | 2013 | 2014 | 2015 | 2016 | 2017 |
| የታክስ ህግ ተገዥነት አፈፃፀምን ማሻሻል | ወደ ታክስ መረቡ የገቡ ግብር ከፋዮች በቁጥር(በሺ.ህ) | 41,396 | 75,609 | 47,448 | 54,755 | 59,404 | 67,309 | 75,609 |
| | በፈቃደኝነት የተከፈለ የታክስ ገቢ ድርሻ በመቶኛ | 83.5 | 88 | 84 | 85 | 86 | 87 | 88 |
| | የንግድ ትርፍ ግብር በወቅቱ ያሳወቁ ግብር ከፋዮች በመቶኛ | 69 | 79 | 71 | 73 | 75 | 77 | 79 |
| | የተ.እ. ታ በወቅቱ ያሳወቁ ታክስ ከፋዮች በመቶኛ | 70 | 80 | 72 | 74 | 76 | 78 | 80 |
| | የንግድ ትርፍ ግብር ከክፍያ ጋር ያሳወቁ ግብር ከፋዮች በመቶኛ | 46 | 69 | 50 | 63 | 65 | 67 | 69 |

| ስትራቴጂክ ግብ | መለኪያ | መነሻ /2012/ | ዒላማ /2017/ | ዓመታዊ ዒላማ | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | 2013 | 2014 | 2015 | 2016 | 2017 |
| | የተ.እ. ታ ከክፍያ ጋር ያሳወቁ ታክስ ከፋዮች በመቶኛ | 29 | 45 | 35 | 39 | 41 | 43 | 45 |
| | የታክስ ኦዲት ሽፋን በመቶኛ | 9 | 17 | 13 | 14 | 15 | 16 | 17 |
| | በታክስ ኦዲት በልዩነት የተወሰነ ገቢ (በቢሊዮን ብር) | 27 | 20 | 28 | 26 | 24 | 22 | 20 |
| | በፍርድ ቤት የመርታት አቅም በመቶኛ | 78 | 88 | 80 | 82 | 84 | 86 | 88 |
| የታክስ ማጭበርበርና ኮንትሮባንድ መከላከል አፈፃፀምን ማሻሻል | የኢንተለጀንስ ዉጤታማነት በመቶኛ | 72 | 82 | 74 | 76 | 78 | 80 | 82 |
| | የኮንትሮባንድ መከላከል ውጤታማነት ኢንዴክስ በመቶኛ | 63 | 77 | 65 | 67 | 70 | 73 | 77 |
| የስጋት ስራ አመራር አፈፃፀምን ማሻሻል | በስጋት መሠረት የተመረጡ የታክስ ከፋዮች ማህደራት ዉጤታማነት በመቶኛ | 90.5 | 93 | 91 | 91.5 | 92 | 92.5 | 93 |
| | የጉምሩክ ሥጋት ሥራ አመራር ውጤታማነት ኢንዴክስ በመቶኛ | 52 | 73 | 59 | 62 | 66 | 70 | 73 |

### 4.4.3 የአሠራር ልህቀት መለኪያዎች

ሰንጠረዥ 10፡ የአሠራር ልህቀት መለኪያዎች

| የስትራቴጂክ ግብ | መለኪያ | መነሻ /2012/ | ዒላማ /2017/ | ዓመታዊ ዒላማ | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | 2013 | 2014 | 2015 | 2016 | 2017 |
| የተጣጣመ ሀገራዊ የታክስ አስተዳደር ስርዓት | የተጣጣመ ሀገራዊ የታክስ አስተዳደር አፈፃፀም ኢንዴክስ በመቶኛ | 70 | 95 | 75 | 80 | 85 | 90 | 95 |
| የአሠራር ስርዓት አፈፃፀምን ማሻሻል | በስታንዳርድ መሠረት የተመዘገቡ ግብር ከፋዮች በመቶኛ | 75 | 90 | 78 | 81 | 84 | 87 | 90 |
| | በስታንዳርድ መሠረት ታክስ በማስታወቅ የከፈሉ ግብር ከፋዮች በመቶኛ | 59 | 69 | 61 | 63 | 65 | 67 | 69 |
| | በኢ-ታክስ ያሳወቁ ግብር ከፋዮች በመቶኛ | 30 | 100 | 45 | 70 | 100 | 100 | 100 |
| | በኢ-ታክስ የከፈሉ ግብር ከፋዮች በመቶኛ | 11 | 100 | 20 | 40 | 60 | 90 | 100 |
| | በስታንዳርድ መሠረት ኦዲት የተደረገላቸዉ ግብር ከፋዮች በመቶኛ | 61 | 76 | 64 | 67 | 70 | 73 | 76 |
| | የተከማቸ የታክስ ዕዳ በዓመት ዉስጥ ከተሰበሰበዉ የታክስ ገቢ ያለው ድርሻ በመቶኛ | 19 | 5 | 16 | 13 | 10 | 7 | 5 |
| | በስታንዳርድ መሠረት የታክስ ክሊራንስ ያገኙ ግብር ከፋዮች በመቶኛ | 73 | 88 | 76 | 79 | 82 | 85 | 88 |
| | በስታንዳርድ መሠረት የታክስ ተመላሽ የተደረገላቸው ግብር ከፋዮች በመቶኛ | 70 | 80 | 72 | 74 | 76 | 78 | 80 |
| | በስታንዳርድ መሠረት የታክስ ቅሬታ የታየላቸው ግብር ከፋዮች በመቶኛ | 80 | 90 | 82 | 84 | 86 | 88 | 90 |

| የስትራቴጂክ ግብ | መለኪያ | መነሻ /2012/ | ዒላማ /2017/ | ዓመታዊ ዒላማ | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | 2013 | 2014 | 2015 | 2016 | 2017 |
| | በወቅቱ የተዘጉ የገቢ ሂሳቦች በመቶኛ | 95 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| | በስታንዳርድ መሠረት የተፈፀመ የገቢ ትልልፍ በመቶኛ | 90 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| | በጉምሩክ በስታንዳርድ መሠረት የተሰጠ አገልግሎት በመቶኛ | 88 | 93 | 89 | 90 | 91 | 92 | 93 |
| | ገበያ ላይ የዋሉ አዳዲስ የሎተሪ ጨዋታ ዓይነቶች በቁጥር | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 |
| የመረጃ አስተዳደር አፈፃፀምን ማሻሻል | የመረጃ አስተዳደር አፈፃፀም ኢንዴክስ በመቶኛ | 56 | 75.8 | 59.5 | 62.8 | 66.1 | 70.9 | 75.8 |
| የአገልግሎት አሰጣጥ አፈፃፀምን ማሻሻል | የተገልጋዮች ዕርካታ በመቶኛ | 74 | 84 | 76 | 78 | 80 | 82 | 84 |

### 4.4.4 የስትራቴጂክ አጋርነት ልህቀት መለኪያዎች

ሰንጠረዥ 11፡ የስትራቴጂክ አጋርነት ልህቀት መለኪያዎች

| የስትራቴጂክ ግብ | መለኪያ | መነሻ /2012/ | ዒላማ /2017/ | ዓመታዊ ዒላማ | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | 2013 | 2014 | 2015 | 2016 | 2017 |
| የሀገር ውስጥ አጋር አካላት አጋርነትና ትብብር ማሻሻል | የሀገር ውስጥ ትብብር አፈፃፀም ውጤታማነት ኢንዴክስ | 70 | 85 | 73 | 76 | 79 | 82 | 85 |
| የውጭ አገራትና ድርጅቶች አጋርነትና ትብብርን ማሻሻል | የውጭ ትብብር አፈፃፀም ውጤታማነት ኢንዴክስ | 50 | 75 | 55 | 60 | 65 | 70 | 75 |

### 4.4.5 የተቋማዊ አቅም ልማት መለኪያዎች

| የስትራቴጂክ ግብ | መለኪያ | መነሻ | ዒላማ /2017/ | ዓመታዊ ዒላማ |
|---|---|---|---|---|

| | | /2012/ | | 2013 | 2014 | 2015 | 2016 | 2017 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የሰው ኃይል የመፈፀም ብቃትን ማሳደግ | የሠራተኛ ምርታማነት (በአንድ ሰው የሚሰበሰብ ገቢ በሚሊዮን ብር) | 18 | 37 | 20 | 22 | 25 | 30 | 37 |
| | የሰራተኛ ዕርካታ በመቶኛ | 68 | 83 | 71 | 74 | 77 | 80 | 83 |
| የባለብዙ ዘርፍ አካታችነትና ተጠቃሚነትን ማሳደግ | ወደ አመራር የመጡ የሴት ሰራተኞች ድርሻ በመቶኛ | 38 | 50 | 42 | 46 | 50 | 50 | 50 |
| | የባለብዙ ዘርፍ አካታችነት አፈፃፀም ኢንዴክስ | 60 | 95 | 65 | 70 | 75 | 85 | 95 |
| የሀብት አጠቃቀም ውጤታማነትን ማሻሻል | የኦዲት ግኝት ልዩነት ማስተካከል አፈፃፀም በመቶኛ | 70 | 100 | 75 | 80 | 85 | 90 | 100 |
| | የበጀት አጠቃቀም ውጤታማነት በመቶኛ | 80 | 98 | 90 | 90 | 95 | 98 | 98 |
| የመረጃ ቴክኖሎጂ ሀብት እና አጠቃቀም ማሻሻል | በስራ ላይ የዋሉ ቴክኖሎጂዎች ውጤታማነት ኢንዴክስ በመቶኛ | 46 | 90 | 59 | 71 | 79 | 85 | 90 |
| ተቋማዊ የስጋት ስራ አመራርን ማሻሻል | የቀነሰ የስጋት ተጋላጭነት በመቶኛ | 83 | 48 | 76 | 69 | 62 | 55 | 48 |
| | የቀነሰ የስነ-ምግባር ግድፈት በመቶኛ | 1.78 | 0.94 | 1.61 | 1.45 | 1.28 | 1.11 | 0.94 |

# 5 ስትራቴጂካዊ የማስፈፀሚያ እርምጃዎች

እያንዳንዱ የትኩረት መስክ የታለሙትን ዉጤት እንዲያመጣ ወይም እንዲፈፀም የማስፈፀሚያ እርምጃዎች ማለትም ተግባሮችን ወደ ተጨባጭ ዉጤት ለመለወጥ አስቻይ ሁኔታዎች ማለት ሲሆን በዚህ መሰረት በቀጣይ አምስት ዓመታት ስትራቴጂክ የትኩረት መስኮችን እና ግቦችን በማስፈፀም ሂደት ላይ አስቻይ ሁኔታዎችን ለይቶ ማስተግበር እና አፈፃፀማቸዉንም ክትትል በማድረግ አስፈላጊ ነዉ፡፡ ስለሆነም የእነኝህ እርምጃዎች መተግበር ብቻ ሳይሆን የመተግበራቸዉ ዉጤት የግቦች መሳካት ስለሆነ የእነኝህን ሂደቶች ትስስር መከታተል አስፈላጊ ይሆናል፡፡ ስለሆነም ስትራቴጂክ ግቦችን ለማስተግበረ ቀዳማይ ወይም ትይዩ አስቻይ የሆኑ ስራዎች እንደሚከተለዉ ተለይተዉ ቀርበዋል፡፡

## 5.1 የትኩረት መስኮች/ ስትራቴጂክ ግቦች /፣ ኢኒሼቲቮች እና ፕሮጀክቶች

ሰንጠረዥ 12፡ ኢኒሼቲቮች እና ፕሮጀክቶች

| የትኩረት መስኮች | ስትራቴጂክ ግቦች | ኢኒሼቲቮች እና ፕሮጀክቶች |
|---|---|---|
| ቀጣይነት ያለው ተቋማዊ አቅም ልማት | 1. የሰዉ ኃብት መሳብ፣ ማቆየትና የመፈፀም ብቃት ማሳደግ<br>2. የመረጃ ቴክኖሎጂ ሀብት እና አጠቃቀምን ማዘመን<br>3. የሀብት አጠቃቀም ውጤታማነትን ማሳደግ<br>4. የባለብዙ ዘርፍ አካታችነትና ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ<br>5. ተቋማዊ የስጋት ስራ አመራርን ማጠናከር | 1. የሰው ኃብት ስትራቴጂ መቅረፅና መተግበር፣<br>2. የፈፃሚ እና አመራር ብቃትን ማሳደግ*፣<br>3. የታክስ እና የጉምሩክ ስልጠና ማዕከልን አቅም መገንባት*፣<br>4. የሠራተኛ የአፈፃፀም ምዘና ስርዓት በቴክኖሎጂ ማስደገፍ፣<br>5. የሠራተኛ ማትጊያ/ማበረታቻ ስርዓት መዘርጋት፣<br>6. ምቹ የሆነ የስራ ከባቢ መፍጠር*፣<br>7. የመረጃ ቴክኖሎጂ ስትራቴጂ መቅረፅና መተግበር፣<br>8. የመረጃ መጠባበቂያ ማዕከል (Disaster Recovery Center) ማቋቋም፣<br>9. የመረጃ ደህንነት መሰረተ ልማት (IT Security Infrastructure) መዘርጋት፣<br>10. ዲጂታል የታክስ እና የጉምሩክ አስተዳደር መዘርጋት* (E-invoice, National ID, Cargo Tracking, Cargo Scanning, E-Single Window, SIGTAS, etc) ፣<br>11. የጉምሩክ የዋጋ ትመና መረጃ ስርዓት እና ዳታቤዝ ማሻሻል፣<br>12. የData Modeling and Big Data Analysis |

| የትኩረት መስኮች | ስትራቴጂክ ግቦች | ኢኒሼቲቮች እና ፕሮጀክቶች |
|---|---|---|
| | | ስርዓት መዘርጋት፣<br>13. የተቋማዊ ቁሳዊ እና የፋይናንስ ሀብት አጠቃቀም ውጤታማነትን ማሳደግ፣<br>14. የባለብዙ ዘርፍ አካታችነትና ተጠቃሚነት ስትራቴጂ መቅረፅና መተግበር፣<br>15. ተቋማዊ የስጋት ስራ አመራርን ማጠናከር፣<br>16. የውጭ ሀገር ተልዕኮ ትምህርት ማመቻቸት፣ |
| የአሰራር ልህቀት | 6. የአገልግሎት አሰጣጥ አፈፃፀምን ማሻሻል<br>7. የመረጃ አስተዳደር አፈፃፀምን ማሻሻል<br>8. የአሠራር ስርዓት አፈፃፀምን ማሻሻል<br>9. የተጣጣመ ሀገራዊ የታክስ አስተዳደርን ማስፈን | 17. የስራ ሂደቶች ማሻሻያ (Business Process Transformation) መቅረጽና መተግበር*፣<br>18. የታክስ kiosks እና Tax Clinic ፕሮግራም መዘርጋትና መተግበር*፣<br>19. የታክስ አካውንት ማናጀርስ ፕሮግራምን ማስፋት፣<br>20. ከአጋር አካላት ጋር የመረጃ ልውውጥን በተክኖሎጂ ማስተሳሰር (Interface)፣<br>21. የመረጃ ጥራት ማሻሻያ ስርዓት መዘርጋት እና መተግበር፣<br>22. የታክስ ዕዳ አስተዳደር ስርዓትን ማዘመን፣<br>23. የታክስ ተመላሽ ስርዓትን ማሻሻል፣<br>24. የኤክሳይስ ታክስ አስተዳደር ማጠናከር፣<br>25. የተ.እ. ታ አስተዳደር ማጠናከር፣<br>26. የተጣጣመ ሀገራዊ የታክስ አስተዳደር ማስፈን፣<br>27. ከአዋሳኝ ሀገሮች ጋር የአንድ አለቅ ፕሮጀክቶችን /one stop border post / ማጠናቀቅ*፣ |
| ስትራቴጂያዊ አጋርነት ልህቀት | 10. የሀገር ውስጥ አጋር አካላት አጋርነትና ትብብር ማሻሻል<br>11. የውጭ ሀገራትና ድርጅቶች አጋርነትና ትብብርን ማሻሻል | 28. ባለድርሻ አካላትን ቅንጅታዊ አሰራር የሚመራበት ፕሮግራም መቅረፅና መተግበር፣<br>29. የቀረጥ ነፃ መብትና የታክስ ዕፎይታ አሰጣጥና ቁጥጥርን ለማሻሻል ከአጋር አካላት ጋር አሰራር መቅረፅና መተግበር፣<br>30. የአጋሮችና ባለድርሻ አካላት አስተዳደር ስትራቴጂ መቅረፅና መተግበር፣<br>31. ከዉጪ አጋር አካላት ጋር የመረጃ ልውውጥ ስርዓት መቅረፅ፣ |

| የትኩረት መስኮች | ስትራቴጂክ ግቦች | ኢኒሼቲቮች እና ፕሮጀክቶች |
|---|---|---|
| የህግ ተገዢነት አመራር ልህቀት | 12. የስጋት ስራ አመራር አፈፃፀምን ማሻሻል<br>13. የታክስ ማጭበርበር እና የኮንትሮባንድ መከላከል አፈፃፀምን ማሻሻል<br>14. የታክስ ህግ ተገዢነትን አፈፃፀምን ማሻሻል | 32. የስጋት ስራ አመራር ማጠናከር፣<br>33. የኢንዱስትሪዎችን Input/ Output Coefficient ማዘጋጀት፣<br>34. የታክስ ኦዲት አሰራር ማሻሻል፣<br>35. የዋጋ ትልልፍ ኦዲት አቅምን ማጎልበት*፣<br>36. የታክስ ማጭበርበርን ለመለየትና ለመከላከል ስትራቴጂ መቅረፅና መተግበር፣<br>37. የታክስ ማበረታቻዎች አስተዳደር ስርዓት መዘርጋት፣<br>38. የተቀናጀ የኮንትሮባንድ ቁጥጥር ስርዓት መዘርጋት፣<br>39. የታክስ አጠቃላይ አገራዊ ፋይዳን በሀገሪቱ የትምህርት ሥርዓት ውስጥ ማካተት፣<br>40. የማህበረሰብ አቀፍ የግንዛቤ ማስጨበጫ ፕሮግራም በመዘርጋት መተግበር፣<br>41. አጠቃላይ የታክስ ጋይድላይን (Comprehensive Tax Guideline) ማዘጋጀት፣<br>42. የትምህርትና የተግባቦት ስትራቴጂ መቅረፅ እና መተግበር*፣<br>43. የግብር ፍትሃዊነትና ትብብር ፕሮጀክት ማጠናከር እና ማስፋት*፣<br>44. የደረሰኝ ሎተሪ ሽልማት ስርዓት መቅረፅ፣ |
| ዘላቂ የገቢ ዕድገት | 15. የገቢ አሰባሰብ ውጤታማነትን ማሻሻል | 45. የሀገሪቱን እምቅ የታክስ አቅም (Tax potential) እንዲጠና ማድረግ፣<br>46. የታክስ ፖሊሲ ማሻሻያ ጥናቶች ማከናወን (Tax base, rate, bracket, type) ፣<br>47. አዳዲስ ታክስ ከፋዮችን ወደ መረቡ ማስገባት፣ |

* ከ30 ሚሊዮን ብር በላይ ወጪ የሚጠይቁ ፕሮጀክቶች

# 6 የተጓዳኝ ተቋማት የትስስር ፍላጎት

ሚኒስቴር መ/ቤቱ የተሰጠዉን ሀገራዊ ኃላፊነት መወጣት እንዲያስችለዉ ከምንም ጊዜ በላይ በስትራቴጂክ ዘመኑ የላቀ ቅንጅታዊ ትስስር ከሃገር ዉስጥ ካሉ ተቋማት ጋር መፍጠር ይኖርበታል፡፡ የሚፈጠረዉም ቅንጅት ችግሮችን በጋራ በመፍታት በስትራቴጂክ ዘመኑ ለመድረስ የተቀመጠዉን ግብ ለማሳካት የሚረዳ ይሆናል፡፡ ስለሆነም ከተቋማት ጋር ተሚኖረዉን ቅንጅትና ትስስር የሚያሳይ ሰንጠረዥ እንደሚከተለዉ ቀርቧል፡፡

## 6.1 የተቋማት የትስስር ደረጃ

ሰንጠረዥ 13፡ የተቋማት የትስስር ደረጃ

| የመ/ቤቱ ስም | የትስስር ደረጃ | ምርመራ |
|---|---|---|
| 01. የገንዘብ ሚ/ር | 4 | |
| 02. የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ | 4 | |
| 03. ኢትዮ ቴሌኮም | 4 | |
| 04. የትራንስፖርት ሚ/ር | 4 | |
| 05. የኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ሚ/ር | 4 | |
| 06. የንግድ እና ኢንዱስትሪ ሚ/ር | 4 | |
| 07. የፌደራል ዓቃቤ ህግ | 4 | |
| 08. የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን | 4 | |
| 09. የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚ/ር | 4 | |
| 10. ሰላም ሚኒስቴር | 4 | |
| 11. ፕላንና ልማት ኮምሽን | 4 | |
| 12. የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚ/ር | 3 | |
| 13. ግብርና ሚ/ር | 3 | |
| 14. ትምህርት ሚኒስቴር | 3 | |
| 15. የወጪ ጉዳይ ሚኒስቴር | 3 | |
| 16. የማዕድንና ነዳጅ ሚ/ር | 3 | |
| 17. ጤና ሚኒስቴር | 3 | |
| 18. የዉሀ ምስኖና ኢነርጂ ሚ/ር | 2 | |
| 19. የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር | 2 | |
| 20. የሴቶች ህፃናትና ወጣቶች ሚኒስቴር | 2 | |
| 21. የሰራተኛና ማህበራዊ ሚኒስቴር | 2 | |

<u>ማስታወሻ</u>

1= ምንም ግንኙነት የሌለዉ፣
2= ዝቅተኛ ግንኙነት ያለዉ፣
3= መካከለኛ ግንኙነት ያለዉ እና
4= ከፍተኛ ግንኙነት ያለዉ።

## 6.2 ትስስር የሚፈለግባቸው ዋና ዋና ጉዳዮች

| የመ/ቤቱ ስም | 2013 — 2017 | 2018 — 2022 |
|---|---|---|
| 01.የገንዘብ ሚ/ር | • የታክስና የጉምሩክ አዋጆች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎች እና የታሪፍ ማሻሻያዎች በወቅቱ አዘጋጅቶ ማፀደቅ፣<br>• በተደራራቢ ታክስ ስምምነቶች ዙሪያ ፣ በዓመታዊ ዕቅድ እና በአድቫንስ ሩሊንግ (advance ruling) አብሮ መስራት | • የታክስና የጉምሩክ አዋጆች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎች እና የታሪፍ ማሻሻያዎች በወቅቱ አዘጋጅቶ ማፀደቅ እንዲሁም ማሻሻያ ማድረግ፣<br>• በተደራራቢ ታክስ ስምምነቶች ዙሪያ ፣ በዓመታዊ ዕቅድ እና በአድቫንስ ሩሊንግ (advance ruling) አብሮ መስራት |
| 02.የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ | • የታክስ ክፍያ በባንክ ለመፈፀም የሚያስችል መመሪያ ማዉጣት፣<br>• የታክስ ገቢ በወቅቱ ወደ መንግስት ካዝና የሚገባበትን አሰራር መዘርጋት፣<br>• የፍራንኮ ቫሉታ መመሪያዎችን ማዉጣት፣<br>• ከዋጋ በታችና ከዋጋ በላይ የሚካሄዱ ግብይቶችን ለመከላከል የሚያስችል የአሰራር ስርዓት መዘርጋት፣<br>• የገቢና የወጪ ንግዱ በፋይናንስ የሚደገፍበትን ስርዓት መዘርጋት፣ | |
| 03.ኢትዮ ቴሌኮም | • የቴሌኮም መሰረተ ልማት ዝርጋታ፣ የአገልግሎት አቅርቦት(ኢንተርኔት) እና ልዩ ድጋፍ ማድረግ፣<br>• ወደ ሀገር የሚገቡ የመገናኛ እቃዎች ፈጣን የጥራት ማረጋገጫ ፍቃድ መስጠት፣ | |
| 04.የትራንስፖርት ሚ/ር | • የአገሪቱ ሎጂስቲክስ ዘመናዊና ወጪ ቆጣቢ እንዲሆን የሚያደርግ ስርዓት መዘርጋት፣<br>• የደረቅ ወደቦችን ማስፋፋትና ያሉትም በዘመናዊ ግብዓቶች እንዲሟሉ ማድረግ፣<br>• ፈጣን የወጪና ገቢ ዕቃዎች የመረጃ ልዉዉጥ ስርዓት መዘርጋት፣<br>• በገቢና ወጪ እቃዎች ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎችን ለመከላከል የሚያስችል ስርዓት መዘርጋት፣<br>• የዕቃ አስተላላፊዎች የሚመሩበትን የአሰራር ስርዓት ማዘመን፣ | |

| የመ/ቤቱ ስም | 2013 — 2017 | 2018 — 2022 |
|---|---|---|
| 05.የኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ሚ/ር | • የታክስና የጉምሩክ አስተዳደር አገልግሎቶችን ዲጂታላይዝ ማድረግ፣<br>• የታክስና ጉምሩክ የመጠባበቂያ ዳታ ማዕከል መገንባት፣<br>• የታክስና የጉምሩክ የመረጃ ደህንነት የሚጠበቅበትን ስርዓት መዘርጋት፣<br>• የትልልቅ መረጃዎች ትንተና ስርዓት መዘርጋት፣<br>• በመረጃ ቴክኖሎጂ ዙሪያ የአቅም ግንባታ ድጋፍ መስጠት፣ | • በታክስና ጉምሩክ አስተዳደር ዉስጥ የአርተፊሺያል ኢንተለጀንስን ተግባራዊ ማድረግ፣ |
| 06.የንግድና ኢንዱስትሪ ሚ/ር | • የአንድ አለቅ (One Stop) የንግድ ምዝገባና የክሊራንስ አገልግሎት ስርዓት መዘርጋት፣<br>• ህገወጥ ንግድን በጋራ መከላከል፣<br>• የወጪና ገቢ ዕቃዎች በትክክለኛ ዋጋ ስለመሸጣቸዉ ወይም ስለመገዛታቸዉ ለማረጋገጥ የሚያስችል ስርዓት መዘርጋት፣<br>• የግበዓት ምርት ጥምርታ (Input Output Coefficient) ማዘጋጀት፣<br>• በወጪ እና ገቢ እቃዎች ላይ ፈጣን የደረጃ ማረጋገጫ የሚሰጥበትን ስርዓት መዘርጋት፣ | • የኤሌክትሮኒክስ ንግድ (e-Commerce) ስርዓት መዘርጋት፣ |
| 07.የፌዴራል ዓቃቤ ህግ | • የታክስ እና ጉምሩክ የወንጀል ጉዳዮች ላይ ፈጣን ክስ መመስረትና መከራከር፣<br>• በፍትሀብሄር ጉዳዮች ላይ ተቋሙን ማማከርና ክስ መመስረት፣ | • የታክስና ጉምሩክ ወንጀሎችን አስቀድሞ ለመከላከል የሚያስችል ስትራቴጂ መቅረፅ፣ |
| 08.የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን | • የአንድ አለቅ (One Stop) ኢንቨስትመንት ምዝጋባ ስርዓት መዘርጋት፣<br>• የኢንደስትሪ ፓርኮችን አሰራር ከታክስና ጉምሩክ የአሰራር ስርዓት ጋር የተጣጣመ ማድረግ፣<br>• በከፍተኛ ኢንቨስትመንት ላይ የተሰማሩ ባለሃብቶች ከታክስ አስተዳደሩ ጋር የተሳለጠ የመረጃ ልዉዉጥ ስርዓት መዘርጋት፣<br>• በኢንቨስትመንት ስም የገቡ የካፒታል ዕቃዎች ለታለመላቸዉ ዓላማ ስለመዋላቸዉ መከታተል የሚያስችል የአሰራር ስርዓት መዘርጋት፣ | • ኦንላይን የኢንቨስትመንት ምዝገባና መረጃ ልዉዉጥ ስርዓት መቅረፅና መተግበር፣ |
| 09.የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚ/ር | • ከኮንስትራክሽን ስራዎች ጋር የተያያዙ የንግድ ስራ ሀብቶች ፈጣን የመረጃ ልዉዉጥ ስርዓት መዘርጋት፣<br>• የኮንስትራክሽን የንግድ ስራ ሀብቶች የገበያ ዋጋ | • ኦንላይን የኮንስትራክሽን ንግድ ስራ ሀብቶች መረጃ ልዉዉጥ ስርዓት መዘርጋት፣ |

| የመ/ቤቱ ስም | 2013 — 2017 | 2018 — 2022 |
|---|---|---|
| | ግምት መረጃ ስርዓት መዘርጋት፣ | |
| 10.ሰላም ሚኒስቴር | • ፈጣን የታክስና የጉምሩክ ወንጀሎች ምርመራ ስርዓት መዘርጋት፣<br>• በኮንትሮባንድ ንግድ ላይ የተሰማሩ ወንጀለኞች ላይ ፈጣን የመከላከል ዕርምጃ መዉሰድ፣<br>• የታክስ ማጭበርበር፣ የኮንትሮባንድና የህገ-ወጥ ንግድ የመረጃ ልዉዉጥ ስርዓት መዘርጋት፣<br>• ብሄራዊ የመታወቂያ ስርዓት መተግበር፣<br>• ወደ ሀገር የሚገቡ የመገናኛ መሳሪያዎች ፈቃድ አሰጣጥ ስርዓት ማጠናከር፣ | • የታክስና ጉምሩክ ወንጀሎችን አስቀድሞ ለመከላከል የሚያስችል ስትራቴጂ መቅረፅ፣<br>• ኦንላይን የታክስና ጉምሩክ ወንጀሎች መረጃ ልዉዉጥ ስርዓት መዘርጋት፣ |
| 11.የፕላንና ልማት ኮሚሽን | • የማክሮ ኢኮኖሚ ማዕቀፍ ፈጣን የመረጃ ልዉዉጥ ስርዓት መዘርጋት፣ | • ኦንላይን የማክሮ ኢኮኖሚ መረጃዎች ልዉዉጥ ስርዓት መዘርጋት፣ |
| 12.የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚ/ር | • ተቋሙ በሚፈልጋቸዉ የሙያ መስኮች የሰለጠነ የሰዉ ኃይል ማፍራት፣<br>• በታክስና ጉምሩክ አስተዳደር ዙሪያ ገቢራዊ ጥናቶችን ማካሄድ፣<br>• የታክስና ጉምሩክ ጉዳይ በከፍተኛ ትምህርት ስርዓት ውስጥ ማካተት፣<br>• የማማከርና የቴክኒክ ድጋፍ መስጠት፣<br>• የከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራት ችግሮችን ለመቅረፍ ስትራቴጂ ቀርፆ መተገበር፣ | • በከፍተኛ ደረጃ የሰለጠነ የሰዉ ኃይል ማቅረብ፣ |
| 13.ግብርና ሚ/ር | • የገቢና የወጪ የእንስሳት ኳራንቲን አገልግሎት አሰጣጥ ስርዓት መዘርጋት፣<br>• ከግብርና ጋር ለተያያዙ ገቢ ዕቃዎች ፈጣን የሙያ ድጋፍ አገልግሎት መስጠት፣<br>• ለኮንትሮባንድ መከላከል ስራ ትብብር ማድረግ፣ | |
| 14.ትምህርት ሚኒስቴር | • የታክስና ጉምሩክ ጉዳይ በትምህርት ስርዓት ውስጥ ማካተት፣ | |
| 15.የውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር | • በታክስና ጉምሩክ አስተዳደር ዙሪያ የቴክኒክ፣ የአቅም ግንባታ እና የመረጃ ድጋፍ የሚሰጡ የዉጪ አጋር አካላትን ማስተባበር፣<br>• በዉጪ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን እና ትዉልደ ኢትዮጵያዊያን የዉጪ ዜጎች በተቀላጠፈ ሁኔታ የግብር ከፋዮች ምዝገባ እንዲያገኙ ድጋፍ መስጠትና በታክስና ጉምሩክ ዙሪያ ግንዛቤያቸዉን ማሳደግ፣<br>• የዉጪ ኢንቨስተሮች በታክስ ዙሪያ የሚያጋጥማቸዉን ችግሮች በጋራ መፍታት፣ | • ከዉጪ ግንኙነት ጋር የተያያዙ ኦንላይን የመረጃ ልዉዉጥ በስራ ላይ ማዋል፣ |

| የመ/ቤቱ ስም | 2013 — 2017 | 2018 — 2022 |
|---|---|---|
| | • ሀገሪቱ ከፍተኛ የንግድ ልዉዉጥ ከምታካሂድባቸዉ ሀገሮች ጋር የጉምሩክ አታሼ አገልግሎት ድጋፍ መስጠት፣<br>• የቀረጥ ነፃ መብት ያላቸዉ የዲፕሎማቲክ ማህበረሰብ የቀረጥ ነፃ ድጋፍ እና ክሊራንስ አሰጣጥ ስርዓቱን ማጠናከር፣<br>• በዓለም ዓቀፍ መንግስታዊ ድርጅቶች እና ኤምባሲዎች ተቀጥረዉ የሚሰሩ ኢትዮጵያዊያን ግለሰቦችና ድርጅቶች የታክስ ግዴታቸዉን እንዲወጡ የሚያስችል ድጋፍ መስጠት፣<br>• ያለመፈተሽ መብት ያላቸዉ የዲፕሎማቲክ አካላት የጉምሩክን ህጎች አክብረዉ እንዲንቀሳቀሱ ግንዛቤ እንዲኖራቸዉ ማድረግ፣ | |
| 16.የማዕድንና ነዳጅ ሚ/ር | • የማዕድን ኮንትሮባንድን በጋራ መከላከል የሚያስችል ስትራቴጂ ቀርጾ መተግበር፣<br>• በማዕድን ዘርፍ የተሰማሩ ባለሀብቶች ከታክስና ከቀረጥ ነፃ ጋር የተያያዙ መረጃዎች ልዉዉጥ ስርዓት መዘርጋት፣<br>• የማዕድን የንግድ ስራ ሀብቶች መረጃ ልዉዉጥ ስርዓት መዘርጋት፣ | • ከማዕድን ስራዎች ጋር የተያያዙ ኦንላይን የመረጃ ልዉዉጥ ስርዓት መዘርጋትና መተግበር፣ |
| 17.ጤና ሚኒስቴር | • በገቢና የወጪ የምግብና የመድሃኒት ዕቃዎች ላይ ፈጣን የጥራት ማረጋገጫ ስርዓት መዘርጋት፣<br>• ከዉጪ የሚገቡ መድሀኒት እና የህክምና መገልገያ ዕቃዎች በፍጥነት ከደረቅ ወደብ የሚወጡበትን አሰራር ተግባራዊ ማድረግ፣ | |
| 18.የዉሃ መስኖና ኢነርጂ ሚ/ር | • በጠረፋማ አካባቢዎች የገቢና ወጪ ትራንዚት አገልግሎትን ለማሳላጥ አስተማማኝ የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት እንዲያገኙ ድጋፍ መስጠት፣ | |
| 19.የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር | • በጊዜያዊነት በቱሪስት መልክ ሀገር ዉስጥ የሚገቡ እቃዎች ተመልሰዉ እንዲወጡ ተገቢዉን ትብብር ማድረግ፣<br>• የሀገሪቱ ቅርሶች በህገወጥ መንገድ ከሀገር እንዳይወጡ ተገቢዉን ድጋፍ መስጠት፣ | • ኦንላይን የመረጃ ልዉዉጥ ስርዓት መዘርጋት፣ |
| 20.የሴቶች ህፃናትና ወጣቶች ሚኒስቴር | • ሀገራዊ የስርዓተ ፆታ ማካተቻ ጋይድላይን በወቅቱ ማዘጋጀት፣<br>• ሴቶችን ወደ አመራር ማምጣት የሚያስችሉ የተለያዩ የአቅም ግንባታ ስልጠናዎችን | |

| የመ/ቤቱ ስም | 2013 — 2017 | 2018 — 2022 |
|---|---|---|
| | መስጠት፣ | |
| 21.የሰራተኛና ማህበራዊ ሚኒስቴር | • የኮርፖሬት /ፐብሊክ/ ማህበራዊ ኃላፊነትን ለመወጣት የሚያስችል ፖሊሲ እና ስትራቴጂ መቅረፅ፣<br>• ለውጭ ሀገር ዜጋ ለሆኑ ታክስ ከፋዮች የስራ እና የመኖሪያ ፍቃድ ማመቻቸት፣ | |

# 7 ስጋቶች እና የመፍትሄ ሃሳቦች

ሚኒስትር መ/ቤቱ የአምስት ዓመት ስትራቴጂያዊ ዕቅድ ለመፈፀም በሚያደርገዉ እንቅስቃሴ የተለያዩ ዉስጣዊና ዉጪያዊ ተግዳሮቶች እንደሚገጥሙ ይጠበቃል፡፡ ከነዚህም ዉስጥ ዓለማቀፋዊና አህጉራዊ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ፣ የግብር ከፋዩ ለግብር ያለዉ አመለካከት እና የተቋሙ አጠቃላይ የአገልግሎት አሰጣጥ ሁኔታ ተጠቃሽ ናቸዉ፡፡ ለዚህም ተቋሙ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ስጋቶችና ስጋቶችን ለመቀነስ ሊወስዳቸዉ የሚገቡ ዕርምጃዎች እንደሚከተለዉ ተቀምጧል፡፡

ሰንጠረዥ 14፡ ስጋቶች እና የመፍትሄ ሀሳቦች

| ስጋቶች | መግለጫ | የመፍትሄ እርምጃዎች |
|---|---|---|
| የማክሮ ኢኮኖሚ ተጽዕኖዎች፣ | • የዓለም ኢኮኖሚ መለዋወጥ በሀገራዊ የማክሮ ኢኮኖሚ ላይ የሚንፀባረቅና ይህም በገቢ አሰባሰቡ ላይ ተፅዕኖ ሊያሳድር የሚችል መሆኑ፣ | • በታክስ አስተዳደሩ ላይ የሚከሰቱ ተፅዕኖዎችን ከሚመለከታቸዉ አካላት ጋር በመቀናጀት ዕርምጃ እንዲወሰድ ማድረግ፣ |
| የህቡዕ ኢኮኖሚ እንቅስቃሴ | • በህጋዊ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ዉስጥ ሳይታቀፉ በህገወጥ ንግድ፣ ኮንትሮባንድ፣ በህገወጥ የገንዘብ ዝዉዉር፣ አራጣ ብድር፣ በህገወጥ ደረሰኝ እና በመሳሰሉት ተግባራት ላይ በመሳተፍ በመንግስት ገቢ፣ በህጋዊ ንግድ እና በሀገር ደህንነት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ህቡዕ እንቅስቃሴዎች መኖርና ወደፊትም ችግሩ ሊቀጥል የሚችል መሆኑ፣ | • ህቡዕ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴን ለመከላከል የሚያስችል የትምህርት ስትራቴጂ ነድፎ መተግበር፣<br>• ባለድርሻ አካላትን ያካተተ ቀጣይነት ያለዉ የኮንትሮባንድ መከላከል ስትራቴጂ ነድፎ መተግበር፣<br>• የንግድ ልዉዉጦች የባንክ ስርዓትን ተከትለዉ እንዲሄዱ ማድረግ፣<br>• የአምራችና አስመጪዎች የግብይት ሰንሰለት በመረጃ ቴክኖሎጂ ተደግፎ እንዲከናወን ማድረግ፣<br>• ህገወጥ የገንዘብ እንቅስቃሴን ለመግታት የሚያስችል ስትራቴጂ መቅረፅና መተግበር፣<br>• ከድርጊታቸዉ በማይታረሙ ዋና ዋና ተዋናዮች ላይ የማያዳግምና አስተማሪ የሆነ ህጋዊ እርምጃዎችን መዉሰድ፣ |
| የህግ ተገዥነት በተሟላ ሁኔታ አለማረጋገጥ | • ከግብይት ዋጋ በታችና በላይ ማቅረብ፣ ዋጋ ማሸጋገር፣ ያልተገባ ተመላሽ መጠየቅ፣ ከህግ ዉጪ | • የህግ ተገዢነት ማረጋገጫ ስትራቴጂ ቀርፆ መተግበር፣<br>• የተቋሙን የህግ ማስከበር አቅም |

| ስጋቶች | መግለጫ | የመፍትሄ እርምጃዎች |
|---|---|---|
| | ማሳወቅ ያቆሙ፣ ባዶ፣ ኪሳራና ተመላሽ ማሳወቅ ሊቀጥል የሚችል መሆኑ፣ | ማጠናከር፣<br>• ከባለድርሻ አካላት ጋር ያለዉን ቅንጅት በማጠናከር ህገወጥነትን መከላከል፣ |
| የማስፈፀም አቅም ውስንነት | • የአመራሩ እና የፈፃሚ የተያዘውን ዕቅድ በብቃት፣ በጊዜ እና በጥራት የማስፈፀም አቅም ክፍተት ሊያጋጥም የሚችል መሆኑ፣ | • ተቋማዊ የሆነ እና በስትራቴጂ የሚመራ ተከታታይነት ያለው የአቅም ግንባታ ስራ ማከናወን፣ |
| ዲጅታል የታክስ አስተዳደር ስርዓት አለመረጋገጥ | • የሀገሪቱን የታክስ አስተዳደር ስርዓት ዓለም ወደ ደረሰበት የመረጃ ቴክኖሎጂ ዕድገት ለማሸጋገር የሚያስችል የተቋማዊ አቅም እጥረት ሊያጋጥም መቻል፣ | • የዲጅታል ቴክኖሎጂ ስትራቴጂ መቅረፅና መተግበር፣ |
| ቅንጅታዊ አሰራር አለመረጋገጥ | • ከሀገር ዉስጥና ከዉጪ አጋር አካላት ጋር የሚጠበቀዉ ቅንጅታዊ አሰራር በሚጠበቀዉ ደረጃ ተግባራዊ ሊደረግ አለመቻሉ፣ | • ጠንካራ የቅንጅት ስትራቴጂ ቀርፆ መተግበር፣ |
| የሙስና ተጋላጭነት | • ዘርፉ ከዉስጥና ከዉጪ ለሙስና ተጋላጭ መሆኑ፣ | • አሳታፊና ጠንካራ የሙስና መከላከል ስትራቴጂ ቀርፆ መተግበር፣ |
| የኮሮና ወረርሽኝ ተፅዕኖ | • የኮሮና ቫይረስ ወረርሽኝ በሚቀጥሉት አመታት ከቀጠለ በኢኮኖሚ ፣ በንግድ ስርአቱ እና ታክስ አስተዳደር ስርአቱ ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድር መሆኑ | • ከነባራዊ ሁኔታ ጋር የተጣጣመ አመራር መስጠት<br>• የሰራተኞች እና ተገልጋዮች ደህንነትን ማረጋገጥ<br>• አገልግሎቶችን በቴክኖሎጂ ማስደገፍ |

# 8 የክትትልና ግምገማ ስርዓት

ይህ የገቢዉ ዘርፍ የመካከለኛ ዘመን (የአምስት ዓመት) እቅድ ሲተገበር በዋናነት የተቋሙ የበላይ አመራር በባለቤትነት የሚመራዉ ሲሆን ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ተጠሪ የሆኑ ተቋማት በዚህ እቅድ ላይ መሰረት በማድረግ የየዘርፋቸዉን እቅድ የሚያዘጋጁና ለበላይ አመራሩ የሚያስተዋዉቁ ይሆናል፡፡ በመቀጠልም በአምስት ዓመት እቅድ ላይ መሰረት ያደረገና በዚህ ዓመስት ዓመት እቅድ ዉስጥ በቀጣይ አምስት ዓመታት ሊተገበሩ የተያዙ ጉዳዮችንና እነዚህን ተግባራት እዉን በማድረግ በአምስት ዓመት ሊደረስበት የተያዘን ግብ ሊያሳካ በሚችል መልኩ የየዓመቱ እቅድ እየተዘጋጀ ለተቋሙ ማህበረሰብ የሚተዋወቅና በዚህ ልክ ወደፈፃሚ አካላት የሚወርድ ይሆናል፡፡ ለዚህም ይረዳ ዘንድ ጠንካራ የስትራቴጂ እቅድ ትግበራ ክትትል የስራ ክፍል በየደረጃዉ በማጠናከር አፈፃፀሙን ይከታተላል፣ ይገመግማል፣ ግብረ መልስ ይሰጣል፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ተገቢዉን የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፡፡ የዘርፉ እቅድ ከአገራዊ የብልጽግና እቅድ ጋር የተሳሰረ በመሆኑ ተቋሙ አፈፃፀሙን በየጊዜዉ እየገመገመ ጥራት ያለዉ ሪፖርት በተጠያቂነት መንፈስ ወቅቱን ጠብቆ ለሚመለከታቸዉ ተቆጣጣሪ አካላት ያቀርባል በሚሰጠዉ ግብረ መልስ መሰረት አስፈላጊዉን ማስተካከያ ያደርጋል፡፡

በዚህ አግባብ ዘርፎችና ቅ/ጽ/ቤቶች የራሳቸዉን እቅድ በማዘጋጀት ስራዎችን ስትራቴጂክ በሆነ አግባብ ይመራሉ ይከታተላሉ፣ ስራዎች የሚጠበቀዉን ዉጤት ማምጣታቸዉን ይገመግማሉ ለበላይ አካል የአፈፃፀም ሪፖርት በማቅረብ ያስገመግማሉ በሚሰጣቸዉ ግብረመልስ መሰረት አስፈላጊዉን ማስተካከያ ያደርጋሉ፡፡

## 8.1 የዕሴት መግለጫዎች

1. **አገልጋይነት፡-** ማለት ራስን ለሌሎች መስጠት ማለት ሲሆን ተገልጋዮችን በታማኝነት፣ በተጠያቂነት እና በጥራት ያለአድልዎ ማስተናገድ ማለት ነው፡፡ በተጨማሪም ለሚቀርቡ ቅሬታዎችና አቤቱታዎች ፈጣንና ተገቢ ምላሽ መስጠት፣ ተጨባጭ ምክንያት ካልተገኘ በስተቀር በተገልጋዮች ላይ ሙሉ እምነት ማሳደር እንዲሁም ሙሉ ትኩረቱ የደንበኞችን ፍላጎት ማሟላት እንደመሆኑ መጠን ከደንበኞች ጋር ቋሚ ምክክር ማድረግ ነው፡፡
2. **መስጠት፡-** ከቁርጠኝነት ጋር ተመሳሳይ ሲሆን የገቡትን ቃል ሳይሸራረፍ እንደውም ከሚጠበቀውም በላይ ተግባራዊ ማድረግ ማለት ነው፡፡ አገልግሎት የሚሻሻለው ተሰጥዎ ባላቸው አመራሮችና ሠራተኞች

ጥረት ነው፡፡ መሰጠት ካለ መፍጠር ማሻሻል ከመቻሉም በላይ ችግር ሲያጋጥምም ተስፋ አለመቁረጥ ማለት ነው፡፡

3. **ሙያዊ ብቃት ፡-** ኃላፊነትን፣ ቅንነትን እና ተጠያቂነትን እና የላቀ የሆነ ሥራን አጣምሮ የያዘ እና በእሴቱ ላይ በፍጹም የማይደራደር ባለሙያ ማለት ነው፡፡ መያዊ ብቃት ያለው አመራርም ይሁን ፈጻሚ ሁልጊዜም ቢሆን ዝግጁ የሆነ ሲሆን ቅድሚያ ያቅዳል፣ ጊዜ ይወስናል፣ ትኩረት አድርጎ ይሰራሉ፣ በመጨረሻም በየጊዜው ዕቅዱን እየገመገመ እና እያሻሻለ የሚሄድ ማለት ነው፡፡

4. **ታማኝነት፡-** ማለት የገቡትን ቃል ኪዳን መጠበቅ፣ ህጎችን፣ ደንቦችና መመሪያዎችን ሳያዛንፉ ተግባራዊ ማድርግ ማለት ነው፡፡ ለሀገርና ለህገመንግስት ታማኝ መሆን፣ ቃል ለገቡትና ለተስማሙበት የሥነምግባር ደንብ ተገዥ መሆን፣ የመንግሥትን ሃብት በጥንቃቄና ለተፈቀደው ተግባር ብቻ ማዋል፡ ሕገ ወጥ ተግባር ሲፈፀም አግባብ ላለው ኃላፊ ማሳወቅ በመጨረሻም በስራው አማካኝነት ያገኘውን የተቋሙን መረጃ ለማይገባው ሰው አሳልፎ አለመስጠት ማለት ነው፡፡

5. **በቡድን መስራት፡-** አስቀድሞ ዓላማን ማጋራት እና መግባባት ላይ መድረስ፣ የሌሎችን ሀሳብና ዕውቀት ማክበርና ማዳመጥ፣ በጋራ ችግሮችን መፍታት፣ ሥራን ተጋግዞ በቅንጅት መስራት፣ መተማመንና በግልፅ መነጋገር፣ ኃላፊነትን በጋራ መውሰድ፣ ዕውቀትን፣ መረጃና ልምድን ማካፈል /መለዋወጥ/መማማር፣ ጤናማ የሆነ የቡድን መንፈስ መፍጠር ነው፡፡

# 9 የሰው ሀብት እና የፋይናንስ ፍላጎት

## 9.1 የሰው ሀብት ፍላጎት[3]

የተቋሙን የአምስት ዓመት ዕቅድ ለማሳካት በየዓመቱ የሚያስፈልግ የሰዉ ኃይል ትንበያ በሚከተለዉ ሰንጠረዥ መሰረት ቀርቧል፡፡

ሰንጠረዥ 15፡ የተጠቃለለ የሰው ሀብት ፍላጎት

| | (መነሻ)2012 | መድረሻ (2017) | 2013 | 2014 | 2015 | 2016 | 2017 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ምርታማነት (በሰው የሚሰበሰብ ገቢ በሚሊዮን ብር) | 18 | 37 | 20 | 22 | 25 | 30 | 37 |
| የሰው ሀብት ፍላጎት | | | | | | | |
| ገቢዎች ሚ/ር | 4,013 | 5,899 | 4,696 | 5,237 | 5,910 | 5,861 | 5,899 |
| ጉምሩክ ኮሚሽን | 6,716 | 14,428 | 9,619 | 12,023 | 12,825 | 13,626 | 14,428 |
| ሎተሪ | 885 | 1,301 | 1,036 | 1,155 | 1,303 | 1,292 | 1,301 |
| ድምር | 11,614 | 21,629 | 15,350 | 18,416 | 20,039 | 20,779 | 21,629 |

[3] የተቀረፀው የሰው ሀብት ስትራቴጂ ፣ የቢዝነስ ፕሮሰስ ትራንስፎርሜሽን እና ቴክኖሎጂ ለውጦች የሰው ሀይል ትንበያውን ሊቀይሩ ይችላሉ።

## 9.2 የፋይናንስ ፍላጎት

ተቋሙ የአምስት ዓመት ዕቅዱን ለመተግበር የሚያስችል የመደበኛ፣ የካፒታል እና የስትራቴጂክ እርምጃዎች ማስፈፀሚያ የሚዉል የበጀት ፍላጎት በሚከተለዉ ሰንጠረዥ መሰረት ቀርቧል፡፡

ሰንጠረዥ 16፡ የ5 ዓመት የፋይናንስ ፍላጎት በቢሊዮን ብር

| ተ.ቁ | ዝርዝር | መነሻ ዓመት | ትንበያ (Projection) | | | | | የ5 ዓመት ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 2012 | 2013 | 2014 | 2015 | 2016 | 2017 | |
| 1 | ጠቅላላ ወጪ (1.1 + 1.2 + 1.3) | 3.5 | 14.48 | 11.65 | 8.57 | 13.21 | 13.94 | 61.85 |
| 1.1 | የካፒታል በጀት | 0.3 | 5.52 | 3.23 | 0.9 | 0.4 | 1.05 | 11.1 |
| 1.2 | የመደበኛ ወጪ | 3.2 | 4.66 | 5.13 | 6.07 | 11.69 | 12.32 | 39.87 |
| 1.3 | ስትራቴጂክ እርምጃ ማስፈፀሚያ በጀት | 0 | 4.3 | 3.29 | 1.6 | 1.12 | 0.57 | 10.88 |
| 2 | የውጭ ምንዛሬ ፍላጎት ከጠቅላላ ወጪ በሚሊዮን አሜሪካን ዶላር | 11 | 37 | 28 | 22 | 40 | 45 | 172 |
| 3 | የፋይናንስ ምንጭ በቢሊዮን ብር | 3.5 | 14.48 | 11.65 | 8.57 | 13.21 | 13.94 | 61.85 |
| 3.1 | ከመንግስት በጀት | 3.5 | 14.48 | 11.65 | 8.57 | 13.21 | 13.94 | 61.85 |

# 10 ዕዝሎች

## 10.1የአምስት ዓመት የወጪ ፍላጎት (በቢሊዮን ብር)

### 10.1.1 የስትራቴጂክ ዕርምጃዎች ማስፈፀሚያ የበጀት ፍላጎት

ሰንጠረዥ 17: የስትራቴጂክ ዕርምጃዎች ማስፈፀሚያ በጀት

| ኢኒሼቲቮች እና ፕሮጀክቶች | ዓመት | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | 2013 | 2014 | 2015 | 2016 | 2017 | ድምር |
| የፈፃሚ እና አመራር ብቃትን ማሳደግ | 165.1 | 165.1 | 162.1 | 162.1 | 162.1 | 816.50 |
| የታክስ እና የጉምሩክ ስልጠና ማዕከልን አቅም መገንባት | 300.1 | 240.1 | 75.0 | 15.0 | 15.0 | 645.20 |
| ምቹ የሆነ የስራ ከባቢ መፍጠር | 1,980.7 | 1,950.7 | 900.3 | 540.2 | - | 5,371.90 |
| ዲጂታል የታክስ እና የጉምሩክ አስተዳደር መዘርጋት* | 1,453.5 | 532.7 | 66.0 | 66.0 | 66.0 | 2,184.20 |
| የታክስ kiosks እና Tax Clinic ፕሮግራም መዘርጋትና መተግበር | 25.5 | 19.5 | 19.5 | 19.5 | 19.5 | 103.50 |
| የስራ ሂደቶች ማሻሻያ (Transformation) መቅረፅና መተግበር | 30.0 | 30.0 | - | - | - | 60.00 |
| ከአዋሳኝ ሀገሮች ጋር የአንድ አለቅ (One Stop Board Post) ፕሮጀክቶችን ማጠናቀቅ | 90.0 | 90.0 | 90.0 | 90.0 | 90.0 | 450.00 |
| የዋጋ ትልልፍ ኦዲት አቅምን ማጎልበት | 60.0 | 60.0 | 60.0 | - | - | 180.00 |
| የትምህርትና የተግባቦት ስትራቴጂ መቅረፅ | 150.1 | 150.1 | 150.1 | 150.1 | 150.1 | 750.50 |
| የግብር ፍትሃዊነትና ትብብር ፕሮጀክት መጀመር* | 45.0 | 49.5 | 54.5 | 59.9 | 65.9 | 274.80 |
| ከዉጪ አጋር አካላት ጋር የመረጃ ልዉዉጥ ስርዓት መቅረፅ | - | - | 25.0 | - | - | 25.00 |

| ኢኒሼቲቮች እና ፕሮጀክቶች | ዓመት | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | 2013 | 2014 | 2015 | 2016 | 2017 | ድምር |
| የዳታ ሞዴሊንግ እና የቢግ ዳታ አናሊሲስ ስርዓት መዘርጋት | - | - | - | 20.0 | - | 20.00 |
| ድምር | 4,300 | 3,287.7 | 1,602.5 | 1,22.8 | 568.6 | 10,881.30 |

### 10.1.2 የሀገር ዉስጥ ታክስ የካፒታል በጀት ፍላጎት እቅድ

ሰንጠረዥ 18፡ የአገር ዉስጥ ታክስ የካፒታል በጀት እቅድ

| ተ. ቁ | ነባር ፕሮጀክቶች (on-going projects) | የፕሮጀክቱ ባለቤት | ፕሮጀክቱ የሚካሄድበት ቦታ | የተጀመረበት ጊዜ | የሚጠናቀቅበት ጊዜ | የተመደበለት ካፒታል በቢሊዮን ብር |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የአዳማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ህንፃና ተያያዥ ስራዎች ግንባታ | ገቢዎች ሚኒስቴር | አዳማ ከተማ | የካቲት 21/2010 | የካቲት 29/2012 | 0.09 |
| 2 | የሀዋሳ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ህንፃና ተያያዥ ስራዎች ግንባታ | ገቢዎች ሚኒስቴር | ሀዋሳ ከተማ | ጥር 24/2010 | ሰኔ 30/2012 | 0.11 |
| ጠቅላላ ካፒታል (በሚሊዮን ብር) | | | | | | 0.192 |
| ተ. ቁ | አዲስ ወደ ትግበራ የሚገቡ ፕሮጀክቶች | የፕሮጀክቱ ባለቤት[1] | የሚተገበርበት ቦታ | የሚጀመርበት ጊዜ | የሚጠናቀቅበት ጊዜ | የተመደበለት ካፒታል |
| 1 | የባህር ዳር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ህንፃና ተያያዥ ስራዎች ግንባታ | ገቢዎች ሚኒስቴር | ባህር ዳር | የካቲት 1/2012 | ሐምሌ 30/2014 | 0.36 |
| 2 | የመቀሌ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ህንፃና ተያያዥ ስራዎች ግንባታ | ገቢዎች ሚኒስቴር | መቀሌ | የካቲት 1/2012 | ሐምሌ 30/2014 | 0.38 |
| 3 | የከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ህንፃና ተያያዥ ስራዎች ግንባታ | ገቢዎች ሚኒስቴር | አዲስ አበባ | ጥቅምት 01/2014 | መስከረም 30/2016 | 0.48 |
| 4 | የመካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ህንፃና ተያያዥ ስራዎች ግንባታ | ገቢዎች ሚኒስቴር | አዲስ አበባ | ጥቅምት 01/2014 | መጋቢት 30/2016 | 0.45 |
| 5 | የምስራቅ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ህንሣና ተያያዥ | ገቢዎች ሚኒስቴር | አዲስ አበባ | ጥቅምት 01/2014 | መጋቢት 30/2016 | 0.45 |
| 6 | የመረጃ ቴክኖሎጂ ማዕከል ግንበታ | ገቢዎች ሚኒስቴር | አዲስ አበባ | ጥቅምት | መጋቢት 30/2016 | 0.50 |

| ተ. ቁ | ነባር ፕሮጀክቶች (on-going projects) | የፕሮጀክቱ ባለቤት | ፕሮጀክቱ የሚካሄድበት ቦታ | የተጀመረበት ጊዜ | የሚጠናቀቅበት ጊዜ | የተመደበለት ካፒታል በቢሊዮን ብር |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | 01/2014 | | |
| 7 | ኮምቦልቻ ቅ/ጽ/ቤት ህንፃ ግንባታ | ገቢዎች ሚኒስቴር | ኮምቦልቻ | ጥቅምት 01/2015 | መጋቢት 30/2017 | 0.40 |
| 8 | ድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት ህንፃ ግንባታ | ገቢዎች ሚኒስቴር | ድሬዳዋ | ጥቅምት 01/2015 | መጋቢት 30/2017 | 0.40 |
| 9 | ጅግጅጋ ታክስ ማዕከል ግንባታ | ገቢዎች ሚኒስቴር | ጅግጅጋ (ሶማሌ) | ጥቅምት 01/2016 | መጋቢት 30/2018 | 0.40 |
| 10 | አሶሳ ታክስ ማዕከል ግንባታ | ገቢዎች ሚኒስቴር | አሶሳ (ቤንሻንጉል ጉምዝ) | ጥቅምት 01/2017 | መጋቢት 30/2019 | 0.35 |
| 11 | ጋምቤላ ታክስ ማዕከል ግንባታ | ገቢዎች ሚኒስቴር | ጋምቤላ (ጋምቤላ) | ጥቅምት 01/2017 | መጋቢት 30/2019 | 0.35 |
| 12 | ሰመራ ታክስ ማዕከል ግንባታ | ገቢዎች ሚኒስቴር | ሰመራ (አፋር) | ጥቅምት 01/2017 | መጋቢት 30/2019 | 0.35 |
| 13 | ሁመራ ታክስ ማዕከል ግንባታ | ገቢዎች ሚኒስቴር | ሁመራ (ትግራይ) | ጥቅምት 01/2018 | መስከረም 30/2020 | 0.10 |
| 14 | ሚዛን ተፈሪ ታክስ ማዕከል ግንባታ | ገቢዎች ሚኒስቴር | ሚዛን ተፈሪ (ደቡብ) | ጥቅምት 01/2018 | መስከረም 30/2020 | 0.10 |
| 15 | ወልዲያ ታክስ ማዕከል ግንባታ | ገቢዎች ሚኒስቴር | ወልዲያ (አማራ) | ጥቅምት 01/2019 | መስከረም 30/2021 | 0.10 |
| 16 | እንጅባራ ታክስ ማዕከል ግንባታ | ገቢዎች ሚኒስቴር | እንጅባራ(አማራ) | ጥቅምት 01/2019 | መስከረም 30/2021 | 0.10 |
| 17 | ሮቤ ታክስ ማዕከል ግንባታ | ገቢዎች ሚኒስቴር | ሮቤ(ኦሮሚያ) | ጥቅምት 01/2019 | መስከረም 30/2021 | 0.10 |
| 18 | ዲላ ታክስ ማዕከል ግንባታ | ገቢዎች ሚኒስቴር | ዲላ(ደቡብ) | ጥቅምት 01/2019 | መስከረም 30/2021 | 0.10 |
| 19 | ወላይታ ታክስ ማዕከል ግንባታ | ገቢዎች ሚኒስቴር | ወላይታ ሶዶ (ደቡብ) | ጥቅምት 01/2019 | መስከረም 30/2021 | 0.10 |
| 20 | አርባምንጭ ታክስ ማዕከል ግንባታ | ገቢዎች ሚኒስቴር | አርባምንጭ(ደቡብ) | ጥቅምት | መስከረም 30/2021 | 0.10 |

| ተ. ቁ | ነባር ፕሮጀክቶች (on-going projects) | የፕሮጀክቱ ባለቤት | ፕሮጀክቱ የሚካሄድበት ቦታ | የተጀመረበት ጊዜ | የሚጠናቀቅበት ጊዜ | የተመደበለት ካፒታል በቢሊዮን ብር |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | 01/2019 | | |
| 21 | ወልቂጤ ታክስ ማዕከል ግንባታ | ገቢዎች ሚኒስቴር | ወልቂጤ(ደቡብ) | ጥቅምት 01/2019 | መስከረም 30/2021 | 0.10 |
| 22 | ሆሳዕና ታክስ ማዕከል ግንባታ | ገቢዎች ሚኒስቴር | ሆሳዕና (ደቡብ) | ጥቅምት 01/2019 | መስከረም 30/2021 | 0.10 |
| 23 | ነቀምት ታክስ ማዕከል ግንባታ | ገቢዎች ሚኒስቴር | ነቀምት(ኦሮሚያ) | ጥቅምት 01/2019 | መስከረም 30/2021 | 0.10 |
| 24 | ሽሬ ታክስ ማዕከል ግንባታ | ገቢዎች ሚኒስቴር | ሽሬ(ትግራይ) | ጥቅምት 01/2019 | መስከረም 30/2021 | 0.10 |
| 25 | አክሱም ታክስ ማዕከል ግንባታ | ገቢዎች ሚኒስቴር | አክሱም(ትግራይ) | ጥቅምት 01/2019 | መስከረም 30/2021 | 0.10 |
| 26 | ደብረብርሃን ታክስ ማዕከል ግንባታ | ገቢዎች ሚኒስቴር | ደብረብርሃን (አማራ) | ጥቅምት 01/2019 | መስከረም 30/2021 | 0.10 |
| 27 | ደብረማርቆስ ታክስ ማዕከል ግንባታ | ገቢዎች ሚኒስቴር | ደብረማርቆስ (አማራ) | ጥቅምት 01/2019 | መስከረም 30/2021 | 0.10 |
| 28 | ቦሾፍቱ ታክስ ማዕከል ግንባታ | ገቢዎች ሚኒስቴር | ቦሾፍቱ(ኦሮሚያ) | ጥቅምት 01/2019 | መስከረም 30/2021 | 0.10 |
| ጠቅላላ ካፒታል (በሚሊዮን ብር) | | | | | | 6.47 |
| ተ. ቁ | በጥናትና ዲዛይን ደረጃ ላይ ያሉ ፕሮጀክቶች | የፕሮጀክቱ ባለቤት | የሚተገበርበት ቦታ | የሚጀመርበት ጊዜ | የሚጠናቀቅበት ጊዜ | የተመደበለት ካፒታል |
| 1 | የጅማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ህንፃና ተያያዥ ስራዎች ግንባታ | ገቢዎች ሚኒስቴር | ጅማ | ሚያዝያ 1/2012 | መጋቢት 30/2015 | 0.36 |
| 2 | የዋናው መ/ቤት የታክስ ስልጠና ማዕከልና ጉምሩክ ላቦራቶሪ ግንባታ | ገቢዎች ሚኒስቴር | አዲስ አበባ | ሚያዝያ 1/2012 | መጋቢት 30/2018 | 1.00 |
| ጠቅላላ ካፒታል | | | | | | 1.36 |

### 10.1.3 የጉምሩክ ኮሚሽን የካፒታል በጀት ፍላጎት ዕቅድ

**ሰንጠረዥ 19፡ የጉምሩክ ኮሚሽን የካፒታል በጀት እቅድ**

| ጠቅላላ ካፒታል (በሚሊዮን ብር) | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ተ. ቁ | አዲስ ወደ ትግበራ የሚገቡ ፕሮጀክቶች | የፕሮጀክቱ ባለቤት | የሚተገበርበት ቦታ | የሚጀመርበት ጊዜ | የሚጠናቀቅበት ጊዜ | የተመደበለት ካፒታል |
| 1 | አዳማ ቢሮ ተያያዥ ግንባታዎች | ጉምሩክ ኮሚሽን | አዳማ | መስከረም 1/2013 | ግንቦት 30/2015 | 0.25 |
| 2 | ጋላፊ የሳይት ኤሌክትሪካልና የሰራተኛ መኖርያ | ጉምሩክ ኮሚሽን | ጋላፊ | ህዳር 1/2014 | ጥቅምት 30/2014 | 0.15 |
| 3 | ጅማ ቢሮና ተያያዥ ግንባታዎች | ጉምሩክ ኮሚሽን | ጅማ | ህዳር 1/2013 | ግንቦት 30/2015 | 0.25 |
| 4 | አ/አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቢሮና ተያያዥ ግንባታዎች | ጉምሩክ ኮሚሽን | አ/አበባ | ህዳር 1/2014 | ህዳር 1/2017 | 0.50 |
| 5 | መቀሌ ቢሮና ተያያዥ ግንባታዎች | ጉምሩክ ኮሚሽን | መቀሌ | ህዳር 1/2013 | ግንቦት 30/2015 | 0.25 |
| 6 | ባሕር ዳር ቢሮና ተያያዥ ግንባታዎች | ጉምሩክ ኮሚሽን | ባሕር ዳር | ህዳር 1/2013 | ግንቦት 30/2015 | 0.25 |
| 7 | አዋሽ ተጨማሪ ቢሮና ተያያዥ ግንባታዎች | ጉምሩክ ኮሚሽን | አዋሽ | ህዳር 1/2015 | ህዳር 1/2016 | 0.10 |
| 8 | ሞጆ ቢሮና ተያያዥ ግንባታዎች | ጉምሩክ ኮሚሽን | ሞጆ | ህዳር 1/2013 | ግንቦት 30/2015 | 0.25 |
| 9 | ድሬዳዋ ቢሮና ተያያዥ ግንባታዎች | ጉምሩክ ኮሚሽን | ድሬዳዋ | ህዳር 1/2013 | ግንቦት 30/2015 | 0.25 |
| 10 | ሞያሌ መኖሪያና ተያያዥ ግንባታዎች | ጉምሩክ ኮሚሽን | ሞያሌ | ግንቦት 1/2012 | ግንቦት 30/2015 | 0.15 |
| 11 | ሀዋሳ ቢሮና ተያያዥ ግንባታዎች | ጉምሩክ ኮሚሽን | ሀዋሳ | ህዳር 1/2013ዓ.ም | ግንቦት 30/2015ዓ.ም | 0.25 |
| 12 | ዋናው መ/ቤት | ጉምሩክ ኮሚሽን | አ/አበባ | ህዳር 1/2014ዓ.ም | ግንቦት 30/2015ዓ.ም | 0.50 |
| 13 | 40 መቅረጫ ጣብያ 40*30 | ጉምሩክ ኮሚሽን | በተለያዩ ቦታዎች | ህዳር 1/2013 | ግንቦት 30/2015 | 1.20 |
| 14 | ካርጎ ስካኒንግ መሰረተ ልማትና ተያያዥ ግንባታ4*35 | ጉምሩክ ኮሚሽን | በተለያዩ ከተሞች | ህዳር 1/2013 | ግንቦት 30/2015 | 0.14 |

| ጠቅላላ ካፒታል (በሚሊዮን ብር) | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ተ. ቁ | አዲስ ወደ ትግበራ የሚገቡ ፕሮጀክቶች | የፕሮጀክቱ ባለቤት | የሚተገበርበት ቦታ | የሚጀመርበት ጊዜ | የሚጠናቀቅበት ጊዜ | የተመደበለት ካፒታል |
| 15 | ጅቡቲ ቅ/ጽ/ቤት | ጉምሩክ ኮሚሽን | ጅቡቲ | ህዳር 1/2014 | ግንቦት 30/2015 | 0.20 |
| ጠቅላላ ካፒታል (በሚሊዮን ብር) | | | | | | 4.69 |
| ተ. ቁ | በጥናትና ዲዛይን ደረጃ ላይ ያሉ ፕሮጀክቶች | የፕሮጀክቱ ባለቤት1 | የሚተገበርበት ቦታ | የሚጀመርበት ጊዜ | የሚጠናቀቅበት ጊዜ | የተመደበለት ካፒታል |
| 1 | አሰሳ መቅረጫና መቆጣጠርያ ጣብያ የቢሮና ተያያዥ ግንባታ | ጉምሩክ ኮሚሽን | አሰሳ | የካቲት 20/2012 | የካቲት 19/2013 | 0.02 |
| 2 | ካርጎ ስካኒንግ መሰረተ ልማትና ተያያዥ ግንባታ | ጉምሩክ ኮሚሽን | በተለያዩ ከተሞች | ግንቦት 15/2012 | ህዳር 14/2012 | 0.04 |
| 3 | መተማ ቢሮ ግንባታ | ጉምሩክ ኮሚሽን | መተማ | ግንቦት 15/2012 | ህዳር 14/2012 | 0.01 |
| ጠቅላላ ካፒታል | | | | | | 0.07 |
| ተ. ቁ | ነባር ፕሮጀክቶች (on-going projects) | የፕሮጀክቱ ባለቤት | ፕሮጀክቱ የሚካሄድበት ቦታ | የተጀመረበት ጊዜ | የሚጠናቀቅበት ጊዜ | የተመደበለት ካፒታል |
| 1 | የኮምቦልቻ ቅ/ጽ/ቤት ቢሮ ህንፃ ግንባታ | ጉምሩክ ኮሚሽን | አማራ ክልል (ኮምቦልቻ) | ህዳር 27/2010 | 26/2011 | 0.08 |
| 2 | የጋምቤላ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት የቢሮና ተያያዥ ግንባታዎች ፕሮጀክት | ጉምሩክ ኮሚሽን | ጋምቤላ ክልል (ጋምቤላ) | Sep 17,2018 | Nov.2/2019 | 0.02 |
| 3 | ቶጎውጫሌ ጉ/መ/ጣቢያ የስካኒንግ መንገድና የአጥር ስራ ግንባታ ፕሮጀክት | ጉምሩክ ኮሚሽን | ሱማሌ ክልል (ሱማሌ) | ሴፕቴምበር 12/2016 | Nov.2/2019 | 0.02 |
| | ጠቅላላ ካፒታል (በሚሊዮን ብር) | | | | | 0.12 |

## 10.2የአምስት ዓመት የሰው ሀብት ፍላጎት ዕቅድ

**ሰንጠረዥ 20፡ ዝርዝር የሰው ሀብት ፍላጎት**

| ትምህርት | 2012 (መነሻ) | በየዓመቱ የሚጨመር | | | | | የሚደረስበት (ድምር) |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 2013 | 2014 | 2015 | 2016 | 2017 | |
| ማህበራዊ ሳይንስ | 8,036 | 3,432 | 2,815 | 1,491 | 677 | 777 | 17,229 |
| ሁለተኛ ድግሪ | 528 | 186 | 152 | 90 | 31 | 38 | 1,025 |
| ሰው ሀብት(Human Resource Management) | 9 | - | - | - | - - | - - | 9 |
| ማርኬቲንግ ማኔጅመንት(Marketing management) | 1 | - | - | - | - - | - - | 1 |
| አካውንቲንግ(Accounting) | 30 | 20 | 17 | 8 | 5 | 5 | 85 |
| አካውንቲንግ እና ፋይናንስ(Accounting and Finance) | 43 | 22 | 18 | 12 | 4 | 5 | 104 |
| ንግድ ስራ አመራር(Business Administration) | 106 | 54 | 44 | 29 | 9 | 12 | 254 |
| ኢንተርፕሪነርሺፕ(Enterpreneurship) | 1 | - | - | - | - | - | 1 |
| መልካም አስተዳደር እና ዕድገት(Good governance and development) | 2 | - | - | - | - | - | 2 |
| ሳይኮሎጂ(Psychology) | 2 | - | - | - | - - | - - | 2 |
| ፐብሊክ ማኔጅመንት(Public management) | 5 | - | - | - | - - | - - | 5 |
| ሎጂስቲክስ እና አቅርቦት(Logistics and Supply) | 1 | - | - | - | - | - | 3 |
| ዲቨሎፐመንት ስተዲስ(Development Studies) | 3 | - | - | - | - - | - - | 3 |
| ኢኮኖሚክስ(Economics) | 32 | - | - | - | - - | - - | 30 |
| ጸሀፊነት እና ቢሮ አስተዳደር(Secretarial Science and Office management) | 10 | - | - | - | - - | - - | 9 |
| ህግ(Law) | 9 | 5 | 4 | 3 | - | 1 | 23 |
| አስተዳደር(Management) | 14 | 5 | 4 | 4 | - | - | 29 |
| ህዝብ ልማት አስተዳደር(Public administration) | 10 | - | - | - | - - | - - | 9 |
| ግዢና ንብረት አስተዳደር(Procurement and Resource management) | 1 | - | - | - | - - | - - | 1 |
| ዲቨሎፐመንት አስተዳደር(Development management) | 24 | - | - | - | - - | - - | 22 |
| ታክስ አስተዳደር(Tax Administration) | 29 | 11 | 9 | 8 | - | 2 | 60 |
| አለም አቀፍ ንግድ(International Trade) | 1 | - | - | - | - | - | 3 |
| ግዢና አቅርቦት(Procurement and supply management) | 4 | - | - | - | - - | - - | 4 |
| ጉምሩክ አስተዳደር(Customs Administration) | 76 | 57 | 47 | 19 | 15 | 16 | 231 |

| ትምህርት | 2012 (መነሻ) | በየዓመቱ የሚጨመር | | | | | የሚደረስበት (ድምር) |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 2013 | 2014 | 2015 | 2016 | 2017 | |
| ፐብሊክ ፋይናንሺያል ማኔጅመንት(Public financial management) | 35 | - | - | - | - - | - - | 33 |
| ታክስ እና ጉምሩክ አስተዳደር(Tax and Customs Administration) | 25 | 9 | 7 | 7 | - | 1 | 49 |
| ፖለቲካል ሳይንስ እና አለም አቀፍ ግንኙነት(Political Science and International Relations) | 1 | - | - | - | - | - | 1 |
| ፐብሊክ ፖሊሲ(Public Policy) | 9 | - | - | - | - - | - - | 9 |
| አመራር እና ለውጥ አስተዳደር(Leadership and Change Management) | 1 | - | - | - | - | - | 1 |
| ፐብሊክ ፋይናንስ(Public finance) | 4 | - | - | - | - - | - - | 4 |
| ዴቨሎፕመንት ኢኮኖሚክስ(Development Economics) | 13 | - | - | - | - - | - - | 12 |
| ፐብሊክ ፕሮኩረመንት(Public procurement) | 1 | - | - | - | - - | - - | 1 |
| ፋይናንስ እና ዴቨሎፕመንት ኢኮኖሚክስ(Finance and Development Economics) | 1 | - | - | - | - - | - - | 1 |
| ፐብሊክ አድሚኒስትሬሽን(Public Administraion) | 1 | - | - | - | - - | - - | 1 |
| ስርዓተ ጾታ(Gender studies) | 1 | - | - | - | - | - | 1 |
| ከተማ አስተዳደር(Urban Management) | 12 | - | - | - | - | - | 12 |
| ገጠር ልማት እና ቤተሰብ ሳይንስ(RDFS) | 1 | - | - | - | - | - | 1 |
| ሊደርሺፕ(Leadership) | 1 | - | - | - | - - | - - | 1 |
| ፕሮጀክት አስተዳደር(Project management) | 2 | - | - | - | - - | - - | 2 |
| ትምህርት ዕቅድ እና አስተዳደር(Education planning and management) | 4 | - | - | - | - | - | 4 |
| የመጀመሪያ ድግሪ | 6,874 | 3,060 | 2,513 | 1,284 | 631 | 712 | 15,073 |
| ጽህፈት(Secretarial Science) | 30 | - | - | - | - - | - - | 28 |
| ፖሊስ ሳይንስ(Police Science) | 5 | - | - | - | - | - | 5 |
| ቋንቋና ስነ ጽሁፍ(Language and literature) | 43 | - | - | - | - | - | 43 |
| ሰው ሀብት(Human Resource Management) | 23 | - | - | - | - - | - - | 22 |
| ማርኬቲንግ ማኔጅመንት(Marketing management) | 167 | - | - | - | - - | - - | 157 |
| አካውንቲንግ(Accounting) | 1,459 | 663 | 538 | 410 | 84 | 125 | 3,279 |
| ላይብረሪ እና ኢንፎርሜሽን ሳይንስ(Library and Information science) | 3 | - | - | - | - | - | 3 |
| ፖለቲካል ሳይንስ(Political Science) | 32 | - | - | - | - | - | 32 |
| አካውንቲንግ እና ፋይናንስ(Accounting and Finance) | 1,184 | 886 | 732 | 291 | 236 | 244 | 3,573 |

| ትምህርት | 2012 (መነሻ) | በየዓመቱ የሚጨመር | | | | | የሚደረስበት (ድምር) |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 2013 | 2014 | 2015 | 2016 | 2017 | |
| ንግድ ስራ አመራር(Business Administration) | 417 | 263 | 216 | 109 | 59 | 65 | 1,129 |
| ንግድና ኢኮኖሚክስ(Business and Economics) | 7 | 6 | 5 | 2 | 2 | 2 | 23 |
| ኢንተርፕሪነርሺፕ(Enterpreneurship) | 2 | - | - | - | - | - | 2 |
| መልካም አስተዳደር እና ዕድገት(Good governance and development) | 23 | - | - | - | - | - | 23 |
| ሳይኮሎጂ(Psychology) | 17 | - | - | - | - - | - - | 16 |
| ሶሾሎጂ(Sociology) | 35 | - | - | - | - - | - - | 33 |
| ትምህርት ዕቅድ እና አስተዳደር(Education Administration) | 71 | - | - | - | - | - | 71 |
| ስነ ዜጋ(Ethics) | 14 | - | - | - | - | - | 14 |
| ስጋት አስተዳደር(Risk management) | 1 | - | - | - | - | - | 3 |
| ፐብሊክ ማኔጅመንት(Public management) | 12 | - | - | - | - - | - - | 11 |
| ታሪክ(History) | 13 | - | - | - | - | - | 13 |
| ባንኪንግ እና ፋይናንስ(Banking and Finance) | 59 | 46 | 38 | 14 | 13 | 13 | 183 |
| ሎጂስቲክስ እና አቅርቦት(Logistics and Supply) | 176 | 149 | 124 | 41 | 44 | 44 | 578 |
| ሆቴል እና ቱሪዝም(Hotel and Tourism) | 2 | - | - | - | - | - | 2 |
| ጂኦግራፊ/ አካባቢ ጥናት(Geography/Environmental Science) | 23 | - | - | - | - | - | 23 |
| ቱሪዝም አስተዳደር(Tourism management) | 3 | - | - | - | - | - | 3 |
| ዲቨሎፕመንት ስተዲስ(Development Studies) | 60 | - | - | - | - - | - - | 56 |
| ኢኮኖሚክስ(Economics) | 884 | - | - | - | - - | - - | 832 |
| ህትመት(Printing) | 1 | - | - | - | - | - | 1 |
| ጸሀፊነት እና ቢሮ አስተዳደር(Secretarial Science and Office management) | 87 | - | - | - | - - | - - | 82 |
| ህግ(Law) | 94 | 59 | 48 | 25 | 13 | 15 | 253 |
| ማናጀሪያል ኢንፎርሜሽን ሳይንስ(Managerial Information Science) | 1 | - | - | - | - - | - - | 1 |
| አስተዳደር(Management) | 1,266 | 818 | 673 | 326 | 191 | 209 | 3,483 |
| ህዝብ ልማት አስተዳደር(Public administration) | 65 | - | - | - | - - | - - | 61 |
| ግዢና ንብረት አስተዳደር(Procurement and Resource management) | 6 | - | - | - | - - | - - | 6 |
